Montgomery County Public Schools
UNLEASHING POTENTIAL

2025-2026

በሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ

# ስለ ተማሪ መብቶች እና ኃላፊነቶች

## የተማሪ መመሪያ

የፌዴራል እና የስቴት ሕጎች፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ፖሊሲ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አስተዳደራዊ ደንቦች እና ሌሎች መመሪያዎች ሊለወጡና እና በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ያሉትን መግለጫዎች እና ማጣቀሻዎች ሊተኩ ይችላሉ።

የተማሪ ስም

ስልክ



# ማውጫ


ፈጣን የማጣቀሻ/የማመሳከሪያ መመሪያ . . . iv
መግቢያ . . . 1
ነፃ የህዝብ ትምህርት . . . 1
ፀረ-መድልዎ . . . 1
የግል ጉዳይን የመጠብቅ መብቶች . . . 2
 ቨርቹዋል ትምህርት ላይ መሳተፍ . . . 2
 የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የደህንነት መቆጣጠሪያ ካሜራዎች . . . 2
 ማስተማር ላይ መሳተፍ . . . 2
የመጠየቅ እና ኃሳብን የመግለጽ ነፃነት . . . 2
 ንግግር . . . 2
 አለባበስ እና ማጌጥ/መዋብ . . . 2
 ስብሰባ . . . 2
 አቤቱታዎች . . . 3
 የታተሙ ጽሑፎች፣ ትግበራዎች እና የመረጃ ቁሳቁሶች . . . 3
 የፖለቲካ ቁሳቁሶች . . . 3
 በፖለቲካ ዘመቻዎች ላይ ስለ መሣተፍ . . . 3
የሀይማኖት ነፃነት . . . 3
የአገር ወዳድነት ልምምዶች . . . 4
የተማሪ ተሳትፎ . . . 4
የተማሪ አስተዳደር . . . 4
 ተሳትፎ . . . 4
 የፋኩልቲ ድጋፍ . . . 4
 የተማሪ አመራር ስልጣን . . . 4
ትምህርት መከታተል . . . 5
 የተፈቀደ መቅረት . . . 5
 ያልተፈቀደ መቅረት . . . 5
 በመቅረት ምክንያት ያመለጠ ስራ . . . 5
የክፍል ስራ . . . 6
 የትምህርት ውጤት አሰጣጥ እና ሪፖርት ማድረግ . . . 6
 የላቀ ችሎታ-Honors፣ ከፍተኛ-ደረጃ፣ እና የላቀ ደረጃ ምደባ (AP) ኮርሶች . . . 6
 በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የተወሰዱ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርሶች . . . 6
የተማሪ ሪከርዶች . . . 6
Synergy ParentVUE/StudentVUE . . . 7
ቴክኖሎጂ . . . 7
 ሃላፊነት የተሞላበት የተማሪ መመርያዎች አጠቃቀም . . . 7
 የግል ሞባይል መሣሪያዎች . . . 7
የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) . . . 8
MCPS ኤክስትራከሪኩለር (ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሚከናወን እንቅስቃሴ) የተማሪ ድርጅቶች እና ቡድኖች . . . 8
 ኤክስትራከሪኩለር . . . 8
 ት/ቤት ስፖንሰር የሚያደርጋቸው ድርጅቶች . . . 8
 ት/ቤት ስፖንሰር የማያደርጋቸው የተማሪ ድርጅቶች . . . 8
 ቡድኖች . . . 8
ደህንነት እና የድንገተኛ አደጋ ማኔጅመንት . . . 8
መጓጓዣ/ትራንስፖርቴሽን . . . 9
የተማሪ ጤና እና ጤናማ ቁመና . . . 10
 የተማሪ የአስቸኳይ አደጋ ጊዜ መረጃ . . . 10
 የመስማት እና የእይታ ምርመራ . . . 10
 ስለ ተማሪ የፀሐይ መከላከያ/ሰንስክሪን አጠቃቀም . . . 10
 ራስን ስለ ማጥፋት ግንዛቤ/Suicide Awareness . . . 10
 ቀውስ ሁኔታ ሲከሰት ክፍት የስልክ መስመር . . . 10
 ስለ አስጊ ባህሪ ግምገማ . . . 10
ስለ መድኃኒት መስጠት . . . 10
 ስለ አናፊላክሲስ እና የምግብ አለርጂ ግንዛቤ . . . 11
 የአናፊላክሲስ መድሃኒት . . . 11
 ስለ ስኳር በሽታ ግንዛቤ እና መድሃኒት . . . 11
 ስለ "Naloxone" እና "Opioid" አደንዛዥ እፆች ግንዛቤ . . . 11
የተማሪዎች የስነምግባር ደንብ . . . 11
ፍተሻ እና መውረስ . . . 11
ጉልበትን ተጠቅሞ ሌሎችን መጉዳት፣ ጭቆና-በደል-ጥቃት፣ ወይም ማስፈራራት . . . 12
 የጾታ ብልግና እና ወሲባዊ ትንኮሳ . . . 13
MCPS የሠራተኛ ስነምግባር ኮድ . . . 13
 ማህበራዊ ሚዲያ፡- የሠራተኞች መልካም ተግባር . . . 13
የይግባኝ- ቅሬታ አቀራረብ ሂደት-የጊዜ ገደብ . . . 13
 በት/ቤት ደረጃ-የሚሰጥ ውሳኔ . . . 13
 የርእሰ መምህር ውሳኔ ይግባኝ . . . 14
 የዲስትሪክት ኦፐሬሽን ዋና ኃላፊ ውሳኔ ይግባኝ . . . 14
አባሪ—የተመረጡ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦች . . . 15–17

# ፈጣን መረጃ ለማግኘት የሚጠቅም መመሪያ
# የተማሪዎች መገልገያዎች/ሪሶርሶች

## በቀውስ ግዜ ክፍት የስልክ መስመር
**24-ሰዓት መረጃ መስጠት፣ሪፈራል፣ እና በውይይት መርዳት**

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ቀውስ ማዕከል**
Hotline/EveryMind/ . . . . . . . . . . . . . 988
እና https://www.every-mind.org/
በይነመረብ ላይ የሚያነጋግሩ ሰዎች ያሉበት እና የድንገተኛ ጥሪ የስልክ መስመር፥ 24 ሰዓት የማወያየት አገልግሎት ይሰጣል።

Montgomery County Crisis Center - 240-777-4000

ሞንትጎመሪ ካውንቲ ቀውስ ማእከል
ቀውስ ማዕከል የአእምሮ ጤና ችግር ላጋጠማቸው ግለሰቦች 24/7 ነፃ የድጋፍ አገልግሎት ይሰጣል።

Trevor Project . . . . . . . 866-488-7386፣ Text 678 678

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ወጣቶች ድንገተኛ የስልክ ጥሪ መስመር፡-**
Youth Crisis Hotline of Montgomery County 988
በሰለጠኑ ካውንስለሮች አማካይነት 24 ሰዓት በስልክ የማማከር ድጋፍ እና ሪፈራል የምስጢር አገልግሎት ይሰጣል።

## የደህንነትና የፀጥታ አስጊ ሁኔታዎችን ሪፖርት ለማድረግ፡-

MCPS የደህነነት እና የድንገተኛ አደጋ ማኔጅመንት ክፍል . 240-740-3066
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤቶችን እና ጽ/ቤቶችን ደህንነት የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለው ቢሮ።

MCPS የተማሪ ምግባር እና ይግባኝ SCA@mcpsmd.org ወይም TitleIX@mcpsmd.org . . . . . . . . . . 240-740-3215
MCPS ዲስትሪክት አቀፍ Title IX አስተባባሪ እና ዲስትሪክት አቀፍ የሕፃናት በደል እና ቸልተኝነትን የሚመለከት ግንኙነት ሃላፊ። የተማሪ ስነምግባር እና ይግባኝ (SCA) ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል፡- www.montgomeryschoolsmd.org/compliance/ SCA ከትምህርት ቤቶች፣ ከህግ አገልግሎት ክፍል፣ እና ከሌሎች የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ቢሮዎች እና ከማህበረሰብ ኤጀንሲዎች ጋር በመተባበር የፖሊሲዎችን፣ የደንቦችን እና የመመሪያዎችን አፈፃፀም ወጥነት ለማረጋገጥ ከሰብአዊ የግንኙነቶች ክፍል ጋር በማቀናጀት ይሰራል። ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ (ታይትል IX ጾታዊ ትንኮሳ ጭምር) እና ማስፈራራት፣ የልጅ ጥቃትን እና ቸልተኝነትን ማወቅ እና ሪፖርት ማድረግ፣ ጥላቻ፣ አድሎአዊነት፣እና የተማሪ ጾታ ማንነት ክስተቶችን በሚመለከት አፈጻጸሙና ትግበራው ወጥነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ይሠራል።

MCPS Cyber Safety dropbox፡- . CyberSafety@mcpsmd.org
MCPS ውስጥ ተገቢ ያልሆነ ኦንላይን እንቅስቃሴን ሪፖርት ማድረጊያ Dropbox።

ከኮምፒተር ኔተዎርኮች ጋር ስለተገናኙ ጉዳዮች የጥቆማ መስመር - Cyber Tipline . . . . . . . . . . . . . . . 1-800-843-5678
24/7 ልጆችን ለወሲብ ድርጊት በማባበል የተጠረጠሩትን ሪፖርት ለማድረግ የድንገተኛ ጥሪ የስልክ መስመር፣ ከቤተሰቦቻቸው ውጪ የሚፈፀሙ ወሲባዊ ድርጊቶች፣የህፃናት ፖርኖግራፊ፣የህፃናት ወሲባዊ ቱሪዝም፣የህፃናት የወሲብ ንግድ፣ለልጆች የሚላኩ ያልተጠየቁ ጸያፍ ቁሶች፣የተሳሳተ/የተጭበረበሩ የተጠቃሚ ስሞች እና አሳሳች ቃላትን ወይም በኢንተርኔት ላይ የሚለጠፉ ዲጂታል ምስሎችን ሪፖርት ለማድረግ 24/7 የሚያገለግል የስልክ መስመር።

Safe Schools Maryland Hotline . . 833-MD-B-Safe (833-632-7233)
ደህንነታቸው የተጠበቀ የሜሪላንድ ት/ቤቶች የአስቸኳይ ጊዜ ጥሪ መስመር 24/7 ስም ሳይገለጽ ነፃ የሪፖርት ማድረጊያ ስርዓት ለተማሪዎች፣ ለአስተማሪዎች፣ ለት/ቤት ሰራተኞች፣ ለወላጆች እና ለጠቅላላው ማህበረሰብ የአእምሮ ጤና ጉዳዮችን ጨምሮ ማንኛ ውንም የት/ቤት ወይም የተማሪ ደህንነት ስጋቶችን ሪፖርት ለማድረግ ያገለግላል። ስልክ የሚደውለውን ሰው ማንነት በመደበቅ ስለተፈጠረው ክስተት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ አግባብ ካላቸው ቢሮዎች ጋር መረጃ ይጋራል።

Montgomery County Child Protective Services, Department of Health and Human Services
የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕፃናት ጥበቃ አገልግሎት፣ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት
(24 ሠዓት ክፍት የስልክ መስመሮች) 240-777-4417 ወይም 240-777-4815 TTY
ተጠርጣሪ የልጅ ጥቃትን ወይም ቸልተኝነትን ለሞንትጎመሪ ካውንቲ የልጆች ደህንነት ጥበቃ አገልግሎት ክፍል ለማሳወቅ 24/7 ሪፖርት የሚቀበል የስልክ መስመር።

ለአደጋ ተጋላጭ ጎልማሶች የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጎልማሶች ጥበቃ አገልግሎት . . . . . 240-777-3000፣ 240-777-4815 TTY
በአዋቂዎች ላይ የሚጠረጠር ጥቃትን እና ቸልተኝነትን ሪፖርት ለማድረግ 24/7 ክፍት የሆነ የስልክ መስመር።

የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፖሊስ መምርያ የልዩ ተጠቂዎች ምርመራ ክፍል (24 ሰዓት) ስልክ፡- . . . . . . . . . . . . 240-773-5400
በልጆችና በጎልማሶች ላይ የሚፈጸሙ የወሲብ ወንጀሎችን፣ የአካል ጉዳተኛ ልጆችን፣ ሸሽተው፣ የጠፉ ልጆች፣ ከባድ የቤት ውስጥ ጥቃት፣ የተጋላጭ አረጋውያን ጥቃት/አደጋ በአዋቂዎች ላይ የሚደርስ በደል፣ እና የተመዘገበ ሪከርድ ያላቸው የወሲብ ጥቃት ወንጀለኞችን ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ መምሪያ ለማሳወቅ 24/7 የስልክ መስመር።

የሞንጎሞሪ ካውንቲ ፖሊስ፡-
የአደንዛዥ ዕፅ እና የወሮበሎች (ጋንግ) የጥቆማ መስመር። 240-773-GANG (4264) ወይም . . . . . . . . . . . . .240-773-DRUG (3784)
በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ህገ-ወጥ እጽ ማዘዋወር/የወሮበሎች ቡድን (ጋንግ) እንቅስቃሴዎችን የሚመለከት ማንነት ሳይገለጽ ጥቆማ ለማቅረብ 24/7 ክፍት የስልክ መስመር።

## MCPS ሪሶርሶች

ካውንቲ አቀፍ የተማሪ አመራር
www.montgomeryschoolsmd.org/departments/student-leadership

ዳይሬክተር፣ የተማሪ አመራር ተግባራት. . . . . . . 240-740-3977

ተማሪ የቦርድ አባል
www.montgomeryschoolsmd.org/boe/members/student.aspx

የትምህርት ቦርድ ጽ/ቤት ስልክ፡- . . . . . . . . 240-740-3030

የትምህርት ቤት አመራር እና ማሻሻያ ክፍል ዋና ኃላፊ . 240-740-3100

የልዩ አገልግሎት ድጋፍ ክፍል . . . . . . . . . 240-740-5630

ሰክሽን 504 አስተባባሪ. . . . . . . . . . . . 240-987-8031

## የሞንትጎመሪ ድንገተኛ ያልሆነ ሪሶርሶች

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ

ድንገተኛ ላልሆነ ጉዳይ የስልክ መስመር. . . . . . . 301-279-8000

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች የመረጃ መስመር
የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ
አጠቃላይ መረጃን ያነጋግሩ . . . . . . . . 311, 301-251-4850 TTY
ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪዎች . . . . . . . . . . . . . -777-0311

## MCPS መረጃ እና የአስቸኳይ ጊዜ ማስታወቂያዎች

በዚህ ድረ-ገጽ አማካይነት ከ MCPS ጋር ሁልጊዜ መገናኘት ይችላሉ፡- www.montgomeryschoolsmd.org

አጠቃላይ ተቋሙን የሚመለከት መረጃና የአስቸኳይ ሁኔታ ማስታወቂያዎችን ለማግኘት፡-

ትዊተር፡- MCPS on Twitter. . . . . . . . . . www.twitter.com/mcps

ትዊተር በስፓንሽኛ፡- MCPS en Español . . www.twitter.com/mcpsespanol

MCPS ፌስቡክ፡- . . . . . . . . . . . . www.facebook.com/mcpsmd

ፌስቡክ በስፓንሽኛ፡- MCPS en Español . www.facebook.com/mcpsespanol

የማንቂያ/የማስጠንቀቂያ መልክቶች፡-
Alert MCPS . . . . . . www.montgomeryschoolsmd.org/alertMCPS

## MCPS መረጃ እና የአስቸኳይ ክስተት ማስታወቂያዎች (የቀጠለ)

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ፈጣን መልክቶች፣ የኢሜይል መልክቶች እና ዘገባዎች
MCPS QuickNotes Email Messages and Newsletter . www.mcpsQuickNotes.org

MCPS የመረጃ አገልግሎትን ይጠይቁ፡-
ስልክ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 240-740-3000
የስፓንሽኛ አስቸኳይ የስልክ መስመር 240-740-2845
Email . . . . . . . . . . . . . . AskMCPS@mcpsmd.org

MCPS የማህበረሰብ መረጃ ቢሮ 240-740-2837
MCPS Television www.mcpsTV.org;
ቴሌቪዥን

Comcast 34, 998; RCN 89, 1058; Verizon 36

በድምፅ የተቀረጸ የአስቸኳይ ጊዜ እና የአየር ሁኔታ መረጃ . . 301-279-3673

## MCPS ሪሶርሶች የሚገኙበት ድረ-ገጽ
www.montgomeryschoolsmd.org

ዳሰሳ ወይም ቅኝት፡-

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ት/ቤቶች የመረጃዎች ዝርዝር ማውጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች የመረጃዎች ዝርዝር ማውጫ

MCPS ስልታዊ (ስትራቴጂያዊ) እቅድ

አትሌቲክስ

Be Well 365

የትምህርት ቦርድ

ጉልበተኝነት፣ ጥቃት/ትንኮሳ፣ ዛቻ/ማስፈራራት

የአውቶቡስ መስመሮች

የልጅ ማጎሳቆል እና ቸልተኝነት

የኮሌጅ እና የሙያ ማዕከል

የግንዛቤ ትምህርት Common Sense Education

የኮርስ ጥንቅር መግለጫ

የማህበራዊ ሚዲያዎችንና ሌሎች የዲጅታል መሳሪያዎችን ኃላፊነት በተሞላበት መንገድ መጠቀምና የኢንተርኔት ደህንነት - Cybercivility and CyberSafety

የዲፐሎማ መስፈርቶች

ወሮበሎች (ጋንግ) እና የወሮበሎች ተግባር

## MCPS የሪሶርስ ድረ-ገጽ (የቀጠለ)
www.montgomeryschoolsmd.org

የውጤት አሰጣጥና ሪፖርት አቀራረብ

የሃይማኖት ብዝሃነትን የማክበር መመርያዎች

ስለ ተማሪ ጾታዊ ማንነት መመሪያ

የምሣ ምግብ ዝርዝር

የሜሪላንድ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ምዘናዎች

ፀረ-መድሎአዊነት

በኦንላይን የመመረቂያ ትምህርት

የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት

መርኆች እና ደንቦች

የስነልቦና አገልግሎቶች

የተማሪ ሠራተኛ አገልግሎቶች

የልጅ መበደል እና ቸልተኝነትን ሪፖርት ማደረግ

ፍትኃዊ ተሐድሶ

በት/ቤት የካውንስሊንግ እገልግሎቶች

የትምህርት ቤት የጤና አገልግሎቶች

የትምህርት ቤት ደህንነት

ፆታዊ ጥቃት

የማህበራዊ ሚድያ ዲጂታል ሲትዝንሽፕ (Social Media Digital Citizenship)

ልዩ ትምህርት

ልዩ ፕሮግራሞች

ስልታዊ የእቅድ ዝግጅት

የተማሪ ስነ-ምግባር ደንብ

የተማሪ በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ መማር - eLearning

የተማሪ ግላዊ ጉዳይ

የተማሪ አገልግሎት ትምህርት

ራስን መግደል መከላከል

የሰመር ትምህርት ቤት Summer School

# መግቢያ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በትምህርት ሂደት ላይ ሲሳተፉ በተማሪዎች እና በሠራተኞች መካከል የአዕምሯዊ እድገትን፣ ዜግነትን፣ ኃላፊነትን እና የጋራ መከባበርን ለማጎልበት የተነደፈ የትምህርት ማህበረሰብን ለመገንባት ይጥራል። የዚህ ማህበረሰብ አባላት እንደመሆንዎ፣ ሁሉም ተማሪዎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ (ቦርድ) ፖሊሲዎች፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦች፣ እና የስቴት እና የፌደራል ህጎች በተቀመጡት መሰረት የተወሰኑ መብቶች፣ ኃላፊነቶች እና ልዩ መብቶች አሏቸው። እያንዳንዱ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባል የሁሉንም ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ሰራተኞች ተፈጥሯዊ ክብር በመገንዘብ እና በማክበር ትምህርትን የሚያዳብር አካባቢን የመፍጠር፣ የመከባበር እና የመደገፍ ሃላፊነት እንደሚጋሩ በፅኑ እናምናለን።

ተማሪዎች ስለራሳቸው ትምህርት፣ ስለ ግላዊ ባህሪያቸው፣ እና መብቶቻቸውን ስለሚጠቀሙበት ሁኔታ ሃላፊነት አለባቸው። በትምህርት ማህበረሰብ ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ ይጠበቅባቸዋል፤ ድርጊታቸው የሚያስከትለውን መዘዝ መቀበል፤ እና ህጎችን፣ የቦርድ ፖሊሲዎችን፣ እና የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦችን እና መመሪያዎችን ያከብራሉ። ስለ ተማሪ መብቶች ሁል ጊዜ ግንዛቤ መወሰድ ያለበት፥የተማሪዎችን፣ የሰራተኞችን፣ የወላጆችን/የአሳዳጊዎችን እና የማህበረሰብ አባላት ጭምር ከሌሎች ሰዎች መብቶች እና ኃላፊነቶች ጋር ያላቸውን ግንኙነቶች ግምት ውስጥ ማስገባት ይጠበቅባቸዋል።

ይህ የመመሪያ መጽሔት ተማሪዎች MCPS ውስጥ ያላቸውን መብቶች እና ኃላፊነቶች የሚገልጽ መመሪያ ሲሆን የስቴት እና የፌደራል ህጎችን፣ የቦርድ ፖሊሲዎችን፣ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦችን እና ሌሎች መመሪያዎችን (እዚህ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ህጎች ተብለው የተጠቀሱትን) አጠቃላይ መግለጫ ይሰጣል። በማንኛውም መመዘኛ ይህ የተማሪ መብቶች ፍጹም የሆነ መግለጫ/ትንታኔ ነው ተብሎ አይታሰብም። እነዚህ አጫጭር ማጠቃለያዎች በመሆናቸው፣ በአንድ ርዕስ ጉዳይ ላይ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ወይም ቤተሰቦች በእያንዳንዱ ክፍል መጨረሻ ላይ የተጠቀሱትን የተወሰኑ ሕጎች፣ ፖሊሲዎች፣ እና ደንቦችን ማንበብ ወይም ለበለጠ መረጃ ከአካባቢያቸው የትምህርት ቤት አስተዳዳሪ ጋር መነጋገር አለባቸው። MCPS ደንብ JFA-RA፣ የተማሪ መብቶች እና ኃላፊነቶች በጠቅላላው ይተገበራል። አንዳንድ የሚመለከታቸው የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦች ዝርዝር በዚህ የመመሪያ መጽሔት ከገጽ 14 ጀምሮ ይገኛል። የቦርድ ፖሊሲዎች እና MCPS ደንቦች እዚህ ይገኛሉ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy.

በዚህ ህትመት ላይ ያሉት የMCPS ህጎች እና ደንቦች ሊለወጡ እንደሚችሉ እና በዚህ ህትመት ውስጥ በተካተቱት ህጎች እና ደንቦች መግለጫዎች እና ማጣቀሻዎች የሚተኩ ይሆናል።

## ■ ነፃ ህዝባዊ ትምህርት

እድሜአቸው ሴፕቴምበር 1 ላይ 5 ዓመት የሞላቸው፣ እና በት/ቤት መጀመርያ ቀን 21 አመት እድሜ ያልደረሱ፣ የሞንጎሞሪ ካውንቲ ነዋሪዎች በካውንቲው ፐብሊክ ስኩልስ ያለክፍያ በነፃ የመማር መብት አላቸዉ። ይህ መብት እስከ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ማጠናቀቅ ድረስ፣ ወይም ተማሪው/ዋ 21 አመት በሚሆንበት/በምትሆንበት የትምህርት አመት መጨረሻ ድረስ፣ የትኛውም ቀዳሚ ቢሆን የሚሰጥ እድል ነው።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪ ተማሪ ዕድሜው(ዋ) 21 ዓመት በሆነበት የትም ህርት ዓመት መጨረሻ ከተወለደ(ች)በት ጊዜ ጀምሮ ነፃ ተገቢ ህዝባዊ ትምህርት የማግኘት መብት አለው።

## ■ አድሎአዊ አሠራርን ስለማስቀረት

ቦርዱ ሁሉም ተማሪዎች እና ሰራተኞች የግለሰብን ትክክለኛ ቁመና ወይም በይሆናል ግምት የሚገነዘቡትን ግላዊ ባህሪያት ማለትም ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ የዘር ግንድ፣ ብሄር፣ ዜግነት፣ ሀይማኖት፣ የስደተ ኝነት ሁኔታ፣ የጾታ ምንነትን ሳይጨምር መከባበርን በሚያጎላ መንገድ እንዲሠሩ ይጠበቃል። ጾታ፣ የፆታ ማንነት፣ የፆታ አገላለጽ፣ ጾታዊ ዝንባሌ፣ የቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ዕድሜ፣ ችሎታ (የግንዛቤ ደረጃ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና የማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግስት ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት፣ ወይም ግንኙነቶች፣ ማንነቶች መከበር አለባቸው።

ማናቸውም ዓይነት ህገወጥ የሆኑ አድሎአዊ አሠራሮች ከትግስት ውጪ ከመሆናቸውም በላይ ተቀባይነት አይኖራቸውም። የቦርድ ፖሊሲ ACA፣ ከአድሎአዊነት የፀዳ፣ ፍትሃዊነት፣ እና የባህል ብቃት፣ ሁሉም ተማሪዎች አለምአቀፍ አስተሳሰብ ባለው ማህበረሰብ ውስጥ እንዲኖሩ እና እንዲሰሩ በሚያዘጋጃቸው ማዕቀፍ ውስጥ እንዲማሩ ያበረታታል፤ እና ሁሉንም ልዩ እና ግለሰባዊ ልዩነቶችን የሚያቅፍ አወንታዊ የመማሪያ አካባቢ እንዲጎለብት ያበረታታል።

መድልዎ በግለሰቦች ላይ በተጨባጭ ቁመናቸው ወይም ግምታዊ በሆነ የግለሰባዊ ባህሪያት ምክንያት የሚሠነዘሩ በጥላቻ፣ በአመጽ፣ በግዴለ ሽነት፣ በንቀት፣ ወይም በበቀል ድርጊቶች—የቃላት ስድብ፣ ትንኮሳ፣ ማስፈራራት፣ ዛቻ፣ አካላዊ ጥቃት የመሳሰሉ ውድመትን ወይም ንብረት ማውደም—የመማር ወይም የስራ አካባቢን የሚያደናቅፉ ወይም የሚጎዱ ድርጊቶችን ያካትታል። አድልዎ፡- ላይላዩን አድሎአዊነት የሌለው የሚመስል ነገር ግን ግለሰብ ባለበት ሁኔታ ወይም የተገመቱ ግላዊ ሁኔታዎች ላይ በመመስረት ተገቢ ያልሆነ ተፅእኖ ያላቸው ስነምግባሮችን ወይም ልምዶችን በተጨማሪ ያካትታል። አድልዎ፡- ዘረኝነትን፣ ፆተዊ ትምክህተኛነት/sexism፣ እና ድርጅታዊ ስር የሰደዱ አግባብነት የሌላቸው ጥላቻዎችን ከሞላ መገለጫዎቻቸው ጋር ያካትታል።

በፍትሃዊነት እና ድርጅታዊ ልማት ዲቪዥን/የተማሪ ስነምግባር እና ይግባኝ ክፍል ከላይ በተዘረዘሩት ግላዊ ባህሪያት ላይ ተመስርቶ በተማሪዎች ላይ የሚፈፀም መድልዎን በሚመለከት በት/ቤት ደረጃ መፍታት ያልተቻለ ቅሬታዎችን፣ ስጋቶችን፣ ወይም ጥያቄዎችን ምላሽ የሚሰጥ አካል ነው። ለተጨማሪ መረጃ፥ በዚህ የመመሪያ መጽሔት የኋላ ሽፋን ውስጠኛው ገጽ ላይ የሚገኘውን የፀረ-መድልዎአዊነት መግለጫ ይመልከቱ። የግል ሁኔታን መሠረት ያደረገ በጉልበት ዛቻ ማድረግ፣ ማስፈራራት፣ ማስጨነቅ፣ ወይም ወከባ ተከስቶ ከሆነ ተማሪዎች MCPS Form 230-35 በመሙላት በጉልበት ማስፈራራት፣ ማስጨነቅ፣ ወይም ወከባ ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ፣MCPS ደንብ JHF-RA ላይ እንደተገለጸውተማሪን ማስፈራራት፣ ማስጨነቅ፣ ወይም ወከባ። የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ቅሬታዎችን ወደ ልዩ ትምህርት አገልግሎት ክፍል ሱፐርቫይዘር/የውሳኔ እና ደንብ አስከባሪ ክፍል ሱፐርቫይዘር ስልክ ቁጥር፡- 240-987-8031 ሊያቀርቡ ይችላሉ።

ማጣቀሻዎች፡-
የቦርድ ፖሊሲ ACA MCPS ደንብ JHF-RA
MCPS የተማሪ ስነምግባር ደንብ(
MCPS የሠራተኛ ስነምግባር ደንብ
ሃይማኖታዊ ብዝሃነትን የማክበር መመሪያዎች
MCPS የተማሪ ጾታ ማንነት መመሪያዎች

## ■ የግል ህይወት/ግላዊ መብት

የተማሪ የግል ህይወት/ግላዊ ጉዳይ በት/ቤት የሥራ ባልደረቦች ይከበራል።

### ቨርቹዋል ትምህርት ላይ መሣተፍ

MCPS ቨርቹዋል ትምህርት የሚያገኙ ተማሪዎች እና ወላጆች/አሳዳጊዎች በኦንላይን የሚያገኙትን የክፍል ትምህርቶቻቸውን ወይም የተማሪ መረጃ ዎችን በማንኛውም መንገድ ቅጂ መያዝ፣ ሪከርድ ማድረግ፣ ማባዛት ወይም ለሦስተኛ ወገን ማጋራት/መለጠፍ የለባቸውም፤ እንዲሁም በማንኛውም ሁኔታ የሌሎች ተማሪዎችን መረጃዎች ከመግለጽ ወይም ለራሳቸውም ከማቆየት መቆጠብ አለባቸው። ሰራተኞቹ የተማሪዎችን ግላዊ መረጃዎች መግለጽ የለባቸውም።

### MCPS የደህንነት ካሜራዎች

በ MCPS የደህንነት መቆጣጠሪያ ካሜራዎች የቪዲዮ ቀረጻ MCPS ንብረት ላይ እንዲሁም በ MCPS የትምህርት ቤት አውቶቡሶች የውስጥ እና የውጪ ካሜራዎችን ጭምር የስነምግባር ጉድለትን፣ የወንጀል ድርጊትን የመሳሰለ ከባድ ክስተት ሊቀረፅ ይችላል። በአጠቃላይ ማንኛውም ተማሪ፣ ሰራተኛ ወይም ጎብኚ MCPS የደህንነት ካሜራዎች ባሉባቸው አካባቢዎች ኮሪደር፣ ካፍቴሪያ፣ ጂምናዚየም፣ አዳራሾች እና ትምህርት ቤቶች ቅጥር ግቢ ውስጥ ህገወጥ ድርጊት/ክስተት ሪከርድ ሲደረግ ወይም ፎቶግራፍ ሲነሳ የግላዊ ሁኔታ/ሚስጥራዊነት ይጋለጣል ተብሎ መጠበቅ የለባቸውም። የመማሪያ ክፍሎች እንደ ህዝባዊ ቦታዎች አይቆጠሩም፥ እንዲሁም MCPS በመማሪያ ክፍል ውስጥ የቪዲዮ ክትትል አያደርግም።

ማንኛውም ተማሪ ወይም ሰራተኛ በእንደዚህ ዓይነት የድምፅ ወይም የቪዲዮ ክትትል በኩል በተሰበሰበ ማስረጃ ላይ ተመስርቶ በዲስፕሊን ሊቀጣ ይችላል። በትምህርት ቤት ንብረት ውስጥ የሚገኙ የማህበረሰብ አባላትም እንደዚሁ ከትምህርት ሠዓት በፊት፣ በትምህርት ሠዓት ላይ ወይም ከዚያ በኋላ በቪዲዮ ካሜራ ክትትል ይደረጋሉ፣ ይህም ለሕግ አስከባሪዎች ሊተላለፍ የሚችል ነው።

### በትምህርት ላይ መሣተፍ

ተማሪዎች ስለቤተሰብ ሁኔታዎች ወይም ግላዊ ልማዶች፣ ግንኙነቶች፣ዝ ንባሌዎች፣ ስጋት፣ ውሳኔዎች ወይም ችግሮች፣ ወይም እራሳቸውን ወይም ቤተሰባቸውን ከሌሎች ጋር ሳያወዳድሩ የግል መረጃን ሳይገልጹ በክፍል ውስጥ ውይይት ላይ መሳተፍ፣ ስራዎችን ማከናወን ወይም በሌሎች መንገዶች የትምህርት አላማዎችን የማሟላት መብት አላቸው።

*ማጣቀሻዎች፡–*
MCPS ደንብ EGF-RB
MCPS ደንብ JOA-RA

## ■ የመጠየቅና ሀሳብን የመግለጽ ነፃነት

### ንግግር

በስቴት ወይም ካውንቲ የስርአተ-ትምህርት ሰነዶች የተቀመጡትን ገደቦች ባልጣሰ ሁኔታ ተማሪዎች አማራጭ ሀሳቦችን እንዲገመግሙ እና የራሳቸውን አስተያየት መያዝ እንዲችሉ ግላዊ አስተያየታቸውን መግለጽ፤ እና የመደ ምደሚያ ሀሳብ ላይ ከመድረሳቸው በፊት መረጃ መተንተን እና መገምገም እንዲችሉ፤ በአከራካሪ/አነጋጋሪ ርእሶች ላይ የተለያዩ ሀሳቦች የማግኘት መብት አላቸው፤። ተማሪዎች በኮርሶቻቸው ውስጥ የቀረቡትን ርዕሶች በቁም ነገር የማገናዘብ እና በውይይት በተነሱት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የተገ ለጹትን የተለያዩ አመለካከቶች ለማሻሻል ሀሳባቸውን ለመጨመር በክፍል ውይይቶች ውስጥ የመሳተፍ ሃላፊነት አለባቸው፤ እርስ በእርስ የመከባበር ድባብን ለመጠበቅ የተለያዩ አስተያየቶችን ማክበር፣ እና ምቹ የመማር እና የሥራ አካባቢን የሚጎዳ፣ ከዓላማው ጋር የማይጣጣም ጸያፍ፣ ነውረኛ፣ ሐሜተኛ፣ ጸያፍ ንግግርን፣ ማስፈራራት ወይም የማስፈራራት ዓላማ ካለው የቃላት አጠቃቀም መታቀብ አለባቸው። በተጨማሪም፥ ቦርዱ ቋንቋን እና/ ወይም ጥላቻን የሚያራምዱ እና በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክቱ ሥራዎች ወይም እንቅስቃሴዎች ላይ ከፍተኛ ጫና/መሰናክል ሊያስከትሉ የሚችሉ ምስሎችን እና ምልክቶችን ማሳየትን ይከለክላል። ሆኖም የእን ደዚህ ዓይነቶቹ የቃላትና የቋንቋዎች ክልከላ ኃላፊነት ለተሞላበት ውይይት፣ ምስሎች ወይም ምልክቶችን ለትምህርት ዓላማዎች እንዳይውል ለመከላከል ጥቅም ላይ አይውልም።

### አለባበስ እና ማጌጥ/መዋብ

ተማሪዎች ቨርቹዋል ትምህርትን ጨምሮ፣ በማህበረሰብ የአለባበስ እና የማጌጥ መስፈርቶች መሰረት የትምህርት ድባብን እና የትምህርት ቤት ተግባሮችን በማይረብሽ ሁኔታ ለትምህርት ቤት በተገቢ ሁኔታ ራሳቸውን የማዘጋጀት፣ የመልበስ እና የመዋብ ሃላፊነት አለባቸው። ተማሪዎች የአለ ባበስ ዘይቤያቸው ከሚከተለው መመሪያ ጋር እስካልተከተለ ድረስ ከሃይ ማኖታቸው ጋር የተያያዙ ወይም ሃይማኖታዊ መልዕክቶችን የያዙ አንገት ልብስ፣ ሂጃብ፣ ያርሙለክስ፣ ፓትካስ ወይም ሌላ ልብስ ወይም ጌጣጌጥ እንዲለብሱ ይፈቀድላቸዋል። የተማሪዎች አለባበስ — መሆን የሌለበት

- የራስን ወይም የሌሎችን ጤንነት እና/ወይም ደህንነት አደጋ ላይ ሊጥል ወይም ሊያስፈራራ የሚችል መሆን የለበትም፤
- የኮርስ ስራን ወይም እንቅስቃሴ መስፈርት የማያሟላ መሆን የለበትም፣
- የጥላቻ ወይም አድሏዊ መልዕክቶችን የሚያስተላልፍ ወይም አድሏዊ ምልክቶችን ወይም ምስሎችን የሚያሳይ መሆን የለበትም፣
- የወሮበላ/የጋንግስተር ቡድኖችን አለባበስ የሚያንፀባርቅ መሆን የለበትም፣
- ሴሰኝነትን፣ ብልግናን፣ ዋልጌነትን የሚያንፀባርቅ ጸያፍ፣ ወይም ገላጭ ወይም ወሲባዊ ተፈጥሮን የሚያነሳሳ መሆን የለበትም፣ እና/ወይም
- በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ውስጥ የማይፈቀዱ መድሃኒቶችንና እፆችን ማስተዋወቅ IGO-RA ደንብ፣ አልኮል፣ ካናቢስ፣ ትምባሆ፣ እና ሌሎች ተማሪዎችን የሚመለከቱ የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም መመሪያዎች ላይ በተገለጸው መሰረት የተከለከለ ነው።

በተቻለ መጠን፣ በሃይማኖታዊ እምነቶች ላይ በመመስረት ተገቢውን ልከኝነት ለማረጋገጥ የአካል ማጎልመሻ ትምህርት ክፍል ወይም በትምህርት ቤት በሚደገፉ እንቅስቃሴዎች ወቅት የተወሰኑ ልብሶችን ለመልበስ ወይም ላለመልበስ ፈቃድ ከጠየቁ ትምህርት ቤቶች ለተማሪዎቹ ምክንያታዊ መስተ ንግዶ መስጠት አለባቸው። የዚህ አይነቶቹ መስተንግዶዎች/ማመቻቸቶች የተማሪን በአንድ እንቅስቃሴ መሳተፍ አይከለክሉም/አያግዱም። ለምሳሌ፡- የሜሪላንድ ፐብሊክ ስኩልስ አትሌቲክስ ማህበር በት/ቤቶች መካከል በሚካሄዱ ውድድሮች የሚሳተፉ አትሌቶችን "የራስ መሸፈኛ፣ ጥምጣም፣ ወይም ሌላ አስፈላጊ የሆኑ ሀይማኖታዊ ልብስ ለተጫዋቾች ወይም ለሌሎች ሻካራ፣ ጠንካራ፣ ወይም አደገኛ ያልሆነ፣ እናም በጨዋታ ጊዜ ተመንጥቆ የማይሄድ/ተገፎ የማይወድቅ አይነት አለባበስ እንዲለብሱ" ይፈቅዳል። የአትሌቲክስ አኮሞዴሽንን በሚመለከቱ ሌሎች ጥያቄዎች፣ እባክዎ የትም ህርት ቤቱን የአትሌቲክስ ዳይሬክተር ወይም የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የአትሌቲክስ ክፍል ያማክሩ።

*ማጣቀሻዎች፡–*
*MCPSየተማሪ ስነምግባር መመሪያ*
*በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የሀይማኖት ብዝሃነትን የማክበር መመርያዎች*

### ስብሰባ

ተማሪዎች ለነሱ አሳሳቢ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ውይይት ለማድረግና በሰላማዊ መንገድ ለመሰለፍ የመሰብሰብ መብት አላቸው። ተማሪዎች ያቀዱት ተግባር/እንቅስቃሴ በት/ቤት ቀን ይፈቀድ እንደሆን እና እንዳልሆነ፣ የሚካ ሄድበትን ሰአት እና ቦታ፣ እንዲሁም የሚያስፈልገውን የቁጥጥር አይነት በተመለከተ ከት/ቤት አስተደደር ጋር የመማከር ኃላፊነት አለባቸው። ተማሪዎች በተጨማሪ ከት/ቤት ሰራተኞች ጋር ተባብሮ የመስራት፣ እንቅ ስቃሴው ስርአት የያዘ መሆኑን ለማረጋገጥ እርምጃዎች የመውሰድ፣ እና የተሳተ ስራን የማካካስ ሀላፊነት አለባቸው።

በማናቸውም የትምህርት ቀን ከካምፓስ ጥሎ መውጣት የትምህርት ሥራ ሂደትን የሚያደናቅፍና በሚኖረዉ ተፅዕኖ ያለፈቃድ እንደመቅረት ይቆጠራል።

### አቤቱታዎች

ተማሪዎች ከት/ቤት አስተዳዳሪዎች የመገናኘትና አለመግባባቶችን ማጣራትና ለአቤቱታ መነሻ በሆኑ ርእሶች የመረጃ መለዋወጫ መድረክ የማዘጋጀት ሃላፊነት አለባቸው። የት/ቤት ሥራዎችን እስካላደናቀፉ ድረስ፣ ተማሪዎች አቤቱታዎችን ከትምህርት ክፍለጊዜ ውጭ የማሰራጨት መብት አላቸው። ተማሪዎች የሚያቀርቧቸው አቤቱታዎች የተማሪዎችን እና ሌሎች በት/ቤት ማህረሰብ የሚገኙ ሰዎችን ጤና ወይም ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥሉ ድርጊ ቶችን የማያበረታቱ መሆናቸውን እንዲሁም ስም የሚያጠፋ/የሚያንቋሽ

ወይም ባለጌ/ጸያፍ አለመሆናቸውን ወይም በሌላ ሁኔታ በት/ቤቱ የሥራ እንቅስቃሴ ላይ ጉልህ ማስተጓጎል የማያስከተሉ መሆናቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው። ይህን ሃላፊነት ለማሟላት ካልቻሉ የት/ቤቱ አስተ ዳደር የአቤቱታዎችን መሰራጨት ለማቆም/ማስቆም ይችላል። በት/ቤት ደረጃ፣ ተማሪዎች በአምስት የትምህርት ቀኖች ውስጥ መልስ የማግኘት መብት አላቸው።

### ሕትመቶች፣ (የመድረክ) ዝግጅቶች፣ እና የመረጃ መገልገያዎች

ሕትመቶች፣ ትርኢቶች/ዝግጅቶችን፣ እና የመረጃ ቁሳቁሶችን በተመለከተ ተማሪዎች የሚከተሉት መብቶች አሏቸው።

- ተማሪዎች በት/ቤት የተደገፉ ሕትመቶችን (ለምሳሌ:- ጋዜጣዎች፣ ዓመታዊ መጽሔት፣ የሥነጽሑፍ መጽሔቶች) እና በት/ቤት የተደገፉ እንቅስቃሴዎችን (ለምሳሌ:- የት/ቤት ጭውውቶች፣ እና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች) ለማዘጋጀት መብት አላቸው።
- ከዚህ በታች ባሉት መመሪያዎች እና በት / ቤቱ ስፖንሰር መመሪያ እና መመሪያ መሠረት በትምህርት ቤት በሚደገፉ ህትመቶች እና ትርኢቶች ይዘት ላይ ተማሪዎች የመወሰን መብት አላቸው።
- ተማሪዎች ት/ቤት ስፖንሰር ያላደረጋቸውን ህትመቶች የማሰራጨት መብት አላቸው፣ ህትመቶቹ የስፖንሰር አድራጊውን ድርጅት ወይም ግለሰብ ስም እስከያዙ/እስካሳዩ ድረስ ወይም የሚሸጡ ወይም በሌላ ሁኔታ የሚሰራጩ ህትመቶች ከሆኑ ደግሞ በMCPS ውስጥ በሚ(ምት) ማር ተማሪ እስከሆኑ ድረስ።
- ተማሪዎች የት/ቤት ሥራዎችን የማይመለከቱ የተማሪ ህትመቶችን ስርጭት ለመቆጣተር ካለው የአሠራር መመሪያ ተመሳሳይ ገደቦችን በማይጻረር መልኩ በማስታወቂያ ሰሌዳዎች ላይ፣ ግድግዳ ቦታዎች ላይ ወይም ሌሎች ማስታወቂያ ለመለጠፍ በተዘጋጁ ቦታዎች ላይ በት/ቤት ያልተዘጋጁ ቁሳቁሶችን የማሳየት፣ የመለጠፍ፣ የማስተዋወቅ መብት አላቸው።
- ተማሪዎች በአካባቢ ት/ቤት በተዘረጋው አካሄድ ወይም "MCPS ደንብ JFA-RA" ስለ ተማሪ መብት እና ግዴታዎች/ሃላፊነቶች በተገለጸው መሠረት የት/ቤትን ድጋፍ ሰጭ አካል/ስፖንሰርስ ውሳኔ ይግባኝ የመጠየቅ መብት አላቸው።

ርእሰመምህሩ(ሯ) በሚከተለው መስፈርት ብቻ የተማሪን የሥራ ውጤት ወይም የስነ ጽሑፍ ህትመት ወይም ሌላ የመረጃ ቁሳቁስ ስርጭት በቅድሚያ መገደብ፣ ማቆም ወይም ውድቅ ማድረግ ይችላል-ትችላለች።

- ጸያፍ፣ የሚያጥላላ፣ የብልግና፣ የሚያነሳሳ፣ ስም የሚያጠፋ፣ አስነዋሪ፣ ወይም የትንኮሳ፣ የማስፈራራት፣ የማሸማቀቅ ቋንቋዎችን ያዘለ ከሆነ፤
- መተማመኛ/ማረጋገጫ የሌለው ግላዊነትን የሚዳፈር ከሆነ፤
- ተማሪዎችን ግልጽና ሊፈጸም የሚችል አደጋ እንዲጠነስሱ የሚያነሳሳ ከሆነ፣ (a) ሕገ-ወጥ ድርጊት መፈጸም፣ የቦርድ ፖሊሲ እና/ወይም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ህጎች ጥሰት፣ ወይም (b) የት/ቤትን ሥርዓትና የሥራ ሂደት ማቴሪያላዊ/አይነተኛ በሆነ መልኩ የሚያደናቅፍ/የሚያስተጓጉል ከሆነ። "ከባድ ማስተጓጎል" ማለት፣ በት/ቤት ስራ ጣልቃ መግባት፣ ወይም በርካታ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ሥርዓት በሌለው ሁኔታ ለአመፅ መነሳሳት፣ አድሞ ከት/ቤት መቅረት፣ አድሞ መቀመጥ፣ ንብረት ማውደም፣ እና ለቆ መውጣት።
- የስቴት ወይም የፌደራል ሕግን የሚፃረር ከሆነ፤ ለምሳሌ:- በተማሪዎች ጤና እና/ወይም ደህንነት ላይ አደጋ ሊያስከትል የሚችል ዕፅ፣ አልኮሆል፣ እና የትምባሆ አጠቃቀምን ወይም ማንኛውንም ዓይነት ንጥረነገር ማጨስን፣ ዓመፅ፣ ወሲባዊነትን፣ ሕገ -ወጥ መድልዎን፣ ወይም ሌሎች ሕገ -ወጥ ተግባራት።

ቢሆንም ስለእንደነዚህ ያሉ ድርጊቶች ኃላፊነት የተሞላበት ውይይት እንዳ ይካሄድ ለመከልከል ይህን መመሪያ መጠቀም አይገባም። የአንድን ተማሪ ዝግጅት፣ የተማሪን ህትመት፣ ወይም የተማሪዎች የጽሁፍ/ማቴሪያል ስርጭት ማስቆምን በተመለከተ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ርእሰ መምህራን መከተል የሚገባቸውን አካሄድ MCPS ደንብ JFA-RA ዘርግቷል።

### የፖለቲካ ቁሳቁስ

ማንም ሰው፣ ህገ መንግስታዊ ያልሆነ፣ ህገ ወጥ፣ የስቴት የምርጫ ህጎችን የሚፃረር፣ ወይም፣ በርእሰ መምህሩ/ሯ አስተያየት፣ ለትምህርት አካባቢ የረብሻ አደጋ ያመጣል ተብሎ የተገመተ የምርጫ ዘመቻ ፅሁፍ ማሰራጨት አይችልም። ይህ ውሳኔ ይግባኝ ሊባልበት ይቻላል። የይግባኙ ቅደም ተከተል በዚህ መፅሔት (ገፅ 13) የይግባኝ-አቤቱታ አቀራረብ ሂደት ላይ ተገልጿል።

ሌሎች ፖለቲካዊ ቁሳቁሶች በነዚህ ህጎች መሰረተ ሊሰራጩ ይችላሉ:-

- ለሁሉም ሰው ከመስጠት ይልቅ ፍላጎት ያላቸው ሰዎች እንዲወስዱ/እንዲመለከቱ የተዘጋጁ ቁሳቁሶች። በዚህ ደንብ መሰረተ የሚከናወኑ የስርጭት ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ:- ፍላጎት ላላቸው ሰዎች ብቻ ቁሳቁሶችን መስጠት፣ የሚታይበት ቦታ ማዘጋጀት፣ ወይም በማስታወቂያ ሰሌዳዎች ላይ መለጠፍ።
- ተማሪዎች በመማርያ ክፍሎች፣ በሚድያ ማእከል፣ ወይም በሌሎች የት/ቤት ክፍሎች በትምህርት ቀን የፖለቲካ ቁሶችን ማሰራጨት አይችሉም፣ ከነዚህ በስተቀር-
  - ክፍሉ ለፈቃደኛ መሰብሰቢያ ጥቅም የሚውል ከሆነ፣ ወይም
  - ማቴሪያሉን በክፍል ውስጥ የመደበኛ ማስተማሪያ ፕሮግራም አካል፣ ወይም የበጎ ፈቃድ መድረክ፣ ወይም በተማሪዎች የሚካሄድ ሴሚናር ላይ መጠቀሚያ ሲደረግ።
- የፖለቲካ ቁስ ሁልጊዜ ከትምህርት ክፍለጊዜ ውጭ ብቻ መሠራጨት አለበት።
- የምርጫ ዘመቻ ቁሳቁሶች የፈቃድ መስመር እንዲኖራቸው ያስፈልጋል (MCPS ደንብ KEA-RA፣ በፖሊቲካ ምርጫ ዘመቻ ተሳትፎና የምርጫ ውድድር ቁሳቁሶች ስርጭትን) ይመልከቱ።

### ተሳትፎ በፖሊቲካ ምርጫ ውድድሮች

በፖለቲካ ዘመቻ በመሳተፍ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት ሠዓቶችን ለማግኘት ተማሪዎች MCPS Form 560-50, Individual Student Service Learning (SSL) Requestበመሙላት ለማንኛውም የፖለቲካ አገልግሎት ቢሮ ለሚወዳደር ሰው አገልግሎት ከመስጠቱ በፊት ጠይቆ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል።

*ማጣቀሻዎች:-*
*የቦርድ ፖሊሲ* KBA፣ *ስለ ህዝብ የመረጃ አሰጣጥ ፖሊሲ*
MCPS ደንብ JFA-RA፣ KBA-RB፣KEA-RA፣ IGT-RA፣ እና IID-RA

## ■ የሃይማኖት ነፃነት

ተማሪዎች የሚከተሉት መብቶች አሏቸው—

- ከኃይማኖት ጋር ያልተያያዙ/ገለልተኛ ከሆኑና የኃይማኖት ነክ ድርጊቶችን የማያካትቱ በት/ቤት አማካይነት የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች፣ እና
- በኮርሶች ወይም ት/ቤት በሚያካሄዳቸው የምረቃ ፕሮግራሞች ወይም ስብሰባዎችን በመሳሰሉ እንቅስቃሴዎች ኃይማኖት ነክ እምነቶች በማይሰበክባቸው አካባቢ፤ እና
- የሌሎችን መብት ካልጣሱ ወይም የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎችን ካላስተጓጉሉ በቀር በትምህርት ቤት የማይደገፉ የተማሪ የጸሎት ቡድኖችን ጨምሮ በትምህርት ቤት ውስጥ የሃይማኖታዊ ልምዶቻቸውን ማክበር።

ቦርዱ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተማሪ ማህበረ ሰብን ልዩ ልዩ ኃይማኖቶች፣ እምነቶች፣ እና ባህሎችን ለማክበርና እውቅና ለመስጠት ቁርጠኛ ነው። MCPS በነዚህ አርእስቶች ላይ ዲስትሪክቱ የሚመራበትን MCPS-ህጎች በተመለከተ እንደ ማጣቀሻ የሃይማኖት ብዝሃ ነትን የማክበር መመሪያዎችን አዘጋጅቷል።

*ማጣቀሻዎች:-*
*ሃይማኖታዊ ብዝሃነትን የማክበር መመርያዎች*
MCPS ደንብ IKB-RA

## ■ የአገር ወዳድነት እንቅስቃሴዎች

ተማሪዎች በት/ቤት በሃገር ወዳድ እንቅስቃሴዎች ለመሳተፍ እና/ወይም ለማየት እድል ይኖራቸዋል።

ተማሪዎች በአገርወዳድነት እንቅስቃሴዎች ለመሳተፍ ፈቃደኛ ካልሆኑ እንዳ ይገደዱ፣ ወይም ቅጣት እንዳይደርስባቸው፣ ወይም ሃፍረት እንዳይደርስ ባቸው መብታቸው የተጠበቀ ነው።

አንድ ተማሪ ሌሎች የአገር ወዳድ እንቅስቃሴዎች በሚሳተፉት ላይ ጣልቃ በመግባት ማስተጓጎል/ማቃወስ አይ(ት)ችልም።

*ማጣቀሻዎች፡-*
በሜሪላንድ የትምህርት ኮድ (Annotated Code of Maryland)፣ የትምህርት አንቀፅ፣ §7-105

## ■ የተማሪ ተሳትፎ

ተማሪዎች ስለ እያንዳንዱ ኮርስ አጠቃላይ ዓላማዎች እና አፈፃፀማቸው የሚገመገምበትን መሠረት ይገለጽላቸዋል። ተማሪዎች በትምህርት ክፍል እንቅስቃሴዎች የመሳተፍና ለትምህርት ክፍል ደንቦች፣ ግዴታዎች፣ እና የአፈፃጸም ሂደቶች የመገዛት ሃላፊነት አለባቸው።

ተማሪዎች ከፋከሊቲው ጋር በመመካከር፥ በትምህርት ቀን ከመደበኛ ፕሮግራም በተጨማሪ እና/ወይም ከት/ቤት ቀን ውጭ ፍላጎት በሚኖራቸው ፕሮግራሞች፣ የበጎ ፈቃድ ፕሮግራሞች፣ በተመረጡ ርእሶች ላይ ሴሚና ሮችን፣ ስብሰባዎችን፣ ወይም አጫጭር የትምህርት ኮርሶች እንዲሰጡ ሀሳብ ሊያቀርቡ ይችላሉ።

ተማሪዎች ፕሮግራሞችን ለመንደፍ/ለመቅረጽ ከርእሰ መምህራን እና ከአስተዳደር አባላት ጋር ተባብረው ይሰራሉ። ፕሮግራሞች ከድስትሪክቱ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ እና ከ MCPS መሠረታዊ የትምህርት ተልዕኮ ጋር የሚስማሙ፣ ከሚመለከታቸው ዕድሜ እና ብስለት ጋር ተስማሚ መሆን አለባቸው፣ እና አወዛጋቢ በሆኑ ርዕሶች አቀራረብ ላይ ሚዛናዊነትን በመፍጠር የተዋቀሩ መሆን አለባቸው።

ተማሪዎችን የሚመለከት ዋና ዋና የቦርድ ፖሊሲ ክለሳ ወይም ቀረጻ በሚደረግ ጊዜ የተማሪ ተወካዮች እንዲሳተፉ ይደረጋል።

እንደዚህ ዓይነቱ ተሳትፎ ሊከናወን የሚችለው በስብሰባዎች ላይ የተማሪ ተወካዮችን በማሳተፍ፣ ወይም ክለሳው በማናቸውም ደረጃ ላይ እያለ ተማሪ አስተያየት እንዲሰጥበት በመጠየቅ ይሆናል። ተማሪዎች ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ዋና የአካባቢ ት/ ቤት መመሪያ ወይም ደንቦች ክለሳ ወይም በዝግጅት ሂደት ውስጥ በተመሳሳይ መልኩ የመሳተፍ መብት አላቸው። ተማሪዎችን የሚመለከቱ አበይት የአካባቢ ት/ቤት መመር ያዎች ወይም ደንቦች ከመዳበር ወይም ከመከለሳቸው በፊት የተማሪ አስተያየት እንዲሰጥባቸው ለተማሪዎች አመቺ በሆኑ ቦታዎች ላይ ቅጅዎች ከበቂ (አስተያየት መስጫ) ጊዜ ጋር ይቀመጣሉ/ይለጠፋሉ።

የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች ተማሪው(ዋ) በስቴት መስፈርት ተፈላጊ በሆነው አጠቃላይ የጤና ሥርዓተ ትምህርት "ስለ ቤተሰብ ሕይወት በሚሰጥ የክፍል ትምህርት ላይ እንዳይሳተፍ-እንዳትሳተፍ ከጠየቁ ለተማሪው(ዋ) ተለዋጭ ትምህርት ይሰጣል። MCPS ደንብ IGP-RA አጠቃላይ የጤና ትምህርት ማስተማሪያ ፕሮግራምን ይመልከቱ።

## ■ የተማሪዎች አመራር

### ተሳትፎ

ተማሪዎች የተማሪ አመራር/አስተዳደር የመመስረት፣ የማካሄድ፣ እና የተሳትፎ መብት አላቸው። ተማሪዎች በተማሪ አስተዳደር ድርጅት አማካ ኝነት በት/ቤት ጉዳዮች ድምፃቸውን የማሰማት መብት አላቸው። ተማሪዎች ተጠያቂነቱ ለተማሪዎች የሆነ ውጤታማ የተማሪ አስተዳደር ድርጅት ለመፍጠር የመስራት ሃላፊነት አለባቸው። ማናቸውም በህጋዊ መንገድ በትምህርት ቤት የተመዘገቡ እና በትምህርት ቤቱ ህግ-የተቀመጡትን መመዘኛዎች የሚያሟሉ ተማሪዎች በተማሪ አስተዳደር ውስጥ ለመወዳደር እና ለመመረጥ ይችላሉ። በተማሪዎች አስተዳደር መሳተፍ የአገልግሎት ትምህርት ሰአቶችን ማግኘት ያስችላል።

### የመምህራን/የፋኩሊቲ ድጋፍ

የት/ቤት ሠራተኞች አባላት የተማሪን በተማሪ አስተዳደር የመሳተፍ መብት ይደግፋሉ። ርእሰ መምህሩ ተማሪዎች በት/ቤት ጉዳዮች ላይ ድምጽ እንዲ ኖራቸው በተማሪዎች አመራር ድርጅት በኩል ተግባራዊ ያደርጋል/ታደር ጋለች።

በፀደይ/ስፐሪንግ ወራት፣ የተማሪ አስተዳደር ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ለሚመጣው አመት የአማካሪ መሾምን በሚመለከት ከርእሰ መምህሩ/ሯ ጋር ይመክራል፣ እናም አማካሪው/ዋ ከመሾሙ/ሟ በፊት የተማሪዎቹ አስተያየት በጥንቃቄ ይታያል።

የት/ቤት ሥራ ባልደረቦች የተማሪ አስተዳደር/አመራር የሚያስፈልገውን መገልገያ ግብአቶች እና መጠቀሚያ ክፍሎችን በመስጠት ይረዳሉ።

በት/ቤት አስተዳደር የተፈቀደ የተማሪ አመራር/አስተዳደር እንቅስቃሴዎች ላይ ለመሳተፍ የትምህርት ክፍለ ጊዜ የተጓደለባቸው ተማሪዎች በምክንያት የቀሩ ተደርጎ ይቆጠራል እና ያመለጣቸውን የትምህርት ሥራዎች የማካካስ ኃላፊነት አለባቸው።

### የተማሪዎች አስተዳደር ስልጣን

እንደአስፈላጊነቱ ከት/ቤት ሰራተኞች/አማካሪ ጋር በመማከር ተማሪዎች ለተማሪ አስተዳደሩ መተዳደርያ ደንብ ወይም በስራ ላይ ላለው መተዳደርያ ደንብ ማሻሻያዎች በፅሁፍ የማዘጋጀት ሃላፊነት አለባቸው። ሁሉም የመተ ዳደርያ ደንቦች የርእሰ መምህሩ(ሯ)ን ውሳኔ የመስጠት ስልጣን እውቅና የሚሰጥ አንቀፅ ማካተት አለባቸው። MCPS ደንቦችን ካልጣሰ ወይም በት/ ቤት አሠራር ላይ ከፍተኛ ጣልቃ ገብነት ከሌለው በስተቀር ተማሪዎች የተማሪ አመራር ደንብ እንዲጸድቅ ወይም ማሻሻያዎች እንዲደረጉ ርእሰመ ምህርን የመጠበቅ መብት አላቸው። ያልፀደቀበት ምክንያቶች ለተማሪዎች በፅሁፍ ይገለፅላቸዋል የአስተዳደሩን ቅሬታዎች አስመልክተው የመተዳደርያ ደንቡን ለመከለስ እድል መሰጠትም አለባቸው።

ተማሪዎች፣ በተማሪዎች አስተዳደር አማካይነት፣ በተማሪ አስተዳደር ለሚቀርቡ ማሳሳቢያዎች በአምስት የትምህርት ቀኖች ውስጥ ከት/ቤቱ አስተዳደር መልስ የማግኘት መብት አላቸው። ማሳሰብያዎች ተቀባይነት ካላገኙ ወይም ከተሻሻሉ አስተዳደሩ፣ በጽሁፍም ሆነ በቃል፣ ምክንያ ቶችን ያቀርባል/ይሰጣል። ማሳሰቢያዎቹ ሰፊ ወይም ውስብስብ ከሆኑ፣ የት/ቤቱ አስተዳደር፣ ከተማሪዎች አስተዳደር ተወካዮች ጋር በመመካከር፣ የቃል ወይም የፅሁፍ መልስ የሚሰጥበትን ተቀባይነት ያለው የጊዜ ገደብ ይወስናል።

የስራ አስፈፃሚው ኮሚቴ፣ የተማሪዎች አስተዳደር አማካሪ፣ እና ርእሰ መምህሩ/ሯ በየወቅቱ እየተገናኙ ስለ ተማሪዎች አስተዳደር ድርጅት ግስጋሴና ቅሬታዎች ይመካከራሉ።

*መጣቀሻዎች፡-*
የቦርድ ፖሊሲ IQD
MCPS ደንብ IQD-RA እና IQD-RB
MCPS የተማሪ አመራር፡- 240-740-4691
(http://www.montgomeryschoolsmd.org/departments/student-leadership/ )

## ■ በትምህርት ላይ መገኘት፣መከታተል፣ መሳተፍ

ለተማሪ ስኬት በትምህርት ገበታ ላይ በየእለቱ መገኘት፣መከታተል፣ መሳተፍ አስፈላጊ ሲሆን እንዲሁም አንድን የትምህርት ቁሳቁስ በደንብ ማወቅን ለማሳየትና የኮርሶች ክሬዲትም ለማግኘት ይጠቅማል/ያስፈልጋል። ተማሪዎች ት/ቤት እንዲከታተሉ እና ወደ ት/ቤትና የመማርያ ክፍሎች በወቅቱ እንዲደርሱ ይጠበቅባቸዋል።

ተፈቅዶላቸው ካልሆነ በስተቀር፣ ተማሪዎች በትምህርት ቀን በመማርያ ክፍሎችና በሌሎች ተፈላጊ እንቅስቃሴዎች ላይ መገኘት አለባቸው። የተማሪ በትምህርት ላይ መገኘት፣መከታተል፣መሳተፍ ለወላጆች/ለአሳዳ ጊዎች በተማሪው(ዋ) ሪፖርት ካርድ እና ParentVUE/StudentVUE ላይ ይገለጻል። ተማሪ በትምህርት ቀን 50 በመቶ ወይም ከዚያ በላይ ከተገኘ(ች) ተማሪው(ዋ) ለአንድ ሙሉ የትምህርት ቀን እንደተገኘ(ች) ይቆጠራል። ተማሪው/ዋ የተገኘው/ችው 10 በመቶ ወይም ከዚያ በላይ ቢገኝም፣ ነገር ግን ከትምህርት ቀናት 50 በመቶ ያነሰ ጊዜ ከሆነ ለግማሽ ቀን ብቻ እንደተገኘ(ች) ይቆጠራል።

በአካባቢ ት/ቤት አሰራር መሰረት፣ አንድ ተማሪ ከት/ቤት ከቀረ(ች) ት/ ቤቱ የመቅረቱ(ቷ)ን ምክንያት ይከታተላል።

በትምህርት ቤቶች መካከል በሚካሄድ አትሌቲክስ ውስጥ የሚሳተፉ ተማሪዎች ዝግጅቱ በሚካሄድበት ቀን ወይም በልምምድ ቀን ሁሉንም

የክፍል ትምህርት መርሃ ግብሮቻቸውን መከታተል አለባቸው። ተማሪ-አትሌቶች ከመቅረት ወይም ከመዘግየት ጋር ለተያያዙ ጥያቄዎች፣የበለጠ እርዳታ ለማግኘት አሰልጣኞቻቸውን ወይም የአትሌቲክስ ዳይሬክተሮቻቸውን ማነጋገር አለባቸው።

### ምክንያት/ፈቃድ ያላቸው መቅረቶች

የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት (MSDE) የሚከተሉትን ሁኔታዎች እንደ ህጋዊ መቅረት ይቆጥራል፦

- በትምህርት ቤት፣ MCPS ወይም MSDE የጸደቀ ወይም የተደገፈ ሥራ
- የቅርብ ዘመድ ከሞተ
- የተማሪ ሕመምና የደኅንነት ስጋቶች (በሽታው ሥር ከሰደደ ወይም በተራዘመ መቅረት ምክንያት ርእስ መምህሩ(ሯ) የሐኪም የምስክር ወረቀት እንዲያቀርቡ ወላጅን/አሳዳጊን መጠየቅ ይችላል።)
- ከእርግዝና እና ከወሊድ ጋር በተያያዙ ሁኔታዎች (በህመም ወይም በተማሪው(ዋ) ልጅ የህክምና ቀጠሮ ምክንያት መቅረት እና ቤተሰብ የህግ ጥሪ ጋር በተገናኘ ቀጠሮ ምክንያት መቅረትን ጨምሮ ጉዲፈቻ፣ ጥበቃ እና ጉብኝት ጭምር)። እነዚህ እናት እና አባት ለሆኑ ተማሪዎች የተሰጡ መብቶች ናቸው።
- የፍርድ ቤት መጥሪያ
- አደገኛ የአየር ሁኔታ (ተማሪው/ዋ ከቤት ወደ ት/ቤት ለመመላለስ የአየር ሁኔታ የሚያሰጋ ከሆነ)
- የዶክተር/የህክምና ቀጠሮዎች
- ኃይማኖታዊ በዓል ለማክበር
- ድንገተኛ ሁኔታ
- ከትምህርት ክፍል መታገድ
- የተፈቀደው መጓጓዣ ካልደረሰ (ለምሳሌ፦ የትምህርት ቤት አውቶቡስ ካልመጣ)
- ከርእሰ መምህሩ ፈቃድ ከተሰጠ

ተማሪዎች ከነዚህ ምክንያቶች በአንዱ ትምህርት ቤት ካልመጡ፣ ወደ ትምህርት ቤት ከተመለሱ በኋላ በሶስት የትምህርት ቀናት ውስጥ ከወላጅ/ከአሳዳጊ የቀሩበትን ምክንያት የሚገልፅ ማስታወሻ ይዘው መምጣት አለባቸው። ለምሳሌ፦ አንድ ተማሪ ረቡዕና ሃሙስ ከት/ቤት ቢቀር/ብትቀር እና ዓርብ ቢመለስ/ብትመለስ፣ ስለመቅረቱ/ቷ ምክንያት የሚያብራራ ማስታወሻ በሚቀጥለው ማክሰኞ ማቅረብ አለበ(ባ)ት። አለዚያ መቅረቱ ያልተፈቀደ ተብሎ ይመዘገባል። አንድ ት/ቤት "በት/ቤት እንከን የሌለበት መገኘት፣መከታተል፣መሳተፍ" ሽልማት ማዘጋጀት ቢፈልግ፣ ተማሪዎቹ የቀሩባቸው ቀናት በሀይማኖት ምክንያት የተፈቀዱ ቀናት ብቻ ከሆኑ ሽልማቱን ማስቀረት አይችልም።

ተማሪዎች 18 ዓመት እድሜ ወይም ከዚያ በላይ ወይም ያገቡ ከሆኑ፣ MCPS ቅጽ 281-12Eligible Student Declaration Form (የተማሪ ብቁነት ማረጋገጫ ቅጽ) ከሞሉ በኋላ የራሳቸውን ማስታወሻ መፃፍ ይችላሉ። እድሜው(ዋ) የሚፈቅድ ያለ ምክንያት/ያለፈቃድ የሚቀር (የምትቀር) ተማሪ ከወላጅ/አሳዳጊ ጋር በጥገኝነት የሚ(ምት)ኖር ከሆነ ለተማሪው/ዋ ሳይገለጽ ያለፈቃድ ከት/ቤት ስለመቅረቱ(ቷ) ለወላጅ/አሳዳጊ ተጨማሪ ማሳወቂያ ሊላክ ይችላል።

ወላጅ/ሞግዚት፣ (ብቁ ተማሪ) ቢያንስ ከአምስት የትምህርት ቀናት አስቀድሞ ፈቃድ ጠይቀው ከሆነ ርእስ መምህር ለሥራ ወይም ሌላ እንቅስቃሴ ለተማሪዎች መፍቀድ ይችላል/ትችላለች። ተማሪዎች ከሚከተሉት አንዳቸውን ለማከናወን ከት/ቤት ቢቀሩ ርእስ መምህሩ/ሯ ይቅርታ ያደርግላቸዋል/ታደርግላቸዋለች፦

- የኮሌጅ ግቢ ለመጎብኘት
- በኮሌጅ የመተዋወቅያ ፕሮግራም ለመሳተፍ
- ስራ ለመቀጠር ቃለ መጠይቅ ለማድረግ
- የጋራ ትምህርት ፕሮግራም አካል የሆነ ስራ ለመስራት
- የአጭር ጊዜ ወይም የሙሉ ጊዜ ስራ ለመሳተፍ

የቤተሰብ እረፍቶች በአብዛኛው አይፈቀዱም። ከተለመደው ውጭ ሁኔታዎች ከተፈጠሩ ግን፣ ርእሰ መምህሩ/ሯ መቅረቱን ይቅርታ ማድረግ ይችላል/ትችላለች።

እያንዳንዱ ት/ቤት በየቀኑ በት/ቤት መገኘት፣መከታተል፣መሳተፍ፣ በት/ቤት የተገኙበትን ቀናቶች ለመቆጣጠር፣ እና (የማስተካከያ) ርምጃዎችን የመውሰድ አሠራር ይዘረጋል።

### ፈቃድ የሌላቸው ቀሪዎች

እላይ በተገለጹት ሁኔታዎች መሰረት ያልተፈቀደ ቀሪ "ያልተፈቀደ ቀሪ" ነው። አንድ/ዷት ተማሪ አንድ የትምህርት ቀን ከቀረ(ች) እና ፈቃድ ከሌለው/ከሌላት፣ ተማሪው(ዋ) ባመለጠው/ባመለጣት በያንዳንዱ የትምህርት ክፍል ያለፈቃድ መቅረት ይመዘገብበ(ባ)ታል።

ያለፈቃድ በተቀረበት ቀን ርእሰመምህሩ/ሯ ተማሪው/ዋ ከትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎች ላይ እንዳይሳተፍ/እንዳትሳተፍ መከልከል ይችላል/ትችላለች።

አምስት ቀኖች ወይም ከዚያ በላይ ከት/ቤት ያለፈቃድ የቀሩ ተማሪዎች ት/ቤት ቀሪ መሆናቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ ይሰጣቸዋል። የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት፣ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት፣ እና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ከመጠን ያለፈ መቅረት እና/ወይም ዘግይተው መምጣት፣ምክንያት ኖሯቸው የተፈቀደላቸውም ቢሆን ወይም ያለምክንያት የሚቀሩ/የሚያረፍዱ ከሆነ ተገቢውን የትምህርት ማጠናከሪያ ጣልቃ ገብነት ፕሮግራም እንዲከታተሉ ሊደረጉ ይችላሉ። በርእሰመምህሩ(ሯ) ወይም በተወካይ ፈቃድ፣ ደጋግሞ የመቅረት አዝማሚያ ያሳዩ ተማሪዎች በት/ቤት በመደበኛነት መገኘት፣መከታተል፣መሳተፍ የሚችሉበትን ሁኔታ ለመጨመር የተቀረጹ ከበድ ያለ የማስተካከያ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ለማድረግ ወደ ተገቢው ሠራተኛ ወይም ከት/ቤት ውጭ ወደ ሚገኙ ሌሎች ኤጀንሲዎች ሊላኩ ይችላሉ።

የትምህርት ቤት ካውንስለር ከተማሪ እና ከወላጆች/ሞግዚቶች ጋር በመምከር ለመቅረት ምክንያት የሆኑ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ እንደ ትምህርት ቤቱ ልምድ እና MCPS ደንብ JEA-RA መሠረት ተገቢ የማስተካከያ ርምጃ መወሰን ያስፈልጋል የተማሪ ከትምህርት ቤት መቅረት።

### በቀሪነት ወቅት ያመለጡ ስራዎች

የቀሩበት ህጋዊ ይዘት የፈለገም ቢሆን ያመለጣቸውን ስራ ለማስተካከል መጣር ለተማሪዎች እጅጉን አስፈላጊ ነው። ተማሪዎች ከማናቸውም ክፍል ከቀሩ በኋላ ሲመለሱ መምህራን ተመጣጣኝ፣ ነገር ግን የተለየ ስራ ወይም ግምገማ መስጠት ይችላሉ። ላልተፈቀዱ ቀሪዎች፣ በርእሰ መምህርሩ/ሯ እና በአመራር ቡድኑ በፀደቀው አካሄድ/አሠራር መሰረት፣ መምህራን ላመለጡ/ላልተሰሩ ስራዎች ወይም ግምገማዎች ክሬዲት መንሳት ይችላሉ።

*ማጣቀሻዎች፦*
የቦርድ ፖሊሲ IKB፣ የቤት ስራ
MCPS ደንቦች IKA-RA, IOA-RA, IOE-RA, IQB-RA, JEA-RA, JGA-RB, and JGA-RC.
*ሜሪላንድ የተማሪ ሪከርድ አያያዝ መመርያ*
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የኮርስ መፅሄት (MCPS High School Course Bulletin)

## ■ የክፍል ሥራ

### ውጤት አሰጣጥና ሪፖርት አቀራረብ

የውጤት አሰጣጥና ሪፖርት አቀራረብ ልምምዶች ፍትሃዊ፣ ትርጉም ያላቸው፣ እና ለሁሉም ተማሪዎች ጥብቅ የአፈፃፀም መመዘኛ ደረጃዎችን የሚያሟሉ ይሆናሉ። በከሪኩለሙ ላይ እንደተገለጸው፣ የትምህርት ውጤቶች እንደየክፍል ደረጃ እና በየኮርሶቹ እንደሚጠበቀው ውጤት መጠን በጠቅላላ ዲስትሪክቱ ውስጥ ወጥ የሆነ ትርጉም ይኖራቸዋል። የቦርድ ፖሊሲ IKA ስለ ውጤት አሰጣጥና ሪፖርት ማድረግ እና MCPS ደንብ IKA-RA ስለ ውጤት አሰጣጥና ሪፖርት ማድረግይመልከቱ። ስለ ውጤት አሠጣጥ፣ ስለ ቤት ሥራ፣ ዳግም ማስተማር፣ እና እንደገና የመፈተን አሠራር ሂደቶች በየትምህርት ቤቶቹ በአንድ አይነት ይተገበራሉ። በትምህርት ቤት ደረጃ የሚካሄዱ አሠራሮች በርእሰመምህር አማካይነት፣ ከትምህርት ቤት አመራር ቡድን ጋር በትብብር ይተገበራሉ።

1ኛ እስከ 5ኛ ባሉት ክፍሎች፣ የውጤት አሰራር የሚወሰነው የክፍል ደረጃን የሚመጥን ወይም የኮርስ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ ይሆናል። መምህራን ተማሪዎች እውቀታቸውን፣ ምክንያታዊ አስተሳሰባቸውንና የፈጠራ ችሎታዎቻቸውን፣ እንዲሁም በቃል፣ በጽሁፍ፣ በአፈጻጸም እና በውጤቶች

የአካዴሚያዊ ስኬት ክህሎቶቻቸውን ማሳየት የሚችሉባቸውን በርካታና የተለያዩ እድሎች ለተማሪዎች በማቅረብ ግንዛቤአቸውን ይፈትሻሉ።

በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ የውጤት አሠጣጥ የሚያተኩረው የሚጠበቅባቸውን የኮርስ ማከናወን መሠረት በማድረግ ይሆናል።

የመሀከለኛ ደረጃ ት/ቤት እና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች እና ወላጆች/አሳዳጊዎች MCPS ደንብ IKA-RA፣ የትምህርት ውጤት አሰጣጥ እና ሪፖርት ማድረግፖሊሲ እንዲገመግሙ ይበረታታሉ።፣ በተለይ ማተኮር ያለባቸው—

- በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት የተዘጋጁ ወይም ለመመረቂያ አስፈላጊ የሆኑ ምዘናዎች ወይም ለተማሪ ውጤት አስተዋጽዖ ሊያደርጉ የሚችሉ (የኮርስ የመጨረሻ ግምገማዎችን ጭምር)።
- ቀነገደብ፣ የመጨረሻ ቀናት፣ እና ዘግይቶ የሚቀርብ ሥራ፣
- የቤት ሥራ ለተማሪ ውጤት እንዴት እንደሚረዳ፣
- የማርክ መስጫ ጊዜ ውጤቶች እና የሴሚስተር ውጤቶች ስሌት፡-
- ተማሪ ዜሮ የሚያገኝበት/የምታገኝበት "50 በመቶ/ፐርሰንት ደንብ" እና ሁኔታዎች፡-
- እንደገና ለመገምገም እድል ያላቸው ስራዎች እና ድጋሚ የመገምገም እድል የሌላቸው ሥራዎች፤
- አንድ ተማሪ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲት የሚያስገኝ ኮርስ ሙሉውን ወይም በከፊል እንደገና የሚወስድባቸው ሁኔታዎች፣ እና
- የአካዳሚክ ታማኝነት ማጉደል አንድምታ፣ ሆን ብሎ መልስ ሰርቆ መስጠት ወይም መቀበል፣ ያልተፈቀደ፣ ኢፍትሐዊ፣ ሐቀኝነት የጎደለው፣ ወይም በአካዳሚክ ሥራ ከሌሎች ተማሪዎች ማጭበርበር፣ ማስገደድ፣ ማታለል፣ መስረቅ፣ በመናገር፣ በምልክቶች መስጠት/ማስተላለፍ፣ መቅዳት/መኮረጅ፣ ወይም ሌላ ማንኛውንም ዘዴ በመጠቀም ማጭበርበር ማለት ነው።

ተማሪዎችና ወላጆች/አሳዳጊዎች በግምገማዎች ወይም በሌላ ውጤት/ማርክ የተሰጠበት ስራ ላይ የሚገኝ መረጃ እንዳያጋሩ ወይም እንዳያሳራጩ ክልክል መሆኑን መገንዘብ አለባቸው።

ለወላጆች/ለሞግዚቶች እና ለተማሪዎች ስለ ውጤት አሠጣጥ እና ሪፖርት አሰጣጥ የሚገልጽ ተጨማሪ መረጃ-ኢንፎርሜሽን በዚህ የ MCPS ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል www.montgomeryschoolsmd.org/info/grading፣ እና በትምህርት ቤቶች ዋና ጽ/ቤቶች ጭምር ይገኛል።

*ማጣቀሻዎች፡-*
*የቦርድ ፖሊሲ IKA እና MCPS ደንብ IKA-RA ይመልከቱ።*

### የላቀ ደረጃ (Honors)፣ ከፍተኛ ደረጃ(Advanced-level)፣ እና ለከፍተኛ ደረጃ ምደባ (AP) ኮርሶች

የትምህርት ቤት ርእሰ መምህራን የላቀ ደረጃ፣ ከፍተኛ-ደረጃ፣ እና / ወይም የ AP ኮርሶችን ለመውሰድና አዳጋች ነገሮችን ለመቀበል/ለመጋፈጥ ችሎታ፣ ተነሳሽነት፣ወይም እምቅ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች ሁሉ ኮርሶቹን የመውሰድ እድሉን ማግኘታቸዉን ማረጋገጥ አለባቸዉ። እያንዳንዱ ትምህርት ቤት በሚከተሉት መመዘኛዎች ጥልቅ ግምገማ ላይ ለሁሉም ተማሪዎች ጥብቅ እና ከፍተኛ ደረጃ ኮርስ እንዲከታተሉ የላቀ፣ ከፍተኛ ደረጃ እና/ወይም AP ኮርሶችን ኃላፊነት በተሞላበት መልኩ ይፋ የሆነ ምዝገባ ያደርጋል።

- ኮርሱን ለመውሰድ የቅድሚያ መስፈርቶች የዕውቀት ደረጃ (A፣ B፣ ወይም C ውጤቶች/ማርኮች)
- የወላጅ/ሞግዚት "የብቃት/ችሎታ/" የድጋፍ ሀሳቦች/ምስክርነት
- መደበኛ የፈተና ውጤቶች፣ እንደአግባቡ
- ከበድ ያሉ/ተፈታታኝ ስራዎችን ተቋቁሞ ለመፈፀም ፈቃደኛነት
- የተማሪ ፍላጎት ወይም ተነሳሽነት
- የመምህር/አማካሪ (የችሎታ/ብቃት) የድጋፍ ሀሳቦች/ምስክርነት
- የስራ ናሙናዎችና የመረጃ ሰነዶች

### በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት (ሚድል ስኩል) የተወሰዱ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርሶች።

2016–2017 የትምህርት ዘመን 6ኛ ክፍል ለገቡ ተማሪዎች፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኮርሶች የመጨረሻ ክፍል እና ክሬዲት በተሳካ ሁኔታ ያጠናቀቁት በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት በነበሩበት ወቅት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ትራንስክሪፕት ላይ ሪፖርት ተደርጓል እና የተማሪው(ዋ) ድምር GPA ስሌት ውስጥ ተካትቷል።

2016–2017 የትምህርት ዘመን 6ኛ ክፍል ለገቡ ተማሪዎች በመለስተኛ ደረጃ ት/ቤት እያሉ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርሶችን በተሳካ ሁኔታ ያጠናቀቁት የመጨረሻ ክፍል እና ክሬዲት በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ትራንስክሪፕት ላይ ሪፖርት ይደረጋል፣ ነገር ግን የተገኘው ውጤት የተማሪውን ድምር GPA ካላሻሻለ በስተቀር ወደ ድምር GPA ስሌት ውስጥ አይገባም። በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት እያለ(ች) የተወሰደ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኮርስ የተማሪው(ዋ)ን አማካይ ድምር ጨት GPA የሚያሻሽል ከሆነ በ MCPS በቀጥታ ይተገበራል። ወላጆች/አሳዳጊዎች በቀጥታ ስሌት ውስጥ እንዳይገባ ከፈለጉ የትምህርት ቤቱን ካውንስለር ማነጋገር ይችላሉ።

*ማጣቀሻዎች፡-*
*የቦርድ ፖሊሲ IKA፣ MCPS ደንብ IKA-RA፣ እና IKC-RA*
*የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የትምህርት ውጤት እና ሪፖርት ድረ-ገጽ*

## ■ የተማሪ መዝገቦች

ት/ቤቶች የሁሉንም ተማሪዎች መረጃዎችን/መዝገቦችን/ሪኮርዶችን ይይዛሉ። በተማሪ ፋይል ላይ MCPS ቅጾች በቅድሚያ የተጠራቀመ መሠረታዊ ሪኮርድ ይገኛል። ባንዳንድ ሁኔታዎች፣ ሚስጢራዊ ማህደር ሊፈጠር ይችላል። የት/ቤት ሰራተኞች ሚስጢራዊ ማህደር ሲፈጥሩ ወላጆችን/ሞግዚቶችን ማሳወቅ አለባቸው።

ከት/ቤት ሰራተኞች ጋር በሚካሄድ ስብሰባ ተማሪዎችና ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው የተከማቸ የተማሪ ሬኮርድ የማየት መብት አላቸው። ሲጠየቅ፣ የት/ቤት ሰራተኛ የተከማቸ የተማሪ ሬኮርድ ለተማሪዎችና ለወላጆች/አሳዳጊዎች ማብራራት ወይ መተርጎም ይችላል/ትችላለች።

የትምህርት አመቱ በተጀመረ 30 ቀናት ውስጥ፣ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) MCPS ቅጽ 281-13፣ ዓመታዊ የመረጃ ማስታወቂያ እና የተማሪ ግላዊ ጉዳይ፣ወይም MCPS ቅጽ 281-13ISC አመታዊ የመረጃ ማስታወቂያ እና የተማሪ ግላዊነት ለሁሉም MCPS ኢኖቬቲቭ ትምህርት ቤት ቤተሰቦች፣ መረጃ ተብለው የሚሰጡ የመረጃ ምንጮችን ይዘረዝራል። የቤት አድራሻዎችና የስልክ ቁጥሮች ሊገለፁ የሚችሉት ለወላጆች/አሳዳጊዎች ድርጅቶች፣ ለመምህራን፣ እና ለት/ቤት ተማሪዎች፤ ለሚሊታሪ ቅርንጫፍ፣ በት/ቤቱ ወይም በትምህርት ቦርድ ለተቀጠረ ሰው፣ ወይም ለሜሪላንድ የማህበረሰብ ኮሙኒቲ ኮሌጅ ብቻ ነው። ወላጆች/አሳዳጊዎች የተወሰነ ወይም ጭራሹንም የግል መረጃዎችን ለተወሰነ ጊዜ በይፋ እንዳይገለፅ መከልከል ይችላሉ፣ እናም፣ እንደማኛውም ሌላ የተማሪ ሬኮርድ፣ መረጃው በሚስጢር ይያዛል።

ተማሪዎች ሲጎለምሱ፣ ተማሪዎችና ወላጆች/አሳዳጊዎች የተማሪን መረጃ በሚመለከት ተመሳሳይ መብት አላቸው። ቢሆንም፣ የእድሜ ብቃት ያላቸው በወላጆቻቸው ጥገኝነት የሚኖሩ ተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች ያለ ተማሪው(ዋ) ፈቃድ የልጃቸውን መረጃ ለማግኘት ይችላሉ።

ወላጅ/ሞግዚት ወይም ብቃት ያለው/ያላት ተማሪ ከተማሪው(ዋ) ጋር የተገናኙ የትምህርት መረጃዎች ትክክል አይደሉም፣ ወይም ያሳስታል፣ ወይም የተማሪ የግል ህይወትን መብት ይጻረራል፣ ተብሎ ከታመነ፣ ወላጅ/ሞግዚት ወይም ብቃት ያለው(ያላት) ተማሪ፣ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ቅጽ-MCPS Form 270-8 በመጠቀም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሪኮርዱን እንዲያሻሽል ለመጠየቅ ይቻላል፣ ከህዝብ የሚቀርብ ቅሬታ/ስሞታ።

*ማጣቀሻዎች፡-*
MCPS ደንብ JOA-RA እና KLA-RA

## ■ Synergy ParentVUE/ StudentVUE

የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ወቅታዊ መርሃ ግብራቸውን፣ የቤት ሥራዎችን፣ የትምህርት ውጤቶችን፣ የተማሪ የአደጋ ጊዜ ግንኙነት መረጃ፣ የተመደበላቸውን ካውንስለር/አማካሪ፣ ሎከራቸውን፣ የተመደቡበት የአውቶቡስ ማቆሚያ መረጃ፣ እና ለአስተማሪዎች ኢሜይል ማድረግ ይችላሉ። በተጨማሪም የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ለሚቀጥለው ዓመት የሚጠይቁትን/የጠየቁትን ኮርሶች ማየት ይችላሉ፤ እንዲሁም የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የምረቃ ሁኔታቸውን ማየት ይችላሉ። ወላጆች/አሳዳጊዎች ParentVUE ሞባይል መተግበሪያን ወይም ድረ-ገጽ በመጠቀም PreentVUE ላይ ተመሳሳይ መረጃ ማግኘት ይችላሉ። በአብዛኛው ወላጆች/አሳዳጊዎች ወቅታዊ የአደጋ ጊዜ የግንኙነት መረጃዎችን ማስመዝገብ፣ ህጻናትን በየትምህርት ቤት አትሌቲክስ ማስመዝገብ፣ የትምህርት ቤት ምደባ ለውጥ (COSA) ጥያቄ ሊያቀርቡበት፣ ወይም አዲስ ተማሪዎችን ሊያስመዘግቡበት ይችላሉ። ለተጨማሪ መረጃ እባክዎን ለተማሪዎች የቴክኖሎጂ መረጃ እና ድጋፍ ድረ-ገጽ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/parents/tech-info-support/

## ■ ቴክኖሎጂ

### ኃላፊነት የተሞላበት የተማሪ መመርያዎች አጠቃቀም

MCPS ከተልእኮው ጋር የተዛለጡ የኮምፒውተር መሣርያዎችን፣ የኮምፒውተር አገልግሎቶችን፣ ከት/ቤቶች እና ከተማሪዎች ጋር መገናኛ የውሂብ/የኔትዎርክ አገልግሎት ይሰጣል። MCPS ተማሪዎች ክፍት የሆነው ስፋት ያለው በርካታ የመረጃ ቴክኖሎጂ አዳዲስ መልካም እድሎችን እና ስጋቶችን ያስተዋውቃል። ተማሪዎች ቴክኖሎጂን በሚገለገሉበት ጊዜ ተገቢ/መልካም የአጠቃቀም ስነ-ምግባር እንዲኖራቸው ማሳወቅ እና መሠረት ማስያዝ የት/ቤት ሠራተኞች እና የእያንዳንዱ ተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ የጋራ ኃላፊነት ነው። በት/ቤቶች፣ የተማሪዎች የድረ-ገጽ/ኦን ላይን መገናኛ መስመር አጠቃቀም እንቅስቃሴዎች በስርአት-አቀፍ ቴክኖሎጂ የመከላከል ጥበቃ እርምጃዎች በት/ቤት ሰራተኞች አማካይነት ቁጥጥር ይደረግባቸዋል። ተማሪዎች መረጃዎችን እና ግብዓቶችን ከስርቆት፣ ከተንኮል-አዘል ጉዳት፣ ያልተፈቀደ ተደራሽነት፣ ከማስተጓጎል እና ከኪሳራ መጠበቅ እና የቦርድ ፖሊሲዎችን፣ MCPS ደንቦችን እና ህጎችን እንዲሁም የአካባቢ፣ የስቴት እና የፌደራል ህጎችን ማክበር አለባቸው።

የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች በሙሉ MCPS ደንብ IGT-RA፣ ለኮምፒውተር ሲስተም አጠቃቀም፣ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ፣ እና የአውታረ መረብ ደህንነት የተጠያቂ ሀላፊነቶች እና MCPS ደንብ COG-RA፣ የግል ሞባይል መሳሪያዎች፣የሚከተሉትን ጨምሮ የተዘረዘሩትን ሂደቶች ለመከተል መስማማት ይጠበቅባቸዋል።

- ተማሪዎች MCPS ኔትወርክን ውጤታማ፣ ተገቢ እና ከት/ቤት ጋር ለተያያዙ ዓላማዎች ብቻ የሚጠቀሙ ሲሆን ከዲስትሪክቱ፣ ከተማሪው ወይም በተማሪው ቤተሰብ የተሰጠውን ማንኛውንም የቴክኖሎጂ ሪሶርስ የሌሎች ተማሪዎችን እና የሥራ ባልደረቦችን እንቅስቃሴ በሚያስተጓጉል መልኩ ከመጠቀም ይቆጠባሉ።
- ተማሪዎች ኢሜል እና ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎችን (ለምሳሌ:- X (Twitter, blogs, wikis, podcasting, chat, instant-messaging, discussion boards, social media, virtual learning environments) ቀደም ሲል ትዊተር በመባል የሚታወቀውን ኩባንያ፣ ብሎጎች፣ ዊኪስ፣ ፖድካስቲንግ፣ ውይይት፣ ፈጣን መልዕክት መላላኪያ፣ የውይይት ሰሌዳዎች፣ ማህበራዊ ሚዲያ፣ ቨርቹዋል የመማሪያ መድረኮች) የመሳሰሉትን ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ ህጎችን ሳይጥሱ፣ የተሰጡ መመሪያዎችን በማክበር መጠቀም አለባቸው።
- ተማሪዎች ሌሎች ሰዎች በሠሩት ስራ ሲገለገሉ ሌሎች ሰዎች ስላበረከቱት ሃሳቦች እና ለስራዎቻቸው እውቅና መስጠት አለባቸው።
- ተማሪዎች የግል መረጃዎቻቸውን (የቤት/የሞባይል ስልክ ቁጥር፣ የፖስታ አድራሻ፣ የተጠቃሚ ይለፍ ቃል ጭምር) እና ሌሎችን የግል መረጃ በምስጢር ይይዛሉ።
- ተማሪዎች ከአግባብ ውጭ የሆነ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ወድያውኑ ያስታውቃሉ።
- አግባብነት የሌለው አጠቃቀም ተለይቶ ካልታወቀ MCPS ኃላፊዎች የትኛው አይነት አጠቃቀም ከአግባብ ውጭ መሆኑን ለማወቅ/ለማረጋገጥ ደንብ እና መመሪያዎችን ለመጠቀም እንደሚችሉ ተማሪዎች ይረዳሉ።
- ሁሉም MCPS መሳርያዎች MCPS አውታረ መረብ፣ እና ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸው MCPS አውታረ መረብ አካውንት MCPS ንብረት መሆናቸውን እና ቁጥጥር እንደሚደረግባቸው፣ እንደሚከፈቱ፣ እና በአውታረ መረብ ፋይል እንደሚያዙ ተማሪዎች ይገነዘባሉ።
- ተማሪዎች (ህግን/መመሪያን) የሚተላለፍ/የማያከብር ድርጊት ቢፈጽሙ፣ ድርጊታቸው ኮምፒዩተር ከማግኘት መብት/ጥቅም መታገድን፣ የስነስርአት ርምጃ፣ እና/ወይም ወደ ህግ አስፈጻሚዎች መመራት የሚያጠቃልሉ እርምጃዎችን ሊያስከትል እንደሚችል ይረዳሉ።

### የግል ሞባይል መገልገያዎች

ሞባይል ስልኮች፣ ኢ-ሪደርስ/e-readers፣ ታብሌቶች፣ የግል ኮምፒዩተሮች፣ ወይም ሌሎች የድምፅ ማጉያ/ማይክሮፎን ያላቸው መሣሪያዎች፣ ስፒከሮች እና/ወይም ካሜራዎች፣ እና ሌሎች ተመሳሳይ ከሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ያልተሰጡ መሳሪያዎች፣ የግል ሞባይል መሳሪያዎች (PMDs) ምሳሌዎች ሲሆኑ MCPS ደንብ COG-RA የግል ሞባይል መሳሪያዎች እና MCPS ደንብ IGT-RA፣ የኮምፒውተር ሲስተሞች፣ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ እና የአውታረ መረብ ደህንነትድንጋጌዎችን ማክበር ይጠበቅባቸዋል። ለሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ዓላማዎች PMDs ሦስት የተለዩ ባህሪያት አሏቸው:-

- የመሳሪያው ባለቤትነት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ያልሆነ ወይም ከ (MCPS) ያልተሰጠ ነው።
- መሣሪያው መረጃ ለመላክ እና ለመቀበል የበይነመረብ፣ ዋይ-ፋይ/wi-fi፣ ወይም የተንቀሳቃሽ ስልክ/cellular ግንኙነት ማድረግ የሚቻልበት ነው።
- መሣሪያው ድምጽን፣ ምስሎችን/ቪዲዮ ለመቅረጽ የሚያስችል ነው።

ከትምህርት ቤት በፊት እና በኋላ፣ በሁሉም የክፍል ደረጃዎች የሚገኙ ተማሪዎች የግል ተንቀሳቃሽ/ሞባይል መሳሪያቸውን መጠቀም የሚችሉት የትምህርት ቤት ሠዓት ከመጀመሩ በፊት እና የትምህርት ቤት ሠአት ከተጠናቀቀ በኋላ ነው።

አንደኛ ደረጃ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች: በትምህርት ቀን — በክፍል ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ፣ በምሳ ሠዓት እና ወደ መማሪያ ክፍሎች በሚሸጋገሩበት ጊዜ ጭምር — ተማሪዎች የግል ተንቀሳቃሽ/ሞባይል መሳሪያዎቻቸውን ድምፅ አጥፍተው ማስቀመጥ አለባቸው።

የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች: የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የግል ሞባይል መሳሪያቸውን በምሳ ሠዓት እና የክፍል ትምህርት እስኪጀመር ሊጠቀሙ ይችላሉ፤ ነገር ግን ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ ለመጠቀም አይፈቀድላቸውም።

በትምህርት ቤት አውቶቡሶች ውስጥ:- ተማሪዎች በሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ባለቤትነት የሚንቀሳቀሱ ወይም የተቀጠሩ ተሽከርካሪዎች ላይ በሚጓዙበት ወቅት መሳሪያዎቻቸውን እንዲጠቀሙ ይፈቀድላቸዋል፣ ነገር ግን ይህ አጠቃቀም የአውቶቡሱን ደህንነቱ የተጠበቀ አሰራር የማያደናቅፍ እና ሌሎች ተዛማጅ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ህጎችን በማክበር መሆን አለበት።

የተማሪ ኃላፊነት:- ተማሪዎች መሳሪያዎቻቸውን በሃላፊነት እንዲጠቀሙ ይጠበቅባቸዋል፣ መጠቀም በተከለከለ ሠዓት ድምጾቻቸውን አጥፍተው አርቀው ማስቀመጥ ይጠበቅባቸዋል።

ተግሣጽ/ዲስፕሊን እና የሚጠበቁ ነገሮች:- ተማሪ PMD አላግባብ ከተጠቀመ(ች)፣ የሚያስከትለው መዘዝ MCPS በተሻሻለው የተማሪ የስነምግባር ደንብ ላይ የተገለፀውን እርምጃ የመውሰድ መዘዝ ያስከትላል። አጠቃቀሙ መመሪያን የሚደግፍ ከሆነ ርእሰ መምህራን በትምህርት ጊዜ ውስጥ የሞባይል ስልክ አጠቃቀምን የመፍቀድ ስልጣን አላቸው።

የሕክምና እና የመማሪያ አኮሞዴሽኖች:- ተማሪዎች PMD ለመጠቀም በሚፈቅደው 504 ዕቅድ ወይም በግለሰባዊ የትምህርት እቅድ (IEP) ላይ እንደተመዘገበው የመጠቀም እድል ይኖራቸዋል።

የሌሎችን ግላዊነት የሚጥስ መረጃ፣ የተማሪዎችን ጤና እና ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል መረጃ፣ ጸያፍ ወይም ስድብ ካለበት፣ የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎችን የሚያሰናክል/የሚረብሽ ከሆነ፣ የአካዳሚክ ታማኝነት የጎደለው ድርጊት ከሆነ፣ ወይም የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የኮምፒዩተር ሲስተምን የሚያበላሽ ከሆነ፣ ተዛማጅ ቴክኖሎጂ ወይም የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ደህንነትን የሚጥስ ከሆነ ወይም (የትምህርት ውጤቶችን ወይም ሌላ የተማሪ መረጃን ጭምር) PMD በመጠቀም ማስተላለፍ አይቻልም። MCPS ውስጥ የሳይበር ጥቃት በጣም የተከለከለ ነው፣ ከሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ርቆ በሚገኝ ሥፍራ የሚፈፀም የስነምግባር ጥሰትን ጨምሮ የዲሲፕሊን እርምጃ ሊያስወስድ ይችላል። ከትምህርት ቤት መቼት ጋር ግንኙነት ሲፈጠር፣ ምግባሩ ትምህርት ቤት እያሉ ሌሎች ተማሪዎች ላይ የመጉዳት አደጋን የሚፈጥር ከሆነ፣ ወይም ምግባሩ በትምህርት ሥራ ላይ ጣልቃ የሚገባ ከሆነ የዲስፕሊን እርምጃ ይወሰዳል። የግል ተንቀሳቃሽ መገልገያዎቹ (PMDs) የMCPS ደንቦችን ባልተከተለ መንገድ ጥቅም ላይ ከዋለ በት/ቤት ባላሥልጣናት ሊነጠቁ/ሊወረሱ ይችላሉ።

በግል ተንቀሳቃሽ የመገልገያ እቃዎች መጥፋት፣ በእቃዎቹ ላይ የስርቆት ወንጀል መፈጸም፣ ወይም ብልሽት መድረስ ወይም እነዚህን የመሰሉ ማናቸውም መሣሪያዎች ባልተፈቀደ ሁኔታ ለመጠቀም MCPS ኃላፊነት ወይም ተጠያቂነት አይወስድም።

MCPS የተማሪዎችን ጎጂ የኢንተርኔት ድረ-ገጾችን አጠቃቀም ለመገደብና ለማጣራት ሌሎች የቴክኖሎጂ እርምጃዎችን ይጠቀማል። በግላዊ ተንቀሳቃሽ አውታረ መረብ መጠቀሚያ አማካይነት መክፈት ተመሳሳይ የማጣራት ሂደት አይኖረውም፤ ስለዚህ ተማሪዎች MCPS ንብረት ውስጥ እስካሉ ድረስ፣ ኢንተርኔት ለመክፈት MCPS አውታረ መረብ (ለምሳሌ፦ የግል ሞባይል አውታረ መረቦች ሳይሆን) መጠቀም አለባቸው። አንድ ተማሪ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ይዞታ ላይ ኢንተርኔት ለመጠቀም MCPS አውታረመረብ ላይ ሳይሆን PMD ለመክፈትና ለመጠቀም ተማሪው(ዋ) የዚህን ደንብ መስፈርቶች የማክበር ግዴታ አለበ(ባ)ት።

*ማጣቀሻዎች፦*

MCPS ደንብ COG-RA፣ IGT-RA፣ ILA-RA፣ JHF-RA,

MCPS የተማሪ ስነምግባር ደንብ (

MCPS የማህበራዊ መገናኛዎች/Social Media ለሠራተኞች እጅግ ጠቃሚ ምክሮች/ልምምዶች

MCPS የሠራተኛ ስነምግባር ደንብ

የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አመታዊ የተማሪ መመሪያ እና መረጃ

ስለ ግላዊ ህይወት ጉዳይ

ስለ ኢሜል እና ለሌሎች ዲጂታል ግንኙነቶች የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ምርጥ ተሞክሮዎች

## የተማሪ የአገልግሎት ትምህርት (SSL)

ለሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ የሚሠሩ ተማሪዎች በሙሉ ከምዝገባ፣ ከክሬዲት፣ ከኮርሶች፣ እና ሌሎች የመመረቂያ ብቁነት መስፈርቶች በተጨማሪ የአገልግሎት ትምህርት ሰዓቶችን ማሟላት/ማጠናቀቅ አለባቸው። 5ኛ ክፍል ከጨረሱ በኋላ የአገልግሎት ትምህርት ሰአቶችን ከቀጣዩ ሰመር ጀምሮ ለማጠራቀም ይችላሉ።

ተማሪዎች ከመመረቃቸው በፊት 75 የአገልግሎት ትምህርት ሰአት ማጠናቀቅ አለባቸው፣ በዝውውር ለሚገቡ ተማሪዎች የተወሰኑ ልዩ ሁኔታዎች ይኖራሉ። MCPS የተማሪ አገልግሎት ትምህርት ፕሮግራም ዝርዝሮች በዚህ አውታረ መረብ ላይ www.mcps-ssl.orgወይም በማንኛውም የመካከለኛ ወይም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ SSL አስተባባሪውን በማነጋገር ሊያገኙ ይችላሉ።

የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች እና ወላጆች/አሳዳጊዎች የተማሪን የተጠራቀመ SSL ሰአት ParentVue/StudentVue ላይ መመልከት ይችላሉ።

*ማመሳከሪያ/ማጣቀሻ፦*

COMAR 13A.03.02.05 የተማሪ አገልግሎት

Director, Student Leadership and Extracurricular Activities: 240-740-3977 ወይም SSL@mcpsmd.org

## MCPS ኤክስትራከሪኩለር (ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሚከናወን እንቅስቃሴ) የተማሪ ድርጅቶች እና ቡድኖች

ተማሪዎች ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የተማሪ ድርጅቶችን እና ቡድኖችን የመፍጠር እና የመሳተፍ መብት አላቸው። ተማሪዎች የመሳተፍ ችሎታቸውን የሚመለከቱ ተገቢ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ህጎችን የማወቅ ሃላፊነት አለባቸው። ተማሪዎች በክለቦች፣ በቡድኖች፣ ወይም የተማሪ ድርጅቶች ላይ በመሪነት ደረጃ ለመስራት ለመመረጥ ወይም ምደባ የሚፈልጉ ተማሪዎች ጥሩ ስነ-ምግባር፣ ሕግ አክባሪነትን፣ ለሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶችን ህጎች መታዘዝን ጨምሮ MCPS ቅጥር ግቢ ውስጥም ይሁን ወይም በውጭ መልካም ጠባይ ማሳየት እና ምሳሌ መሆን ይጠበቅባቸዋል። አከራካሪ እና ውስብስብ ማህበራዊ እና ህጋዊ ጉዳዮች ላይ ውይይት በማድረጋቸው ምክንያት ብቻ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችን ቡድን ከመፍጠር ሊያግዱ አይችሉም።

### ኤክስትራከሪኩለር

ከመደበኛ ትምህርት ተጓዳኝ እንቅስቃሴ (ECA) ማለት በተማሪዎች ፍላጎት ዙሪያ የተደራጀ እና MCPS ውስጥ ለተመዘገቡ ተማሪዎች ክፍት የሆነ በፈቃደኝነት እና በተማሪዎች የሚመሩ እንቅስቃሴዎች ናቸው። ECA የሚለየው ከሥርዓተ-ትምህርት (co-curricular) ተግባር ይህም ማለት ከክፍል ትምህርት ውጭ ውጤት የሚሰጥበት ኮርስ፣ በክፍል ውስጥ ከሚሰጥ ትምህርት ወይም ከትምህርት ቀን በተለይ የሚሰጥ (ኮርስ) ወይም እንቅስቃሴዎች ላይ ሁሉም በክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች መስፈርቶችን ለማሟላት መሳተፍ አለባቸው።

### በት/ቤት የተደገፋ/ስፖንሰር የተደረጉ ድርጅቶች

እንደ ትምህርት ቤት ተግባር በርዕሰ መምህር/ተወካይ (ለምሳሌ፦ ECA ዳይሬክተር) ስፖንሰር የተደረጉ በት/ቤት የሚደገፉ ECAs ፈቃድ አላቸው። ትርጉሙ፣ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የሚደገፍ ECA የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተቀጣሪ የሆነ(ች) ሰራተኛ ለተማሪዎች ቁጥጥር ኃላፊነት ያለው/ያላት ስፖንሰር ሊኖረው ይገባል።

### ት/ቤት ስፖንሰር የማያደርጋቸው የተማሪ ድርጅቶች

በትምህርት ቤት ስፖንሰር ያልተደረጉ እና በተማሪዎች ተነሳሽነት የሚንቀሳቀሱ ክለቦች/ክበቦች በትምህርት ቤት እንደሚደገፍ ድርጅት ሊወከሉ ወይም ሊታሰቡ አይችሉም። የሚከተሉትን ሀላፊነቶች እስካከበሩ/እስካሟሉ ድረስ ተማሪዎች ትምህርት በማይሰጥበት ጊዜ ስብሰባ የማካሄድ መብት አላቸው።

- ስብሰባው የደህንነት ወይም የፀጥታ አደጋ ስጋት አያስከትልም።
- ስብሰባዎቹ በፈቃደኝነትና በተማሪዎች ተነሳሽነት የተዘጋጁና በት/ቤት ያልተወከሉ ወይም በት/ቤት የተደገፉ ተደርገው የማይወሰዱ ናቸው።
- የትምህርት ቤት ሰራተኞች ስብሰባዎችን አይመሩም ወይም አያበረታቱም፣ ሆኖም ግን የደህንነት ጥበቃ ክትትል ማድረግ ይችላሉ።
- የት/ቤት ተቀጣሪዎች/ሰራተኞች ስብሰባዎቹን አይመሩም ወይም አይሳተፉም፣ የሃይማኖት ስብሰባዎችንም ጨምሮ።
- ስብሰባው በት/ቤቱ ውስጥ በስርዓት ከሚመራዉ የትምህርት እንቅስቃሴዎች አፈፃጸም ጋር በማንኛውም ሁኔታ ከፍተኛ ጣልቃ የመግባት/የማደናቀፍ ሁኔታ ይኖረዋል ተብሎ አይታሰብም።
- ከትምህርት ቤት ያልሆኑ ሰዎች በስብሰባዎች ላይ አይመሩም ወይም አዘውትረው አይገኙም።
- የህዝብ ገንዘብ ለስብሰባ ወጪ አይውልም (የመሰብሰቢያ ቦታ ለማዘጋጀት ከሚወጣው ወጪ በስተቀር)።

### ቡድኖች

MCPS የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) እና የሜሪላንድ ፐብሊክ ስኩልስ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የአትሌቲክስ ማህበር የብቃት መስፈርቶችን ለሚያሟሉ ተማሪዎች ሁሉ ክፍት የሆነ ሁለንተናዊ የአትሌቲክስ ፕሮግራም ይኖረዋል። በትምህርት ቤቶች መካከል በሚካሄድ አትሌቲክስ ውስጥ የሚሳተፉ ተማሪዎች MCPS የአትሌቲክስ ድረ-ገጽ ላይ ያለውን

ጠቃሚ መረጃ ማንበብ አለባቸው። በኦንላይን የምዝገባ ሂደት፣ ወላጆች እና ተማሪዎች ይህንን መረጃ መመልከታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው። www.montgomeryschoolsmd.org/departments/athletics/

*ማጣቀሻዎች፡-*

የቦርድ ፖሊሲ IQB፣ እና MCPS ደንብ IQB-RA፣ IQD-RA፣ IQD-RB፣ እና JFA-RA።

የተማሪ አመራር እንቅስቃሴ ዳይሬክተር 240-740-3977

## ■ ደህንነት እና የድንገተኛ አደጋ ማኔጅመንት

አወንታዊ የመማርያ አካባቢ እንዲሰፍን/እንዲኖር ለማድረግ የተማሪዎችና የሰራተኞች ደህንነት ወሳኝ ነው። የዲስትሪክት ስምምነቶችን/ፕሮቶኮሎችን፣ ልምዶችን፣ እና ተዛማጅ መሠረተልማት በጥብቅ አስፈላጊ የሆነውን ለሁሉም ተማሪዎች ሠላማዊ የሆነ የትምህርት አካባቢን መጠበቅን የሞንት ጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ገምግሟል።

ለሁሉም ትምህርት ቤቶች ሰባት ቅድሚያ የሚሰጣቸው መስኮች፡-

1. ከመረጃ የመነጨ ኃላፊነት/ተጠያቂነት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በጠቅላላ ስለ ት/ቤት ሠላምና ደህንነት እና አዎንታዊ የት/ቤት ባህል የትምህርት ምህዳሩ/ስርዓቱ ተቀዳሚ ትኩረት ይሆናል።
2. የት/ቤት ደህንነት ጥበቃ ሠራተኞች እና የሌሎች ሠራተኞች ውጤታማ ምደባ፣ አጠቃቀም፣ እና ማኔጅመንት።
3. የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማቶች፣ የደህንነት ካሜራዎች እና አጠቃቀማቸውን ጨምሮ።
4. ይበልጥ የተገለሉ/ለብቻቸው የተለዩ ህንፃዎችንና የት/ቤት መጫወቻ ሜዳዎችን የመዳረስ ሁኔታ መገደብ ወይም መግቢያ ላይ ጥብቅ በማድረግ መገልገያዎችን ማሻሻል።
5. በትምህርት ቀናት በሙሉ መልካም የተማሪ ስነምግባርን የመደገፍ ሥርዓትና አፈጻጸሞች፡፡
6. ሥርአት አቀፍ የመከላከል እና ቅድሚያ ጣልቃ ገብ ፕሮግራሞች፡፡
7. ከህግ አስከባሪዎች እና ሌሎችም አጋር ኤጀንሲዎች ጋር በትብብር መስራት።

የት/ቤቶቻችን ደህንነትና ፀጥታ ሁሉንም ሰው የሚመለከት ጉዳይ ነው። MCPS ለት/ቤት ደህንነት፣ ለእቅድ እና ስልጠና ለአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ቀልጣፋ አቀራረብ ቅድመ ዝግጅት ያደርጋል። አስቸኳይ ሁኔታ ፈጣን ምላሽ የሚጠይቅ መተንበይ የማይቻል፣ ዕቅድ ያልተደረገ ሁኔታ ነው። ድንገተኛ አደጋ ማለት፡- የእሳት አደጋ፣ ከባድ የአየር ሁኔታ ጋር የተያያዙ አደጋዎች፣ ሌሎች ድንገተኛ አደጋዎች፣ አደገኛ ቁሳቁሶች፣ የቦምብ ማስፈራሪያ ወይም የወንጀል ድርጊቶችን ሊያካትቱ ይችላሉ፥ ነገር ግን በዚህ ብቻ የተወሰነ አይሆንም። በሜሪላንድ ስቴት የትም ህርት ዲፓርትመንት (MSDE) ድንጋጌ መሠረት፣ MCPS ካሉበት ቦታ ለቆ የመውጣት ሂደቶችን፤ ደህንነቱ በሚያስተማምን ቦታ ላይ መቆየት እና መግቢያ/መውጫ በሮችን የመዝጋት ሁኔታን፣ ለቀው ከወጡበት የመመለስ ትግበራን፣ በሮችና መስኮቶችን መዝጋትና መቆለፍ፤ በወለል ላይ መተኛት፣ እንዳይታዩ ተሸፋፍኖ መቆየት፣ እና ለከባድ የአየር ሁኔታ ተገቢውን ምላሽ የመስጠት ዝግጅት እና ፕሮቶኮሎች አሉት። እነዚህ ሂደቶች የእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የአስቸኳይ ዝግጁነት ዕቅድ አካል ናቸው።

ማንኛውም ድንገተኛ ሁኔታ፣ እሳት፣ ከአየር ሁኔታ ጋር የተዛመደ ክስተት፣ ወይም የወንጀል ተግባር፣ ተማሪዎቻችንን እና ሰራተኞቻችንን ሊያጨናንቅ እንደሚችል MCPS ይረዳል። ስለዚህ MCPS የብሔራዊ ምርጥ ተሞክ ሮዎችን እና የአዕምሮ ጤና ባለሞያዎችን ምክር በመውሰድ ልምምዶችን በማካሄድ ከስቴቱ የተሰጠውን መመሪያ ያከብራል። ተማሪዎች፣ የአስተ ዳደር አባላት፣ እና ወላጆች/ሞግዚቶች የእነዚህ ቅደም ተከተሎች ግንዛቤ እንዲኖራቸው ወሳኝ ነው።

"Lockdown" MCPS ተቋም ውስጥ ለአደጋ ጊዜ አንድ ዓይነት ምላሽ ለመስጠት የሚያገለግል ቃል ነው። "Lockdown" መመሪያ የሚሰጠው በህንፃው ውስጥም ሆነ ከቤት ውጭ አደጋ መኖሩን እና ወደ አስቸኳይ የመሸሸግያ ሁኔታ በፍጥነት መንቀሳቀስ እንደሚያስፈልግ ሠራተኞችን ያስጠነቅቃል። ሁሉም ተማሪዎች የጎልማሳ/አዋቂ ሰው ክትትል እንዲደረግ ላቸው ይጠይቃል። ተማሪዎች እና ሰራተኞች በፍጥነት ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ መንቀሳቀስ፣ ዝም ማለት እና የሰራተኞችን መመሪያዎች መከተል አለባቸው። በተጨማሪም፣ MCPS ከሞንትጎመሪ ካውንቲ የፖሊስ ዲፓርትመንት ጋር፣ እና ከብሄራዊ የትምህርት ቤት ሳይኮሎጂስቶች ማህበር (NASP) ጋር በመተባበር ሰራተኞችን እና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪ ዎችን ወሳኝ የህይወት አድን ደህንነት ጥበቃ ሁኔታን ለማከናወን የሚያስ ፈልጉ ክህሎቶችን ለማስተማር እና ጥቃት ለማድረስ የተዘጋጀ አጥፊ ሲኖር ምላሽ የመስጠት አማራጮችን ለመረዳት ስልጠና በመስጠት በትብብር ይሰራል።

ከስፍራው ማስለቀቅ/ማስወጣት (Evacuate) በት/ቤት ውስጥ የሚደርስን አስቸኳይ ሁኔታ ለመግለፅ ስራ ላይ የሚውል ቃል ነው። የእሳት አደጋ ማስጠንቀቂያ ደወል በመደወል ወይም ከትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች በሚነገር ማስታወቂያ በመጠቀም ሁሉም ተማሪዎች እና ሰራተኞች ከህንጻው ለቀው እንዲወጡ እና ከእሳት አደጋ እንዲያመልጡ ይደረጋል።

መጠለያ ተማሪዎች እና ሰራተኞች በአካባቢያዊ የአየር ሁኔታ አደጋ ምክንያት በህንፃ ውስጥ መጠለል እንዳለባቸው ለማስጠንቀቅ የሚጠቅም ቃል ነው። ይህ የሚከሰተው ከባድ የአየር ሁኔታ ሲከተ ወይም በአቅራቢያ አደገኛ ቁሳቁሶች በሚገኙበት ጊዜ ነው።

በተጠንቀቅ ባሉበት መቆየት ተማሪዎች እና ሰራተኞች በህንፃ ውስጥ ወይም በአቅራቢያው አደገኛ ክስተት ያለ መሆኑን ለማስጠንቀቅ የሚያገለግል ቃል ሲሆን የሁሉንም ሰው ደህንነት ለመጠበቅ ተማሪዎች እና ሰራተኞች ሁሉም ባሉበት መቆየት አለባቸው። ትምህርት ሊቀጥል ይችላል፤ ነገርግን ሁሉም በያሉበት መቆየት አለባቸው።

ከውስጥ አስተማማኝ ቦታ ላይ መቆየት ለተማሪዎችን እና ለሰራተኞች እንዲሁም ለማህበረሰቡ አደገኛ ሁኔታ የተከሰተ መሆኑን ለማስጠንቀቅ የሚጠቅም ቃል ሲሆን የሁሉንም ሰው ደህንነት ለመጠበቅ ተማሪዎች እና ሰራተኞች ወደ ህንፃው ውስጥ እንዲገቡ እና ሁሉም የውጪ በሮች እንዲ ቆለፉ ይደረጋል። ትምህርት ሊቀጥል ይችላል፤ ነገር ግን ሁሉም ሰዎች ደህንነቱ በተጠበቀ ህንፃ ውስጥ በተጠንቀቅ ይቆያሉ።

MCPS የድንገተኛ አደጋ ምላሽ ፕሮቶኮሎችን ለመገምገም እና ለማሻሻል MSDE፣ ከሜሪላንድ የት/ቤት ደህንነት ጥበቃ ማዕከል፣ ከአከባቢ የህግ አስከባሪ አጋር ኤጀንሲዎች እና NASP ጋር በትብብር መስራቱን ይቀጥላል።

ተማሪዎች በአስጊ ሁኔታ የዛቻና ማስፈራራት ባህርይን እንዲገነዘቡ እና የዛቻና ማስፈራራት ባህርይን-ድርጊትን ሪፖርት የማድረግ መመሪያ ይሰጣ ቸዋል፣ እንዲሁም ማናቸውንም በሌላው ሰው ላይ ጉዳት የማድረስ፣ የግንኙነ ቶችን ሁኔታ፣ ወይም ማስፈራራትና ዛቻን የሚያደፋፍሩና የሚያባብሱ ሁኔታ ዎችን ወይም ማንኛውም ግለሰብ በሆነ ሰው ላይ ዒላማ አድርጎ ጥቃት የማድ ረስና የረብሻ ዝንባሌን ተማሪዎች በፍጥነት ለርእሰመምህር/ለተወካይ ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

በሜሪላንድ ህግ መሠረት፣ ዛቻ-ማስፈራራት ማለት አካላዊ ጉዳት የማድረስ ዝንባሌ ነው። የማስፈራራት ወይም የዛቻ መገለጫው በባህርይ፣ በቃል፣ በአይን-ግልምጫ፣ በጽሑፍ፣ በኤሌክትሮኒክስ፣ ወይም በማናቸውም ሌላ ዘይቤ ሊገለጽ የሚችል ሲሆን፣ የተቃጣበ(ባ)ት ሰው በቀጥታም ይሁን በተዘ ዋዋሪ እንዲያውቀው-እንድታውቀው ወይም የተቃጣበ(ባ)ት ሰው ቢያውቅም/ ባያውቅም በሌላ ሦስተኛ ወገን አማካይነት መልእክት ይተላለፋል። ዛቻና ማስፈራራት በቀጥታ ሊሆን ይችላል (ለምሳሌ፡- እመታሃ(ሻ)ለሁ "I am going to beat you up.") ወይም በተዘዋዋሪ (ለምሣሌ፡- አገኘዋለሁ-አገኛታለሁ "I'm going to get him.").

ተማሪዎችን፣ ሠራተኞችን፣ እና ወላጆችን/አሳዳጊዎችን ስለ ደህንነት እና የደህንነት ስጋቶችን ለማሳወቅ ስም-አልባ በሆነ መንገድ ለማቅረብ በሚደ ረገው ጥረት፣ MCPS በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ ውስጥ ከሜሪ ላንድ የትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ ማዕከል ጋር በመተባበር አደጋን ለመጠቆም እና ሪፖርት ለማድረግ- "Safe Schools Maryland" የተሰኘ አሠራር ይጠቀማል። ይህ ተማሪዎች፣ ወላጆች፣ ሞግዚቶች፣ እና የማህበ ረሰብ አባላት በሜሪላንድ ውስጥ በየትኛውም ቦታ ለደህንነት ስጋት የሚሆኑ ነገሮችን በቀላሉ በሚስጥር ሪፖርት ለማድረግ የሚያስችላቸዉ ይፋ የማይ ደረግ ጥቆማ ማቅረቢያ ነው። የተቀበሉት ምክሮች ለአካባቢያዊ እና ለክልል ትምህርት፣ ለሕዝብ ደህንነት፣ ለጤና ጥበቃ ባለሥልጣናት እና/ወይም ለማህበራዊ አገልግሎቶች ድጋፍ ሠራተኛ ለክትትል በተገቢው መንገድ ይተላለፋሉ።

እንደ ---- የመሳሰሉ ስጋቶችን ለማጋራት ግለሰቦች ይህንን ድረ-ገጽ፣ ስልክ፣ እና መተግበሪያ መሚሪያን መጠቀም ይችላሉ—

- የአእምሮ ጤንነት ችግሮች፣
- ጉልበተኝነት፣
- በትምህርት ቤት እና በማህበረሰብ ውስጥ የሚፈጠር ሁከት፣
- አደንዛዥ ዕፅ ማዘዋወር፣
- በደል፣ እና
- ጥቃት/ትንኮሳ

ያስታውሱ፣ የትምህርት ቤቶቻችን እና የመገልገያ ፋሲሊቲዎቻችን ሠላም እና ደህንነት የሁሉንም ሰው ትኩረት የሚስብ ጉዳይ ነው። በሜሪላንድ ህግ ድንጋጌ መሠረት አንድ ሰው ለአካለ መጠን ያልደረሰ(ች) ልጅ መሳሪያው ያለበትን ቦታ መድረስ እንደሚችል/እንደምትችል እያወቀ(ች) ወይም ማወቅ ሲገባው(ት) በቸልተኝነት ተተኳሽ ጥይት የጎረሰ መሳሪያን ያለቁጥጥር ማስቀመጥ ወይም መተው እንደማይችል በግልጽ ተቀምጧል። የት/ቤቶቻችንን ሠላምና ደህንነት የሚያደፈርሱ ማናቸውም ስጋቶች ኃላፊነት ላለው አዋቂ ሰው ወይም ለሜሪላንድ ደህንነታቸው የተጠበቀ ትምህርት ቤቶች ክፍት የስልክ መስመር በጊዜ ሪፖርት መደረግ አለባቸው።

ስለ ት/ቤቶች ሠላም የሜሪላንድ ክፍት-ቀጥታ መስመር:- 833-632-7233 (833-MD-B-SAFE)

በቀን 24 ሰአት በሳምንት 7 ቀናት ሰራተኛ የተመደበባቸው ተጨማሪ የአስቸኳይ ጥሪ መስመሮች

የሞንጎሞሪ ካውንቲ ፖሊስ —

አስቸኳይ ሁኔታ ያልሆነ፡- 301-279-8000

ስለ እፅ መጠቀሚያ የአስቸኳይ ጥሪ መስመር 240-773-DRUG (3784)

ስለ ወሮበላ/ጋንግ መጠቀሚያ የአስቸኳይ ጥሪ መስመር፡- 240-773-GANG (4264)

ስለ አደንዛዥ እፆችና ስለ ወንበዴ (ጋንግ) ጥቆማ 240-773-TIPS (8477)

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና ጥበቃና ሰብአዊ አገልግሎቶች የመረጃ መስመር (ከሰኞ እስከ አርብ 8:30 a.m.–5:00 p.m.) 240-777-0311, TTY 240-251-4850

MCPS የደህንነት እና የድንገተኛ አደጋ አስተዳደር ክፍል፡- 240-740-3066

www.montgomeryschoolsmd.org/departments/security/

ማጣቀሻዎች፡-
የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ COA
MCPS ደንብ COA-RA
"MCPS ደንብ EKA-RA"

## ■ መጓጓዣ/ትራንስፖርት

MCPS ከተማሪዎች፣ ወላጆች/ሞግዚቶች፣ የትምህርት ቤት ባልደረቦች፣ እና የትራንስፖርቴሽን ዲፓርትመንት ሠራተኞች ጋር በመተባበር ወደ ትምህርት ቤት እና ከት/ቤት ወደ ቤት በሁሉም አይነት መጓጓዣዎች ሠላም እና ደህንነታቸው ተጠብቆ መጓጓዝ እንዲችሉ ትብብር ማድረግን ያበረታታል። ተማሪዎች በአውቶቡስ እና በሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ባለቤትነት በሚተዳደሩ ወይም በተቀጠሩ ተሽከርካሪዎች ላይ ሲጓዙ ሁሉንም የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ህጎች እና የተማሪ የስነምግባር ደንብ የማክበር ግዴታ አለባቸው። የስነምግባር እና የደህንነት ህጎችን የሚጥሱ ተማሪዎች "MCPS ደንብ EEA-RA" መመሪያና ድንጋጌ መሠረት በአውቶቡስ የመጓጓዝ ጥቅም በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት ሊታገድባቸው ይችላል ስለ ተማሪ መጓጓዣ ።

የትምህርት ቤት አውቶቡስ ወይም የተማሪ አክቲቪቲ አውቶቡስ የተሳፋሪ መቀመጫ ላይ የሚገታ/የሚይዝ ቀበቶ ሲስተም እንዲያስር/እንድታስር ሲያስፈልግ (ማለትም:- በትክክኛ የሚጠልቁ ቀበቶዎች)፣ ሁሉም ተሳፋሪዎች ይህንኑ በመከተል ሠላማዊ/ጤነኛ ጉዞ ማድረግ አለባቸው። ለሁሉም ተሳፋሪዎች እንደየእድሜአቸው ሁኔታ፣ በተሳፋሪ መቀመጫ ላይ የሚገታ/የሚይዝ ቀበቶ በአግባቡ እንዲጠቀም/እንድትጠቀም መመሪያ ይሰጣል። በተሳፋሪ መቀመጫ ላይ የሚገታ/የሚይዝ ቀበቶ የማይጠቀሙ ወይም ያለአግባቡ የሚጠቀሙ ተማሪዎች የዲስፕሊን ቅጣት ይጠብቃቸዋል። የአካል ስንክልና ያለበ(ባ)ት ተማሪ በተሳፋሪ መቀመጫ ላይ የሚገታ/የሚይዝ ቀበቶ ለመጠቀም ካልቻለ/ች ወይም በአግባብ ካልተጠቀመ(ች)፣ የአውቶቡስ አሽከርካሪው(ዋ) ለርእሰመምህር ያሳውቃል/ታሳውቃለች። ርእሰመምህሩ(ሯ) ስለ ተሳፋሪ መቀመጫ ላይ የሚገታ/የሚይዝ ቀበቶ አጠቃቀም የ IEP ማሻሻያ ማድረግ ያስፈልግ እንደሆነ ለመወሰን IEP ስብሰባ ማድረግ ያስፈልግ እንደሆነ ይወስናል/ትወስናለች።

የተማሪዎችን ደህንነት ለመጨመር MCPS አውቶቡሶች ካሜራዎች ተገጥሞላቸዋል። ካሜራዎቹ ከውስጥም ሆነ ከውጭ የሚታዩ እንቅስቃሴዎችን እና የንግግር ተግባሮችን ሪኮርድ ያደርጋሉ።

## ■ የተማሪዎች ጤንነት እና ደህንነት

ተማሪዎች ስለ ግል ጤንነታቸው ሃላፊነት እንዲወስዱ፣ እና ጤናማ የአመጋገብ ልምድ፣ በየቀኑ የአካል እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ይበረታታሉ። የቦርድ ፖሊሲ JPG ደህንነት የአካል እና የአመጋገብ ጤንነት በት/ቤት የልጆች ጤነኛ አመጋገብ እና የአካል እንቅስቃሴዎችን የማዘውተር ባህል እንዲዳብር እና ጤንነታቸው እየተጠበቀ ለመማር እንዲችሉ ለመደገፍ የቦርዱን ቁርጠኝነት ማረጋገጫ ነው።

MCPS ደንብ JPG-RA፣ ጤነኛ ቁመና/ደህንነት/መልካም ጤንነት አካላዊ እና የአመጋገብ ጤንነት፣ አካላዊ እና የስነ-ምግብ ጤናን እና ማህበራዊ-ስሜታዊ ደህንነትን የሚያበረታቱ እና ለጤናማ የአኗኗር ዘይቤ አስተዋፅዖ የሚያደርጉ ባህሪያትን እና እንቅስቃሴዎችን የሚያስተምሩ የትምህርት ቤት አካባቢዎችን የመደገፍ ሥርአቶችን ያስቀምጣል። በትምህርት ቀናት መጀመሪያ፣ በመካከል እና ከትምህርት በኋላም የአካል እንቅስቃሴዎችን ማድረግ በጣም ይበረታታል።

"MCPS initiative, Be Well 365" የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ተነሳሽነት የተማሪዎቻችንን አካላዊ፣ ማህበራዊ እና ስነ-ልቦናዊ ደህንነት ይመለከታል። ተማሪዎች በአካላቸው፣ በአዕምሮአቸው እና በመንፈሳቸው ጤናማ ሲሆኑ በትምህርታቸው የተሻለ ውጤት ያስመዘግባሉ።

“የጤንነት ቁመና 365 (Be Well 365) ተማሪዎች በት/ቤት እና በሰፊው ማህበረሰብ ውስጥ መልካም አባላት እንዲሆኑ አስፈላጊ ክህሎቶች እንዳላቸው ለማረጋገጥ ይሠራል። ስሜታቸውን እንዲቆጣጠሩ፣ የአካዳሚክ እና ማህበራዊ ጥንካሬን ለመገንባት፣ ለራሳቸው ወይም ለጓደኛ ድጋፍ መስጠት እና መድረስ፣ ግጭትን በሰላም መፍታት፣ እና ሌሎች አዎንታዊ ውሳኔዎችን ለማረጋገጥ ይሠራል።

### የተማሪ የአስቸካይ ሁኔታ መረጃ/ኢንፎርሜሽን

ወላጆች/አሳዳጊዎች ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በአስቸኳይ የአደጋ ጊዜ የሚገኙበትን መረጃ ለመስጠት "ParentVue parent portal" ላይ የተማሪ የድንገተኛ አደጋ ጊዜ የግንኙነት መረጃ የሚለውን ክፍል መሙላት ወይም የተማሪ የአደጋ ጊዜ ግንኙነት መረጃMCPS ቅጽ 565-1 ሞልተው ወቅታዊ መረጃ መስጠት አለባቸው።

### የመስማት እና የማየት ምርመራ

በሜሪላንድ ህግ መሠረት የትምህርት ቤት ልጆች የመስማት እና የማየት ችሎታቸውን ለማጣራት ምርመራ እንዲደረግላቸው ይደነግጋል። ይህንን ህግ በማክበር ሁሉም የቅድመ መዋእለ ህጻናት፣ ሄድ ስታርት፣ መዋእለ ህጻናት፣1ኛ ክፍል፣ 8ኛ ክፍል፣ እና ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አዲስ የሆኑ ተማሪዎች የመስማት እና የማየት ችግሮች ካሉባቸው ምርመራና ማጣሪያ ይደረጋል። በልጅዎ ትምህርት ቤት የሰለጠኑ የት/ቤት የጤና አገልግሎት ሰራተኞች የመስማት እና የማየት ምርመራዎችን ያደርጋሉ። ተማሪያቸው የበለጠ የማጣራት ምርመራ እንዲደረግላቸው ካስፈለገ ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች ይገለጽላቸዋል።

ለልጅዎ የትምህርት ስኬት ጤናማ እይታ እና የመስማት ችሎታ አስፈላጊ ነው። ለመማር እና ማህበራዊ ግንኙነቶችን ለማዳበር ማየት እና መስማት አስፈላጊ ናቸው። ያልታወቁ እና ያልታከሙ የመስማት እና የማየት ችግሮች ካሉ በልጅዎ የማየት እና/ወይም የመስማት እና የመማር ችሎታ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ። ቤተሰቦች የመርጃ ሪሶርሶች የሚገኙበትን እርዳታና ድጋፍ ለማግኘት የትምህርት ቤታቸውን ነርስ ማነጋገር

አለባቸው። በሜሪላንድ ህግ መሰረት፣ በቤተክርስትያን መርሆዎች ወይም የቤተእምነት መርኅ ጋር ይጻረራል በሚል ምክንያት ልጃቸው ምርመራ እንዲደረግለ(ላ)ት የማይፈልጉ ወላጆች/አሳዳጊዎች ለት/ቤት ነርስ በጽሁፍ ጥያቄ ማቅረብ አለባቸው።

ምንጭ፡- Annotated Code of Maryland, Education Article, §7-404. ለተማሪዎች የመስማት እና የእይታ ምርመራ።

### የተማሪ ስክሪን አጠቃቀም

አንድ ተማሪ ከጤና እንክብካቤ ባለሙያ የጽሑፍ ፈቃድ ሳይዝ-ሳትይዝ በትምህርት ቤቱ ንብረት ወይም በትምህርት ቤት ስፖንሰር በተደረገ እንቅስቃሴ ላይ "sunscreen" መያዝ እና መጠቀም ይችላል/ትችላለች። ለፀሐይ የመጋለጥን አደጋ ለመከላከል ተማሪዎች "sunscreen" እንዲ ጠቀሙ ይመከራል።

### ራስን ስለ መግደል-ግንዛቤ

ሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (ከ6ኛ እስከ 12ኛ ክፍል) ራስን የመግደል ግንዛቤን ለማስተዋወቅ እና የአዕምሮ ጤንነትን ስጋቶች ለመቅረፍ ራስን የመግደል ምልክቶችን የመለየት እና የመከላከል ፕሮግራም ላይ ይሳተፋሉ። ዋናው መልእክት ሰዎች ስለ ጓደኞቻቸውም ሆነ ስለራሳቸው ስጋት ካደረባቸው እርምጃ (to ACT) እንዲወስዱ ነው፡-

» ጓደኛህ/ሽ እርዳታ ያስፈልገው/ያስፈልጋት እንደሆን ግንዛቤ መስጠት ያስፈልጋል
» ስለጓደኛህ(ሽ) ጥንቃቄ/እንክብካቤ አድርግ(ጊ)
» ለሚታመን አዋቂ/ጎልማሳ ሰው ተናገር(ሪ)

ማንኛውም ተማሪ፣ ወላጅ/ሞግዚት፣ ወይም የሥራ ባልደረባ ጭንቀት ስለሚታይበ(ባ)ት ተማሪ ካወቀ(ች) ወይም እርዳታ የሚያስፈልገው/የሚያ ስፈልጋት ከሆነ ACT ማድረግ/እርምጃ መውሰድ እና ለሚታመን አዋቂ/ ጎልማሳ ሰው ወይም ለአእምሮ ጤና ባለሙያ መንገር ያስፈልጋል።

በቀን 24 ሰዓት፣ በሳምንት ሰባት ቀናት ድጋፍ እና እርዳታ ይገኛል።

### ለድንገተኛ ጥሪ የስልክ መስመር

የቀውስ ማእከል . . . . . . . . . . . . . 240-777-4000

ብሄራዊ ራስን ማጥፋት መከላከል
National Suicide . . . . . . . . . . . . . . 988
ለመከላከል ክፍት መስመር/Prevention Lifeline (በየቀኑ 24 ሰዓት ክፍት ነው)

Trevor Project . . . . . . 866-488-7386፣ Text 678 678

ኦንላይን መነጋገሪያ
Online chat at www.contact-usa.org/chat

Text CONNECT to 741741 በዩናይትድ ስቴት ውስጥ ከየትም ቦታ ሆነው ቴክስት መላክ ይችላሉ

### አስፈሪ/አስጊ የሆነ ባህርይን መመርመር

በትምህርት ቤት ላይ የተመሰረቱ የባህሪ ስጋት ምዘና ቡድኖች (BTATs) በሁሉም የት/ቤቶች ደረጃ (ማለትም፡ አንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች) ለሚገኙ ተማሪዎች እና ሰራተኞች አስጊ ባህሪን እና የማስፈራራት ድርጊቶችን ስለማሳወቅ ሂደቶች መመሪያ ይሰጣሉ። በት/ቤት ላይ የተመ ሰረተ BTAT በሌሎች ላይ ጉዳት ለማድረስ የሚያስፈራራ/የምታስፈራራ ተማሪ ሲመረምር፣ የት/ቤት BTAT ራስን ስለመጉዳት እና ራስን ስለማ ጥፋት ሀሳብ መኖሩን ያጣራል። አስጊ ሁኔታን በመመርመር ሒደት MCPS ደንብ COA-RA መሠረት፣ አስጊ ባህርይን ስለመመርመር ፣ BTAT ማናቸውንም ራስን የመጉዳት ወይም ራስን የማጥፋት ዝንባሌን እና ተገቢነት ካለው፣ ተማሪው(ዋ)ን ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ቀውስ ማዕከል እና/ወይም ወደራሳቸው አገልግሎት ሰጪ ማስተላለፍ ይኖርበታል።

## ■ የህክምና አሰጣጥ

MCPS እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎት ዲፓር ትመንት (DHHS) በትምህርት ቀን ለተማሪዎች የህክምና መድኃኒት መስጠትን አያደፋፍሩም/አያበረታቱም። ከት/ቤት በፊት እና በኋላ ሊሰጡ የሚችሉ ማንኛውም አስፈላጊ መድሃኒት እንደዛው መታዘዝ ይኖርባቸዋል። ከመድኃኒት መደርደሪያ የሚገዙ መድሃኒቶችና homeopathic እንዲሁም ከዕፅዋት የሚቀመሙ መድኃኒቶች በሐኪም በሚታዘዙ ሕክምናዎች መሠረት ይሰጣሉ። በእርግጠኝነት አስፈላጊ ሲሆን የት/ቤት ሰራተኞች ከክፍል ውጪ በሚከናወኑ ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎች እና የመስክ ጉዞዎች እየተሳተፉ ለሚገኙ ተማሪዎች MCPS Forms 525-13 ቅደምተከተል መሠረት የህክምና መድኃኒት ይሰጣሉበኃኪም የታዘዘ መድኃኒት ለመስጠት የሚሰጥ ፈቃድ/Authorization to Administer Prescribed Medication ወይም 525-14 በተማሪ ላይ Anaphylaxis ሲያጋጥም አስቸኳይ ጥንቃቄ/እንክብካቤ ስለማድረግ - Emergency Care for the Management of a Student with a Diagnosis of Anaphylaxis

MCPS በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ቤት የጤና አገልግሎት መመሪያ መሰረት በትንፋሽ የሚሳብበት መሣሪያ/inhalers መጠቀም እና ኤፒንፍሪን አውቶ-ኢንጀክተሮች የመሳሰሉ በድንገተኛ ጊዜ የሚወሰዱ መድሃኒቶችን ለመስጠት/ራስን ለመውጋት ከጤና መምሪያ (DHHS) ፍቃድ ያለው ሀኪም አማካኝነት መፈቀድ አለበት፤ እና MCPS ቅጽ 525-13 እና 525-14 ተሞልቶ በትምህርት ቤት የጤና ነርስ መጽደቅ አለባቸው።

መጣቀሻ፡-
MCPS ደንብ JPC-RA

### ስለ ምግብ አለርጂ እና አናፊላክሲስ ግንዛቤ

በሜሪላንድ ህግ መሰረት፣ የምግብ እና የተመጣጠነ ስነ ምግብ አገልግሎት ዲፓርትመንት MCPS ድረ ገጽ ላይ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ሰራተኞች DFNS የሚቀርቡ ምግቦች በሜሪላንድ ህግ ከተጠቀሱት ዘጠኝ ዋና ዋና አለርጂዎች ውስጥ አንዳቸውም ካሉ መለየት የሚያስችል "የምግብ መመር መሪያ" ይኖራል።

### የአናፊላክሲስ መድሃኒት

ወላጆች/አሳዳጊዎች የተማሪን ልዩ የጤና አጠባበቅ ፍላጎቶች ወይም የአና ፊላክሲስ በሽታን ለይቶ ለማወቅ፣ ተገቢ የሆኑ መድሃኒቶችን የመስጠት እና ተገቢውን የፍቃድ ቅጽ የመሙላት ሃላፊነት አለባቸው። እነኚህ የህክምና መድሃኒቶች ለልጅዎ/ለተማሪዎ በአጣዳፊ ወቅት እንዲጠቀምበት-እንድትጠቀምበት በት/ቤቱ የጤና ክፍል ይቀመጣል። የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች በሜሪላንድ ስቴት የጤና አገልግሎት መመሪያ መሰረት፣ ለተማሪ የድንገተኛ ጊዜ እርዳታ የአናፊላ ክሲያ መድኃኒት ስለመስጠት፡MCPS ቅጽ 525-14፣ በመሙላት፣ በወላጅ/ አሳዳጊ ፈቃድ፣DHHS ፈቃድ ባከው የጤና ባለሙያ እና ትምህርት ቤት የጤና ባለሙያ ነርስ ፈቃድ፣ ተማሪዎች የኢፒንፍሪን ራሳቸው የሚወጉ በትን መርፌዎች መያዝ ይችላሉ። "Epinephrine Auto Injector" የጉዳት ካሳ ላለመጠየቅ የተደረገ ስምምነት መግለጫ የሜሪላንድ ስቴት ሁሉም ትምህርት ቤቶች ሠራተኞቻቸውን የ "anaphylaxis" ምልክቶችን እንዲያውቁ እና አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም የ epinephrine auto-injectors (ለምሳሌ፡- EpiPens) ክምችት እንዲኖራቸው መሰልጠን እንዳለ ባቸው ይደነግጋል። በየት/ቤቱ የተመደቡ ሠራተኞች epinephrine auto-injectors መስጠት እንዲችሉ የሠለጠኑ ናቸው።

### ስለ ስኳር በሽታ ግንዛቤ እና መድሃኒት

ወላጆች/አሳዳጊዎች ተማሪያቸው የስኳር በሽታ ካለበ(ባ)ት ለትምህርት ቤቱ የማሳወቅ ኃላፊነት አለባቸው፤ የተማሪው(ዋ) የስኳር በሽታ ህክምና እንክ ብካቤ ጋር የተዛመደ የተሟላ፣ ትክክለኛ እና ወቅታዊ የሕክምና መረጃ፣ የጽሑፍ የስኳር ህክምና ጥንቃቄ ዕቅድ (DMMP) ወይም የጤና እንክ ብካቤ ሰጪ የህክምና ትዕዛዝ ቅጽን ጨምሮ ለትምህርት ቤቱ መደበኛ እና የድንገተኛ ጊዜ መድኃኒቶችን እና የመድኃኒት አስተዳደር መሣሪያዎችን ማቅረብ፤ ተገቢውን የፈቃድ ቅጽ መሙላት፣ እና በተማሪው(ዋ) የሕክምና ፍላጎቶች ላይ ማናቸውንም ለውጦች ለት/ቤቱ ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል።

የስኳር በሽታ ላለባቸው ተማሪዎች የዕለት ተዕለት ኃላፊነት ያላቸው ሠራተኞች የተማሪዎቹን DMMP እና/ወይም የጤና እንክብካቤ ሰጪዎችን የህክምና ትዕዛዞች አፈፃፀም ለመደገፍ ተጨማሪ ሥልጠና ያገኛሉ። የት/ቤት ማህበረሰብ የጤና ነርስ ተማሪው/ዋ ት/ቤት በሚፈቅድላቸው ትምህርታዊ የመስክ ጉዞዎች ላይ በትክክል ለመሳተፍ እንዲችል/እንድትችል፣ በአግባቡ የስኳር በሽታ ክወናን/ቁጥጥር እውቀት ያለው "diabetes management activities" ተገቢውን የት/ቤት ሥራ ባልደረባ ለመወከል ከት/ቤቱና ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር በመተባበር ትሠራለች/ይሠራል።

ስለ Naloxone እና Opioid አደንዛዥ እፆች ግንዛቤ

"Start Talking Maryland Act of 2017" የሜሪላንድ ዲስትሪክቶች ስለ ሄሮይን (heroin) እና ኦፒዮይድ (opioid) ሱስ እና በመከላከል ላይ ያተኮረ ተጨማሪ ትምህርት እና እውቀት እንዲሰጡ ይጠይቃል። የት/ቤት ነርስ፣ የት/ቤት የጤና አገልግሎት ባለሞያዎች፣ እና ሌሎችም በ MCPS የሚታወቁ ሠራተኞች ከመጠን በላይ የተወሰዱ መድኃኒቶችን ማርከሻ ለመስጠትና ጉዳቱን ለመቆጣጠር ኃላፊነት የተሰጣቸዉ ሲሆን፣ Naloxone, or other overdose-reversing medication፣ ለተማሪዎች በድንገተኛ ሁኔታ ጊዜ የሚያገለግሉ መድሃኒቶች በት/ቤት ይቀመጣሉ።

JPD-RC ደንብ መሠረት Anaphylaxis ለሚሰቃዩ ተማሪዎች የአደጋ ጊዜ እንክብካቤMCPS ንብረት ውስጥ እና በትምህርት ቤት ስፖንሰር የተደረጉ እንቅስቃሴዎች ላይ በሚሳተፉበት ወቅት ናሎክሰንን የሚወስዱ ተማሪዎች ናሎክሰንን በመያዛቸው ምክንያት ብቻ የቅጣት እርምጃ አይወሰድባቸውም። ኦፒዮይድ ከመጠን በላይ የመውሰድ ጥርጣሬ ካለ፣ ተማሪዎች DHHS ወይም MCPS ሰራተኞችን እና/ወይም 911 እርዳታ ለማግኘት እንዲያነጋግሩ በጥብቅ ይበረታታሉ።

*ማጣቀሻዎች:-*
የቦርድ ፖሊሲ IGN፣ እና MCPS ደንብ JPC-RA፣ JPD-RB፣ እና JPD-RC

## ■ የተማሪ ስነ-ምግባር ደንብ

ሁሉም ተማሪዎች የሚማሩበት ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ የማግኘት መብት አላቸው። አወንታዊ የት/ቤት ድባብን የሚያበረታቱ ትምህርት ቤቶች ሁሉንም ተማሪዎች በመማር ላይ ለማሳተፍ እና ትምህርት የሚያታግላቸው ተጋላጭ ተማሪዎችን ለመደገፍ በተገቢው ሁኔታ ጣልቃ ይገባሉ። ፖሊሲ JGA፣ የባህሪ ጣልቃገብነት፣ ደህንነት እና የጤንነት ቁመና እቅድ፣ የባህሪ ጣልቃገብነት ፍልስፍና እና የተማሪ ባህሪያትን እና የመጥፎ ባህሪ መዘዝን ይገልጻል። የዚህ መመሪያ ትግበራ ለተማሪዎች፣ ለሰራተኞች እና ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ቤተሰቦች በሥነ ምግባር ደንቦች እና በመተግበሪያ ደንቦች ላይ ወጥነት ያለው የሚጠበቅ ሥነምግባር እና የተማሪን ባህሪ መዘዞችን ይዘረዝራል ከተማሪ ስነምግባር ጋር የማይጣጣም MCPS የስነምግባር ደንብ።

*ማጣቀሻዎች-*
MCPS ደንብ JGA-RA, JGA-RB, እና JGA-RC.

## ■ መፈተሽ/መፈለግና መያዝ

MCPS ሠራተኞች በተማሪው ላይ ወይም እቃውን ፍተሻ የሚያካሄዱበት እና ፍተሻ የተደረገበትን ነገር ለመያዝ የሚያስችላቸው ሁኔታዎች በሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች ደንብ "MCPS ደንብ JGB-RA" ፍተሻ ማካሄድ እና መያዝ/መውረስ/Search and Seizure ላይ ተገልጿል። መደበኛ ትምህርት እንዳይደናቀፍ ፍተሻ በማድረግ ለመውረስ እና ይዘው የተገኙ ተማሪዎችን ምንተፍረት ለመቀነስ የተቻለ ሁሉ ጥረት ይደረጋል።

ፍተሻ ለማድረግ እና/ወይም ለመውረስ የሚፈቀድላቸው የት/ቤት ኃላፊዎች ርእስ መምህር ወይም ረዳት ርእሰመምህር፣ MCPS የደህንነት እና የድንገተኛ አደጋ ማኔጅመንት ክፍል ሰራተኛ እና/ወይም የትምህርት ቤት የደህንነት ሰራተኛ፣ (MCPS ተቀጣሪ ሠራተኛ) እና በት/ቤት ስፖንሰር የተደረገ ጉዞ ላይ ያለ(ች) መምህር በፅሁፍ ኃላፊነት የተሰጠው/የተሰጣት እና ፍተሻ ለማድረግ በዳይሬክተሩ/በተወካዩ በጽሑፍ የተፈቀደለ(ላ)ት ሠራተኛ ብቻ ናቸው።

መቆለፊያ ሣጥን፣ ወይም እቃ ማስቀመጫ ክፍል፣ ወይም ሌሎች ከት/ቤት የተሰጡ ቁሳቁሶች የተማሪ የግል ንብረት ተደርጎ ስለማይቆጠር እንዲህ ዓይነቶቹ ቁሳቁሶች ላይ ፍተሻ ለማካሄድ ተማሪው(ዋ) ያልተፈቀደ ነገር መያዙ(ዟ)ን እርግጠኛ መሆን አስፈላጊ ላይሆን ይችላል። ነገር ግን፣ የተማሪ ንብረቶች በመቆለፊያ ክፍል ወይም በማስቀመጫ ኪዩቢክሎች (ለምሳሌ:- በጀርባ የሚያዙ ቦርሳዎች ወይም የእጅ ቦርሳዎች) ወይም በትምህርት ቤት ንብረት ላይ ያሉ ተሽከርካሪዎች (ለምሳሌ:- መኪና ወይም ብስክሌት) ሊፈተሹ የሚችሉት ጥሰቱን ምክንያታዊ መሆኑ ሲታመንበት ብቻ ነው፣ እና በማንኛውም የተማሪ ንብረት ላይ ፍተሻ በሚደረግበት ጊዜ ተጨማሪ MCPS ሰራተኛ አብሮ መኖር አለበት። የተማሪ ፍተሻ መጨረሻ ላይ፣ የተፈተሸ(ች)ውን ተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ ለመገናኘት ተቀባይነት ያለው ሙከራ ይደረጋል ፍተሻ የተደረገበትን ምክንያት እና ስለውጤቱ መረጃ ለመስጠት።

ህጋዊ ፍተሻ ለማድረግ የተማሪው(ዋ) ፈቃደኛ ያለመሆን የዲሲፕሊን እርምጃ ሊያስከትል ይችላል።

*ማጣቀሻዎች:-*
MCPS ደንብ JGB-RA
በሜሪላንድ የትምህርት ኮድ (Annotated Code of Maryland)፣ የትምህርት አንቀፅ፣ §7-308
ድረ-ገጽ www.montgomeryschoolsmd.org/departments/security/

## ■ ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት

በሜሪላንድ ህግ መሰረት፣ ጉልበት ተጠቅሞ ማጥቃት፣ ትንኮሳ እና ማስፈራራት ከባድ ጥፋቶች በመሆናቸው በትዕግስት አይታለፉም። MCPS ቅጽ 230-35 ጉልበተኝነትን፣ ትንኮሳን፣ ወይም ማስፈራራትን ሪፖርት ማድረግ፣ ቅጹ በተማሪ ተሞልቶ መቅረብ አለበት። የተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም የቅርብ ዘመድ፣ ወይም የትምህርት ቤት ሰራተኛ ተፈጽሟል ስለተባለው ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት ሪፖርት ለማድረግ የተሞላው ቅጽ ጉዳት/ጥቃት ለደረሰበት ተማሪ ትምህርት ቤት ለርእሰ መምህር መቅረብ አለበት። ለተጨማሪ መረጃ ወይም ዕርዳታ ትምህርት ቤቱን በማንኛውም ጊዜ ማነጋገር ይችላሉ።

ቦርዱ የሳይበር ጉልበተኝነትን፣ ትንኮሳን (ወሲባዊ ትንኮሳን ጨምሮ)፣ ማስፈራራት፣ ዛቻ፣ ወይም MCPS ንብረት ውስጥ ያለ ማንኛውንም ሰው የጥላቻ አድሎአዊ ድርጊቶችን ጨምሮ የቃል፣ የአካል ወይም የጽሁፍ (የኤሌክትሮኒክስ ጨምሮ) ጉልበተኝነት የተከለከለ ነው። ይህም ትምህርት ቤቶችን፣MCPS የሚተዳደሩ ግቢዎችን ወይም MCPS አውቶቡሶችን፣ ፋሲሊቲዎችን እና/ወይም MCPS የሚደገፉ ተማሪዎችን በሚያካትቱ እንቅስቃሴዎች ላይ የኤሌክትሮኒክስ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሚከናወኑ ትንኮሳዎችን ሁሉ ያካትታል።

በሜሪላንድ ህግ መሰረት፣ የቦርድ ፖሊሲ JHF የተከለከለ ባህሪ ማለት ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት ማለት ነው-

- ሆን ተብሎ የሚደረግ መጥፎ ተግባር፣ የቃል፣ የአካል ወይም የጽሁፍ ባህሪ፣ ወይም MCPS ንብረት ላይ ሆን ተብሎ የሚደረግ ያልተገባ የኤሌክትሮኒክስ ግንኙነት፣ በትምህርት ቤቶች፣MCPS በሚያስተዳድራቸው ግቢዎች፣MCPS አውቶቡሶች፣ ተቋም እና/ወይም MCPS ተማሪዎችን የሚያካትቱ እንቅስቃሴዎች ላይ፣ ወይም የትምህርት ቤቶችን ተግባራት በእጅጉ የሚያበላሹ ስነምግባሮችን ሁሉ ያካትታል፣ እና
- በተማሪ የትምህርት ጥቅማጥቅሞች፣ እድሎች ወይም ክንዋኔዎች ወይም በተማሪ አካላዊ ወይም ስነ-ልቦናዊ ደህንነት ላይ ከፍተኛ መሰናክል በመፍጠር የጥላቻ/የተቃርኖ የትምህርት አካባቢ ይፈጥራል — እና
  - » በቦርድ ፖሊሲ ACA፣ አድሎአዊ አለመሆን፣ ፍትሃዊነት እና የባህል ብቃት በተገለጹት ተጨባጭ ወይም በሚታዩ ግላዊ ባህሪያት የተነሳሳ፤
  - » ወሲባዊ ተፈጥሮ፣ የተማሪ የሰውነት ክፍሎች የተጋለጠበት ወይም በግብረ-ሥጋ ግንኙነት ተግባር ላይ ያለ ተማሪን የሚገልጥ ተግባር ወይም ምስሎችን ጨምሮ፣ ወይም
  - » ማስፈራራት ወይም ከባድ ማስፈራራት

በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት (MSDE) መመሪያ መሰረት፣ የሚከተሉት ትርጓሜዎች ጉልበተኞች (ሳይበር ጉልበተኝነትን ጨምሮ)፣ ትንኮሳ፣ ወይም MCPS ንብረት ላይ ያለ ማንኛውንም ሰው ማስፈራራትን ለመከላከል ጥቅም ላይ ይውላሉ:

ጉልበተኝነት ማለት በተማሪዎች መካከል ያልተፈለገ ወራዳ ባህሪ ማለት በፖሊሲ JHF የተከለከለ ስነምግባር መስፈርት የሚያሟሉ እና የሚከተሉትን ያጠቃልላል —

- » የሃይል አለመመጣጠን (ጉልበተኞች አካላዊ፣ ስሜታዊ፣ ማህበራዊ ወይም አካዳሚያዊ ሀይላቸውን ተጠቅመው ሌሎችን ለመቆጣጠር፣ ለማግለል ወይም ለመጉዳት መጠቀም) እና
- » መደጋገም (ከአንድ ጊዜ በላይ የተከሰቱ የጉልበተኝነት ባህሪያት ወይም በሚሰበሰቡ መረጃዎች ሊረጋገጡ የሚችሉ የመደጋገም ዕድላቸው ከፍተኛ የሆነ ጉልበተኝነትን ማሳየት)።

ሳይበር ጉልበተኝነት ማለት በፖሊሲ JHF ውስጥ የተከለከሉ ድርጊቶችን መስፈርቶች የሚያሟላ እና በተንቀሳቃሽ የመገናኛ መሳሪያ አማካኝነት ግለሰቦች እንዲመለከቱት ወይም እንዲያጋሩ በሚያስችል የኤሌክትሮኒክስ ግንኙነት የሚተላለፍ ትንኮሳና ጉልበተኝነት ማለት ነው።

» የሳይበር ጥቃት ስለ አንድ ሰው ውርደትን የሚያስከትል የግል ገመና ወይም ግላዊ መረጃን ማሠራጨት፣ መለጠፍ ወይም ማዳረስን ያጠቃልላል።

» በትምህርት ቤት መቼት የሳይበር ጥቃት ከተፈጸመ የዲሲፕሊን እርምጃ ሊወሰድ ይችላል። ትምህርት የሚሰጠው በአካል ወይም ቨርቹወል ቢሆንም በትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች ላይ የጉዳት አደጋን ይፈጥራል፣ ወይም የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታን ያውካል።

የኤሌክትሮኒክስ ግንኙነት ስልክ፣ ኮምፒውተር፣ ወይም ተንቀሳቃሽ የመገናኛ መሣሪያን ጨምሮ በኤሌክትሮኒክ መሣሪያ የሚተላለፍ ግንኙነት ነው።

ትንኮሳ ማለት በቦርድ ፖሊሲ ACA ላይ እንደተገለጸው በፖሊሲ JHF ውስጥ የተከለከሉ ድርጊቶችን መስፈርት የሚያሟሉ እና የአንድን ግለሰብ ትክክለኛ ወይም በይሆናል የሚታሰብ የግል ባህሪያትን በተመለከተ ሌላ ግለሰብን ማስቀየም፣ መሳለቂያ ማድረግ ወይም ማዋረድ ማለት ትክክለኛ ወይም የተገነዘቡ አሉታዊ ድርጊቶች ማለት ነው፣ አድሎአዊ ያልሆነ፣ ፍትሃዊነት፣ እና የባህል ብቃት ፣ ወይም ወሲባዊ ተፈጥሮ ያላቸው ናቸው፣ በቦርድ ፖሊሲ ACF፣ የተማሪዎች ጾታዊ ትንኮሳ፣ ወይም የቦርድ ፖሊሲ ACI፣ የሰራተኞች ጾታዊ ትንኮሳ፣ የተማሪው የሰውነት ክፍሎች የተጋለጠበት ወይም በግብረ-ሥጋ ግንኙነት ተግባር ላይ እያለ(ች) የሚያሳይ መግለጫዎች ወይም ምስሎችን ይጨምራል።

ማስፈራራት ማለት በፖሊሲ JHF የተከለከለ የስነምግባር መስፈርቶችን የሚያሟሉ እና የፍርሃት እና/ወይም የበታችነት ስሜትን የሚፈጥር ወይም የሚያነሳሳ በሌላ ግለሰብ ላይ የሚደረግ ማንኛውም እርምጃ ነው። የበቀል እርምጃ እንደ ማስፈራራት ሊቆጠር ይችላል።

ቦርዱ የጉልበተኝነት ትንኮሳን ወይም የማስፈራራት ድርጊቶችን ሪፖርት በሚያደርጉ ግለሰቦች ላይ ማናቸውንም የበቀል እርምጃ ለመከላከል ቁርጠኛ ነው። በጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት ተጎድተዋል የተባሉ ተማሪዎችን፤ ወይም ምስክሮችን፣ ተመልካቾችን፣ ወይም ሌሎች ስለ ጉልበተኝነት ጥቃት፣ ትንኮሳ ወይም የማስፈራራት ድርጊት አስተማማኝ መረጃ ያላቸው ግለሰቦችን ከበቀል እርምጃ ለመታደግ ቁርጠኛ ነው።

ጉልበተኝነት አካላዊ (መምታት፣ መግፋት፣ መገፍተር) ሊያካትት ይችላል ነገር ግን በዚህ ብቻ ሳይወሰን የቃል (መሳለቅ፣ ማስፈራራት፣ ማስገደድ፣ መሳለቂያ ማድረግ፣ የስድብ ስም መጥራት) ወይም ተዛማጅ የሆኑ(ወሬዎችን ማሰራጨት፣ ወይም ማግለል) ነው።

ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት ከተከሰተ ጥቃቱ የደረሰበ(ባ)ት ተማሪ፤ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም የቅርብ ዘመድ፣ ወይም የትምህርት ቤት ሰራተኛ MCPS ቅጽ 230-35፣ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራትን ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ፣ MCPS ደንብ JHF-RA፣ የተማሪ ጉልበተኝነት፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት፣ ቅጽ ሞልተው ወዲያውኑ ለትምህርት ቤቱ ርእሰመምህር ወይም ለሚመለከተው ኃላፊ/አስተዳዳሪ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው። የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጹ ተሞልቶ በወረቀት፣ በአካል ወይም MCPS ድረ ገጽ በኦንላይን www.montgomeryschoolsmd.org/info/bullying ሊቀርብ ይችላል። የት/ቤት ኃላፊ/አስተዳዳሪ ሁሉም ወገን ማስረጃ የሚያቀርቡበትን እድል ጨምሮ በፍጥነት ተገቢ፣ ተአማኒነት ያለው፣ እና አድሎ የሌለበት ምርመራ ያደርጋል/ታደርጋለች። ምርመራው እንደተጠናቀቀ፣ የትምህርት ቤት ኃላፊ/አስተዳዳሪ የመፍትሔ ርምጃዎችን እና ውጤቶችን እንደየአግባቡ ተግባራዊ ያደርጋል/ታደርጋለች፣ ጥቃቶችን፣ ማስፈራራት፣ ማስጨነቅ፣ ማስገደድ የመሣሰሉትን ነገሮች ድጋሚ እንዳይከሰቱ እርምጃ መዉሰድ እና እንዲሁም ለወላጆች/ለሞግዚቶችም ያሳውቃል/ታሳውቃለች።

## ተገቢ ያልሆነ ወሲባዊ ጠባይ እና ወሲባዊ ትንኮሳ

MCPS በማንኛውም ዓይነት የትምህርት መርሃ ግብሮች እና እንቅስቃሴዎች ውስጥ ወይም በንብረቱ ላይ በማንኛውም ዓይነት የጾታ ብልግና ወይም ወሲባዊ ትንኮሳ አይታገስም። ይኼውም፡- እንደ ወሲባዊ ስነምግባር ወይም የወሲብ ትንኮሳ ሊቆጠር የሚችል ተቀባይነት የሌለው ድርጊትን ሊያካትት ይችላል፣ ነገር ግን በዚህ አይገደብም—

- አስጸያፊ ቀልዶች፣ ስድቦች፣ ፀያፍ ምሳሌዎች ወይም ያልተገባ ስም መጥራት፣ አካላዊ ጥቃቶች ወይም ዛቻዎች፣ ማስፈራራት፣ መሳለቅ ወይም ፌዝ፣ ስድብ ወይም ማዋረድ/ማሳፈር፣ አፀያፊ ነገሮች ወይም በግለሰቦች ላይ ወይም በአንድ የተወሰነ ቡድን ላይ የተቃኙ ሥዕሎች፥
- በዚያ ግለሰብ ወይም ቡድን ትክክለኛ ወይም በይሆናል ግምት የጾታ፣ የጾታ ዝንባሌ፣ የሥርዓተ-ፆታ ማንነት፣ የሥርዓተ-ፆታ አገላለጽ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የእርግዝና/የወላጅነት ሁኔታ፣ እና/ወይም በጾታ ላይ የተመረኮዘ አመለካከት፣ በወንድነት ወይም በሴትነት አመለካከት ላይ የተመሠረተ አመለካከት ወይም አለመስማማት ላይ በመመስረት፣ ወይም
- የወሲባዊ ጥቃት፣ በፍቅር ጓደኝነት ውሎ ላይ የሚፈጸም ሁከት፣ የቤት ውስጥ ጥቃት፣ ጾታዊ ጥቃት፣ ወይም ማሳደድን ይጨምራል።

የጾታ ብልግና ወይም የወሲብ ትንኮሳ ቅሬታዎች ሪፖርት መደረግ አለባቸው። እንደዚህ አይነት ባህሪን ሪፖርት ለማድረግ አንዱ መንገድ MCPS ቅጽ 230-35፣ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራትን ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ ለትምህርት ቤት ሰራተኞች ወይም ርእሰመምህር MCPS ደንብ JHF-RA በተቀመጠው አሰራር መሰረት መስጠት ነው። የተማሪዎች ጉልበተኝነት፣ ጥቃት፣ ወይም ማስፈራራት። የወሲባዊ ሥነ ምግባር ጉድለትን ወይም የወሲባዊ ትንኮሳን ሁኔታ ሪፖርት በማድረጉ(ጓ) ምክንያት ወይም በምርመራ ላይ በመሳተፍ ወይም በመተባበር ምክንያት በግለሰቡ(ቧ) ላይ ምንም ዓይነት አሉታዊ እርምጃ አይወሰድም።

በአንዳንድ ሁኔታዎች የወሲባዊ ጥሰት ወይም የወሲባዊ ትንኮሳ የሕፃናትን በደል ወይም ቸልተኝነትን ሊያመለክት ይችላል። የተጠረጠረ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ወድያውኑ ለልጅ ደህንነት አገልግሎት (በተጨማሪም የልጅ ከለላና ጥበቃ አገልግሎት ተብሎ በዘልማድ ለሚጠራው) MCPS ደንብ JHC-RA የልጅ ማጎሳቆልና ቸልተኝነት ሪፖርት ምርመራ የተቀመጡትን ቅደም ተከተሎች በመከተል መቅረብ አለባቸው። የሚጠረጠር በደልን ወይም ቸልተኝነትን ሪፖርት ለማድረግ የሚያመነቱ ግለሰቦች ሪፖርት ባለማድረጋቸው ጥፋተኛ ይሆናሉ።

- ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ተማሪዎች እና የስራ ባልደረቦች ማንኛውንም የአድልዎ እና/ወሲባዊ ትንኮሳ ክስተቶችን ለ Title IX አስተባባሪ TitleIX@mcpsmd.org ላይ ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞችን የሚመለከቱ ሪፖርቶች፣ ቅሬታዎች፣ ወይም ክሶች በፍጥነት ወደ "Office of Human Resources and Talent Management, Department of Compliance and Investigations (DCI)" ሪፖርት መደረግ አለባቸው። DCI@mcpsmd.org በኢሜል ሊደረሳቸው ይችላል
- Safe Schools Maryland Tip Line ዛቻ-ማስፈራራት እና/ወይም ለደህንነት የሚያሰጋ ሁኔታን እና/ወይም የተማሪዎችን ደህንነት የሚያሰጉ ሁኔታዎችን ሪፖርት አድራጊው ማን እንደሆነ(ች) ይፋ የማይደረግ ሪፖርት የሚቀርብበት ሲስተም ነው። 1-833-MD-B-SAFE ይደውሉ ወይም "app" ያውርዱ-ይጫኑ።
- ሌሎች መገልገያዎች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ቀውስ ማእከል የስልክ ቁጥር 240-777-4000፣ የሰለጠኑ ሰራተኞች ወይም በጎ ፈቃደኞች በማዳመጥ ድጋፍ እና መረጃ ለመስጠት ዝግጁ ናቸው። የስልክ መስመር በየቀኑ 24 ሰዓት በሳምንት ሰባቱንም ቀኖች ይሠራል። ሰው ማናገር ለማይፈልጉ እና በአጭር የጽሑፍ መልክት ግንኙነት ማድረግ ለሚመርጡ EverMind የውይይት መድረክ Chat Now፣ www.every-mind.org ስለሆነ 7:00 a.m. ጥዋት እስከ እኩለ ሌሊት ክፍት ይሆናል። ቤተሰቦች ወይም ተማሪዎች ድጋፍ ለማግኘት ሲፈልጉ፥ የተጎጂ እርዳታ እና የወሲብ ጥቃት መከላከል ፕሮግራም/Victim Assistance and Sexual Assault Program (VASAP) ማነጋገር ይችላሉ። VASAP መረጃ እና ሪፈራል፣ መሚገት፣ እንዲሁም የከባድ ቀውስ ሁኔታ ድጋፍ ይሰጣል፥ እንዲሁም ለወሲባዊ ጥቃት ሰለባዎች ቀጣይነት ያለው የካውንስሊንግ አገልግሎት ይሰጣል።

ማጣቀሻዎች፡-
MCPS ደንብ ACF-RA, GKA-RA, JHC-RA, and JHF-RA
MCPSየተማሪ ስነምግባር ደንብ

## ■ MCPS የሠራተኛ ሥነምግባር ደንብ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የቦርዱ ዋና እሴቶች የሆኑትን ትምህርት፣ መልካም ግንኙነት፣ አክብሮት፣ ልቀት፣ እና ፍትሃዊነት ድርጅታዊ ባህል ለማስፋት ቁርጠኝነት አለው። በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሠራተኛ ሥነምግባር ደንብ/ Employee Code of Conduct ላይ እንደተገለጸው፣ለተማሪዎቻችን በሙሉ ሠላማዊ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የትምህርት አካባቢ ለመፍጠር ሁሉም ሠራተኞች ያልተቋጠበ ጥረት ማድረግ አለባቸው። ሁሉም ሰራተኞች ከሁሉም ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ በሁሉም ደረጃ ከሚገኙ ባልደረባዎች፣ እና ማህበረሰብ ጋር እጅጉን ከፍ ባለ ሃቀኝነትና ባለሞያዊነት/ professionalism እንዲገናኙ ይጠበቅባቸዋል።

### ማህበራዊ ሚዲያ፡- ለሠራተኞች እጅግ ጠቃሚ ምክሮች/ ልምምዶች

በተጨማሪም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስለ ማህበራዊ መገናኛ አውታር/ሚዲያ አጠቃቀም ለሠራተኞች መመሪያ ይሰጣል። መመሪያዎች በዚህ ሊንክ ይገኛሉ፡-www.montgomeryschoolsmd.org/social-media-best-practices/

ማጣቀሻዎች፡

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሠራተኛ ሥነምግባር ደንብ/ Employee Code of Conduct

MCPS የማህበራዊ መገናኛዎች/Social Media ለሠራተኞች እጅግ ጠቃሚ ምክሮች/ልምምዶች

ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞች ምርጥ የሆኑ የኢ-ሜይል እና የዲጂታል መገናኛ ተሞክሮዎች

በቦርድ፣ MCPS፣ እና በ MCPS ሠራተኛ ማህበራት መካከል የሰፈነ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የመከባበር ባህል/Culture of R.E.S.P.E.C.T

## ■ ይግባኞች-የቅሬታ ቅደም ተከተል— ተገቢው ሂደት

ይህ ክፍል የተተለመው ቅሬታ፣ የአድልዎ አቤቱታ፣ መታገድ ወይም ስንብት የማያጠቃልል የዲሲፕሊን እርምጃ፣ ወይም የስክልና ትምህርት ያላቸው ግለሰቦች አዋጅን የመሳሰለ በሌላ ህግ ወይም ደንብ ተለዋጭ የአለመግባባት እርቅ በተለይ የቀረበባቸው ሌሎች ጉዳዮች ውስጥ ለሚገኝ ለያንዳንዱ ተማሪ ስለ ርትአዊ አስተዳደር መረጃ ለማቅረብ ነው። እንደዚህ አይነት ህክምናን ለማከናወን የትምህርት ቤት ህጎች ከፌደራል እና ከስቴት ህጎች፣ የቦርድ ፖሊሲዎች እና MCPS ህጎች ጋር መጣጣም አለባቸው።

### በት/ቤት ደረጃ ውሳኔ

A. ተማሪው(ዋ) ለ --- መብት አለው/አላት

1. ይፋ ያልሆነ መፍትሔ/ውሳኔ ለማግኘት ከርእሰ መምህር ወይም ሌላ ተወካይ ጋር መገናኘት። ርእሰ መምህር ወይም ተወካዩ ይፋ ባልሆኑ ዘዴዎች ጉዳዩን ለመፍታት ይሞክራል/ ትሞክራለች፤ ወይም
2. መደበኛ ባልሆነው ሂደት ወይም በቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ካልተደሰቱ፣ ወይም 15 የትምህርት ቀናት ውስጥ መፍትሄ ካልተሰጠ፣ ያቀረቡትን ቅሬታ በሚመለከት ይፋዊ ግምገማ እንዲደረግላቸው MCPS ቅጽ 270-8 ሞልተው የትምህርት ቤት አመራር እና መሻሻል (DSLI) ዳይሬክተርን መጠየቅ ይችላሉ።

B. የተማሪው(ዋ) ቅሬታ በመደበኛ የአሠራር ሒደት በዳይሬክተሩ በሚገመገምበት ወቅት፣ ተማሪው(ዋ) ቅሬታውን የሚደግፉ ምስክሮችን እና ማስረጃዎችን የማቅረብ መብት ይኖረዋል/ ይኖራታል። እንደዚህ አይነት ውይይት ቀደም ሲል ተደርጎ ካልሆነ፥ የጽሑፍ ቅሬታ በደረሰው10 የሥራ ቀናት ውስጥ ዳይሬክተሩ ቅሬታ አቅራቢው(ዋ)ን የሚያነጋግርበትን ቀን እና ሰዓት ይወስናል። የጽሁፍ ቅሬታ በደረሰው 10 የስራ ቀናት ውስጥ ወይም በታቀደለት ስብሰባ ቀን ዳይሬክተሩ ውሳኔውን በጽሁፍ ሰጥቶ ቅጂውን ለቅሬታ አቅራቢው እንዲደርስ ማድረግ አለበት። ቅሬታው የተወሳሰበ ከሆነ ወይም በሌላ መልኩ 10 የስራ ቀናት ውስጥ በምክንያታዊነት ሊፈታ ካልቻለ ዳይሬክተሩ ቀነ-ገደቡን በ 10 የስራ ቀናት ማራዘም ይችላል።

### የርእሰ መምህሩ/ሯ ውሳኔ ይግባኝ

A. የይግባኝ አቀራረብ

ተማሪው(ዋ) DSLI ዲሬክተሩ(ሯ) በተሰጠ(ችው) ውሳኔ ካልረካ(ች)፣ የጽሁፍ ውሳኔ በተሰጠ 15 የትምህርት ቀናት ውስጥ ወይም ውሳኔው መሰጠት ከነበረበት ቀን የትኛውም ቀዳሚ ቢሆን ውሳኔውን ወደ "Division of Equity and Organizational Development" የሱፐር ኢንተንደንት ተወካይ በጽሁፍ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል/ ትችላለች። ይግባኙ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡-

1. የአቤቱታውና የርእሰ መምህሩ/ሯ ውሳኔ ድህረ እይታ እንዲደረግባቸው ጥያቄ
2. ሁሉም ተፈላጊ ሃቀኛ መረጃዎች
3. የሚጠየቀው መፍትሔ/ፍትሕ

B. የይግባኝ ግምገማ

1. "Division of Equity and Organizational Development"/ የፍትሃዊነት እና ድርጅታዊ ልማት ክፍል ኃላፊ የትምህርት ቤቶች ሱፐሪንተንደንት ተወካይ ሲሆን ጉዳዩን እና ተዛማጅ መረጃዎችን የመመርመር ሃላፊነት አለበ(ባ)ት።
2. ይግባኙ በደረሰ 45 የትምህርት ቀናት ውስጥ፣ የፍትሃዊነት እና ድርጅታዊ ልማት ክፍል ኃላፊ ወይም ተወካይ ተጨማሪ ምርመራ ካላስፈለገ በስተቀር ውሳኔ መስጠት እና ለተማሪው(ዋ) እና ለርእሰመምህሩ በጽሁፍ ማሳወቅ ይጠበቅበ(ባ)ታል።

### የፍትሃዊነት እና ድርጅታዊ ልማት ዋና ኃላፊ ውሳኔ ይግባኝ

ተማሪው(ዋ) የፍትሃዊነት እና ድርጅታዊ ልማት ክፍል የሰጠውን ውሳኔ ወደ "Division of Equity and Organizational Development/ Student Conduct and Appeals unit"/የተማሪ ስነምግባር እና ይግባኝ ሰሚ ክፍል በይግባኝ የማቅረብ መብት አለው/አላት። የፍትሃዊነት እና ድርጅታዊ ልማት ክፍል ኃላፊ ውሳኔውን ከሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ በዚህ የኢሜል አድራሻ (boe@mcpsmd.org ወይም በፋክስ ቁጥር 301-279-3860) የውሳኔውን ይግባኝ ማቅረብ ይችላል። ማመሳከሪያዎች/ማጣቀሻዎች፡- የትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎች BLB፣ BLC፣እና MCPS ደንብ KLA-RA ወይም የተማሪ ድጋፍ እና ክትትል አገልግሎት መምሪያን በስልክ ቁጥር 240-740-5620 ማግኘት ይችላሉ።

ማጣቀሻዎች፡-

የቦርድ ፖሊሲ BLB እና BLC እና MCPS ደንብ KLA-RA

የተማሪ ድጋፍ እና የት/ቤት ክትትል አገልግሎት፡- 240-740-5620

# የተመረጡ አባሪ ሠነዶች - APPENDIX—SELECTED
# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደምቦች-MCPS REGULATIONS

www.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy/

**MCPS ደንብ ABC-RA፣ የወላጅና የቤተሰብ ተሳትፎ**

ይህ ደንብ ጠንካራ በቤት እና ት/ቤት መካከል አጋርነት/ግንኙነትን ለማዳበር፣ በአካባቢ ት/ቤቶች የወላጅ/አሳዳጊ እና የቤተሰብ ተሳትፎ በየአካባቢው ት/ቤቶች የማህበረሰብ ብዙሃነትን የሚያንፀባርቅ ስኬታማ የሆነና ሁለገብ የወላጅ/አሳዳጊ እና ቤተሰብ ልምምዶችን እና ድጋፍ የማድረግን ጥረት ለማረጋገጥ የሚያስችል መሠረት ይሰጣል።

**MCPS ደንብ ABA-RC፣ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም አጠገብ ተቋራጮች/Vendors**

ይህ መመሪያ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ህንፃዎች ላይ በትምህርት ቀን ቢዝነስ ለመስራት የሚፈልጉ ተቋራጮች ከርእሰመምህር ፈቃድ ማግኘት ይኖርባቸዋል፣ እና ወቅታዊ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ኮድ እና በማናቸውም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ህዝባዊ መንገድ ወይም ከመንገድ ክልል 500 ጫማ እርቀት በሞንትጎመሪ ካውንቲ የፈቃድ መስጫ አገልግሎት ዲፓርትመንት ዳይሬክተር እና የትምህርት ቤት ርእሰመምህር/ት ለልዩ ሁነት ካልተፈቀደ በስተቀር ተቋራጮች በሞንትጎመሪ ካውንቲ መመሪያዎች መሠረት ፈቃድ ሊኖራቸው እንደሚያስፈልግ ይደነግጋል። ከትምህርት ቤት አውቶቡስ ማቆሚያ 100 ጫማ ርቀት ያነሰ ለአውቶቡስ መዳረሻ ከተያዘው የጊዜ ሠሌዳ 10 ደቂቃ እና አጠገብ በሚገኝ የግል ንብረት አንዳንድ የተቋራጭ እንቅስቃሴዎችን የሞንትጎመሪ ካውንቲ በጥብቅ ይገድባል።

**MCPS ደንብ ACA-RA፣ አድሎ የሌለበት፣ ፍትሃዊነት እና የባህል ብቃት**

ይህ ደንብ ስለአድሎአዊነት ክስ ምላሽ የመስጠት ሂደቶችን የሚደነግግ ሲሆን የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA መድልዎ የሌለበት፣ ፍትሃዊነት እና የባህል ብቃት መርህን ለማስፈፀም ኃላፊነት ያለባቸውን አግባብነት ያላቸው የአመራር ቢሮዎችን ይሰይማል፥ እንዲሁም ሁሉንም የፌዴራል፣ የስቴት፣ እና የአካባቢ አድሎአዊ ያልሆኑ ህጎች ገቢራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጣል።

**MCPS ደንብ CNA-RA፣ የመረጃ ቁሳቁሶችና ማስታወቂያዎችን ለእይታ ማቅረብና ስርጭት**

ይህ ደንብ ስለ ቁሳቁሶች/መገልገያዎች ማስታወቂያ እና/ወይም መግለጫዎች ፈቃድ እና ስርጭት ወይም የምርቶች አገልግሎትና ሽያጭን በተመለከተ መመርያ ይሰጣል።

**MCPS ደንብ CNA-RB፣ ማስታወቂያ**

ይህ ደንብ በሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በሙሉ ስለስፖንሰሮች ማስታወቂያና የእውቅና/ፈቃድ መስፈርቶችን ይገልጻል። ደንቡ ማስታወቂያዎች ዬት እንደሚቀመጡና ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆዩ ይገልፃል፣ ስለ ማስታወቂያዎች ይዘት መመዘኛ/መስፈርት ያስቀምጣል፣ የማስታወቂያ ውል ስለሚገባበት ሁኔታ መመሪያ ይሰጣል።

**MCPS ደንብ COA-RA አስጊ የሆነ ባሕርይን መመርመር/ማጤን**

ይህ ደንብ ከተማሪዎች፣ ከሰራተኞች፣ ከወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ተቋራጮች እና ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ጋር የሥራ ግንኙነት ከሌላቸው ግለሰቦች በትምህርት ቤት ንብረት ላይ ባህሪያቸው ለትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ወይም ለተማሪዎች ደህንነት አስጊ ከሆነ የምርመራ እና ጣልቃገብነት አሰራርን ለመዘርጋት መመሪያ ይሰጣል።

**MCPS ደንብ COB-RA የተከሰተ ነገርን ሪፖርት ስለማድረግ**

ደንቡ በት/ቤት ንብረት ላይ ወይም ከት/ቤት እንቅስቃሴ ጋር የተያያዘ ከባድ ሁኔታ ሲያጋጥም መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች ቅደም ተከተል ያስቀምጣል።

**MCPS ደንብ COC-RA፣ በሞንጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ላይ ጥሶ መግባት ወይም ሆን ብሎ የሚደረግ ረብሻ**

ይህ ደንብ በሞንጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረትን ጥሰዉ በሚገቡ ሰዎች ላይ የት/ቤት ሰራተኞች መውሰድ የሚገባቸውን ርምጃ ስልጣን ይገልጻል፤ ህጉንም ለማስከበር ቅደም ተከተሎችን ያስቀምጣል። ከት/ቤት ለጊዜው የታገዱ ተማሪዎች ከርእሰመምህር/ወይም ከተወካዩ ፈቃድ ካልተሰጣቸው በስተቀር ወደ ት/ቤት ግቢ እንዲገቡ አይፈቀድም።

**MCPS ደንብ COE-RA፣ የጦር መሳሪያዎች**

ይህ ደንብ በሞንጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS ) ንብረት ውስጥ አደገኛ/ወይም ገዳይ ተብለው የሚገመቱ መሳርያዎችን መያዝ የሚከለክልና ህጉ ከተጣሰ መከተል የሚባቸውን ቅደም ተከተሎች ይገልጻል። የጦር መሳሪያዎቹ "... የአካል ጉዳት የሚያስከትሉ መሳርያዎች ተብለው ተገልፀዋል። ይህም የሚተኮሱ መሳርያዎች፣ ጩቤዎች፣ እና ማንኛውም እንደ ጦር መሳርያ የሚያገለግልን ያጠቃልላል።"

**MCPS ደንብ COF-RA፣ አልኮል፣ ትምባሆ፣ እና ሌሎች እፆች MCPS ንብረት ላይ**

ይህ ደንብ በህኪም ትእዛዝ ካልተፈቀደ በስተቀር በት/ቤት ግቢ ውስጥ ማንኛውም ግለሰብ የአልኮል መጠጦች ወይም ቁጥጥር የሚደረግባቸው ንጥረ ነገሮች መብላት፣ መያዝ፣ ወይም ማሰራጨት ህገ ወጥ የሚያደርገውን የስቴት ህግ ያስቀምጣል እናም እንደዚህ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥም የት/ቤት አስተዳዳሪዎች ምን አይነት ቅደም ተከተሎችና መቀጮዎች ስራ ላይ እንደሚያውሉ ያስቀምጣል።

**የሞንጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንብ COG-RA የግል ተንቀሳቃሽ መገልገያዎች**

ይህ ደንብ ተማሪዎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ት/ቤት ውስጥ ወይም MCPS በሚያካሄዳቸው እንቅስቃሴዎች በሚሳተፉበት ወቅት የግል ሞባይል መገልገያዎችን የአጠቃቀም ሥርዓት ይደነግጋል።

**የሞንጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንብ ECC-RA፣ የሞንጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ንብረት መጥፋት ወይም መበላሸት/መጎዳት**

ደንቡ፣ በአደጋና በተንኮል በሁለቱም ለደረሰ ጉዳት፣ የተሰረቀ ንብረት፣ በእሳት የጠፋ ወይም የተበላሸን ጨምሮ የጠፋ ንብረት መለየትና ማመልከት፤ የተሰረቁ ወይም የወደሙ ነገሮችን ከት/ቤት ንብረት ዝርዝር መሰረዝ፤ እናም ለጠፋ ንብረት መተኪያ ማግኘት ቅደም ተከተሎችን ያስቀምጣል።

**MCPS ደንብ ECG-RA፣ ስለ ተማሪዎች ማሽከርከር የመኪና ማቆሚያ ስፍራዎች**

ይህ ደንብ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ተማሪዎች ለሚያሽከረክሯቸው መኪናዎች ያሉትን የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች መመደብን በሚመለከት የአካባቢ ትምህርት ቤት ህጎችን ለማዘጋጀት መመሪያዎችን ይደነግጋል፥ የሜሪላንድ ህጎችን እና የመኪና ማቆሚያ ፍቃዶችን እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ ባለቤትነት ስር ባሉ ንብረቶች ላይ ከመኪና ማቆሚያ ስፍራ ቶው ማስደረግ/ጎትቶ ማስነሳትን በተመለከተ የትምህርት ቦርድ (ቦርድ) ወይም በሞንትጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች (MCPS) ጎትቶ ስለማስነሳት ያለውን ውል የሜሪላንድ ህጎችን አተገባበር ያስቀምጣል።

**የሞንጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS )ደንብ ECI-RA፣ የዩናይትድ ስቴትስና የሜሪላንድ ሰንደቅ አላማዎችን በሚታይበት ቦታ ማድረግ።**

ደንቡ የሰንደቅ አላማዎች ማሳያ ቅደም ተከተሎችን ያስቀምጣል የመክፈቻ/መስቀያ ተግባሮች አፈቃቀድ እና ተማሪዎች በነዚህ ተግባሮች እንዲሳተፉ ማበረታታትን ይደነግጋል። ደንቡ ያለመሳተፍ ቅጣቶችን ይከለክላል።

**የሞንጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንብ EEA-RA፣ የተማሪ ትራንስፖርት/መጓጓዣ**

ይህ ደንብ ለያንዳንዱ የክፍል ደረጃ የእግር ጉዞ ርቀት መጠን ያስቀምጣል እናም ተማሪዎችን በማጓጓዝ፣ ተገቢ ሪፖርቶችን በመያዝ፣ እና ተገቢ የደህንነት ጥንቃቄዎች መወሰዳቸውን በማረጋገጥ ርእሰ መምህሩ/ሯ መከተል ያለበትን/ያለባትን መርሆች ይዘረዝራል። የአውቶቡስ አሽከራካሪ የዲሲፕሊን ችግሮችን ለማመልከት መከተል ያለበትን/ያለባትን ቅደም ተከተል ያስቀምጣል ርእሰ መምህሩ(ሯ)ም የተማሪ ዲሲፕሊን በሚገባ የመከታተል ሃላፊነቱ(ቷ)ን ይገልፃል። የልዩ ትምህርት ተማሪዎች እና ስለ አካለስንኩል ተማሪዎች ትራንስፖርትም ተመልክቷል።

**MCPS ደንብ EGF-RB የቪዲዮ ሪኮርዶችን መቅዳትና መያዝ እና ይፋ ማድረግ**

ይህ ደንብ በኮሪደሮች፣ ካፍቴሪያዎች፣ ጂምናዚየሞች፣ አዳራሾች፣ እና የት/ቤት ግቢዎች እንዲሁም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የትምህርት ቤት አውቶቡሶች ከውስጥ እና ከውጪ ከሚገኙት MCS የደህንነት ካሜራዎች የቪዲዮ ቀረጻዎችን መውሰድ እና ይፋ የማድረግ ሂደቶችን ይደነግጋል። የመማሪያ ክፍሎች እንደ የሕዝብ ቦታዎች አይቆጠሩም፣ እንደዚሁም MCPS በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ በቪዲዮ ካሜራ ክትትል አይደረግም።

**የሞንጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንብ EKA-RA፣ ለአስቸኳይ ሁኔታና ለአደጋ ጊዜ ቅድመ-ዝግጅት**

ይህ ደንብ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሥራ ቦታዎች ላይ ለሚገኙ ሰዎች ደህንነታቸውን ለመጠበቅ በት/ቤት የሚከሰቱ ቀውሶችን ለመከላከል የሚያስችሉ ሁለገብ እቅዶችን አሠራር ቅደምተከተል ማጎልበትና አጠባበቅ ሥርዓት ይደነግጋል።

**MCPS ደንብ FAA-RA ስለ ትምህርት ፋሲሊቲዎች ማቀድ**

ይህ በቅርቡ ክለሳ የተደረገበት ደንብ የቦርድ ፖሊሲ/Board Policy FAA ሦስት ቁልፍ ክፍሎች የሚተገበሩበትን ሂደት ይገልጻል፡- 1) የተማሪ ምዝገባ ግምትን እና ቁስ-አካላዊ የትምህርት ፋሲሊቲዎች እና የህንፃ ሲስተሞችን በቀጣይነት በዝርዝር መገምገም፣ 2) ስለፋሲሊቲ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ እና አስተዋጽ፣ እና 3) ምላሽ አማራጮችን ጠቋሚ እና ወደ ፍትኃዊ ሃላፊነት የተሞላበት የገንዘብ እና ትርጉም ያለው ትምህርት ውሳኔዎች፣ የአካባቢ፣ ስቴት፣ እና ፌደራል መስፈርቶች፣ የቦርድ ፖሊሲ ACA ሚዛናዊ አንድምታ፣ ከአድሎአዊነት የፀዳ፣ ፍትሐዊ፣ እና ባህላዊ ብቃትን ሁሉ ወደሚያገናዝብ ውሳኔ የሚያመራ የውሳኔ አሰጣጥ ማዕቀፍ።

**MCPS ደንብ FFA-RA፣ የትምህርት ቤት መገልገያዎችን መሰየም**

ይህ ደንብ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ FFA፣ የትምህርት ቤት መገልገያዎችን መሰየም የመተግበር ሂደቶችን ያስቀምጣል።

**MCPS ደንብ IGO-RA፣ የአልኮል ስካር ክስተቶች መመሪያ፣ ካናቢስ፣ ትምባሆ እና ሌሎች ተማሪዎችን የሚመለከቱ የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀምን የሚገድብ መመሪያ**

ይህ ደንብ አልኮል፣ ካናቢስ፣ ትንባሆ፣ እና ሌሎች ተማሪዎችን የሚመለከቱ የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም ወይም ማጨስ የተከለከሉ ሂደቶችን ያስቀምጣል።

### MCPS ደንብ IGT-RA፣ የኮምፒውተር ስርአቶች፣ የኤሌክትሮኒክ መረጃዎች፣ እና የአውታረ መረብ ጥበቃ ተጠቃሚ ሀላፊነቶች

ይህ ደንብ የኢሜል አካውንት እና አግባብነት ያለው የስቴት፣ የአካባቢ እና የፌደራል ህግን ማክበር እና የኮምፒዩተር ኔትወርኮችን በአግባቡ የመጠቀም ሂደቶችን እና የሚጠበቁ ስነስርአቶችን ያስቀምጣል።

### MCPS ደንብ IID-RA፣ በሞንጎምሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የትምህርት አውታሮች ስለሚሰራጩ/Cablecast/ ፕሮግራሞች

ይህ ደንብ በሜሪላንድ ስቴት ተፈላጊ የሆነዉን እና የሞንጎምሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ የተቀበለው/የተስማማበት ሁለገብ የጤና ትምህርት ፕሮግራም ለሁሉም ተማሪዎች መሰጠት እንዳለበት ቅደም ተከተሎችን ይዘረዝራል።

### MCPS ደንብ IGP-RA፣ አጠቃላይ የጤና ትምህርት ማስተማርያ ፕሮግራም

ይህ ደንብ በሜሪላንድ ስቴት ተፈላጊ የሆነዉን እና የሞንጎምሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ የተቀበለው/የተስማማበት ሁለገብ የጤና ትምህርት ፕሮግራም ለሁሉም ተማሪዎች መሰጠት እንዳለበት ቅደም ተከተሎችን ይዘረዝራል።

### MCPS ደንብ IKA-RA፣ የትምህርት ውጤት/ማርክ አሰጣጥና ሪፖርት አቀራረብ

ይህ ደንብ ማርክ አሰጣጥንና-የሪፖርት አቀራረብ ሂደቶችን በተመለከተ ከሞንጎምሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እና በሜሪላንድ ስቴት በደረጃ ስርአተ ትምህርትና ግምገማዎች ጋር በማቀናጀት የተማሪ ግኝትን/የምህርት ክህሎትን በትክክል የሚያንፀባርቁ ማርክ አሰጣጦችን ያንጸባርቃል።

### MCPS ደንብ IKB-RA፣ የቤት ስራ ቅደም ተከተሎች

ይህ ደንብ ስለቤት ስራ ቅደም ተከተሎችና የሚሰጡ ስራዎች ዝርዝር መመርያ ይሰጣል። በተጨማሪም በኃይማኖት ምክንያት ተፈቅዶላቸው ትምህርት ያመለጣቸው ተማሪዎች የማካካሻ ቤት ሥራ የመስራት እድል እንደሚሰጣቸው ይገልጻል።

### MCPS ደንብ IKC-RA፣ የክፍል ትምህርት ማርክ/ነጥቦች አማካይ ውጤት(GPA) እና Weighted Grade Point Averages/የተመዘነ የአጠቃላይ ነጥቦች ማርክ አማካይ (WGPA)

ይህ ደንብ የክፍል ማርክ አማካይ ነጥብ እና የተመዘነ የአጠቃላይ ማርክ አማካዮች ውጤት አወሳሰንና ለአሁንና ለወደፊት ቀጣሪዎች እንዲሁም እንደ ማመልከቻና የመቀበያ ሂደት አካል የሚጠይቁት ከ2ኛ ደረጃ በላይ ላሉ የትምህርት ተቋሞች ዘግቦ ለማስተላለፍ ቅደም ተከተሎችን ያስቀምጣል።

### MCPS ደንብ IOE-RA ስለ ነፍሰጡር እና ወላጅ የሆኑ ተማሪዎች ትምህርት የመቀጠል መመሪያዎች።

ይህ መመሪያ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሚማሩ ነፍሰጡር እና ወላጅ ተማሪዎች በትምህርት ለመቆየት እንዲችሉ በት/ቤት ትምህርታቸውን ለመቀጠል የሚያስችላቸውን የአፈጻጸም ሥርአት ቅደምተከተሎች፣እንደአግባቡ ከፌደራል እና ከስቴት ህግ ጋር የሚጣጣም ኃላፊነት ስለመስጠት ይደነግጋል።

### MCPS ደንብ IOE-RB፣ ቤት ውስጥ እና በሆስፒታል ስለማስተማር

ይህ መመሪያ በሜሪላንድ ህግ መሠረት በታወቀ አካላዊ ወይም የአእምሮ የጤና ሁኔታ ምክንያት በተመዘገበ(ች)በት MCPS ትምህርት ቤት ሊሳተፉ ያልቻሉ ተማሪዎች MCPS የትምህርት መስፈርት እንዲያሟሉ ስለ ሽግግር የማስተማር አገልግሎት (IIS) የትምህርት አሰጣጥ ሂደት ይደነግጋል።

### MCPS ደንብ IPD-RA፣ የትምህርት ጉዞ ፕሮግራሞች፣ የመስክ ጉዞዎች፣ እና የተማሪዎች ድርጅት ጉዞዎች

ይህ ደንብ ስለ መስክ ጉዞዎች፣ ስለተማሪ ድርጅት ጉዞዎች፣ እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሚተገበር የትምህርት-ጉዞ ፕሮግራሞች፣ እና እቅድ ማዘጋጀት፣ ፈቃድ/ይሁንታ ስለማግኘት፣ እና የተፈቀዱ ጉዞዎችን ስለመተግበር ይዘረዝራል።

### MCPS ደንብ IOA-RA፣ የከፍተኛ ተሰጥኦና የላቀ ችሎታ ትምህርት

ይህ ደንብ የከፍተኛ ተሰጥኦ እና የላቀ ችሎታ ላላቸው ትምህርት መመርያ ተግባራዊ የሚደረግበትን ቅደም ተከተል ይዘረዝራል።

### MCPS ደንብ IQA-RA፣ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በት/ቤቶች መካከል የአትሌቲክ ፕሮግራሞች አስተዳደር

ይህ ደንብ በሞንትጎመሪ ካውንቲ 2ኛ ደረጃ ትም/ቤቶች መካከል የሚከናወን አትሌቲክስ ካውንቲ-አቀፍ የት/ቤቶች ፕሮግራሞች አስተዳደር ስልጣን ያብራራል። ሁሉንም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአትሌቲክስ ዘርፎችን የሚመለከቱ መርሃ ግብሮች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአትሌቲክስ መመሪያ መጽሔት ውስጥ ይገኛሉ፣ እንዲሁም በእያንዳንዱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚዲያ ማእከል ውስጥ ይኖራል። በተጨማሪም፣ MCPS የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአትሌቲክስ መመሪያ መጽሃፍ MCPS የአትሌቲክስ ድረ-ገጽ የሪሶርስ መረጃ ቋት ላይ ይገኛል።

### MCPS ደንብ IQB-RA፣ ከመደበኛ ከሪኩለም ውጭ እና ከሪኩለም ጋር የተቀናጁ አክቲቪቲዎች

ይህ ደንብ ከስርአተ ትምህርት-ውጭ እንቅስቃሴ ፕሮግራሞችን የመመስረት፣ የማስተዳደር፣ የመምራት መስፈርቶችን ያስቀምጣል።

### MCPS ደንብ IQD-RA፣ ኢንተርኮላስቲክ አትሌቲክስ ውስጥ ስለሚሳተፉ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የአካዳሚክ ብቁነት

ይህ ደንብ ላይ የተመሰረተው 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ማሟላት የሚገባችውን/ብቃት ቅደም ተከተሎችን ያስቀምጣል።

### MCPS ደንብ IQD-RB፣ ኢንተርኮላስቲክ አትሌቲክስ ውስጥ ስለሚሳተፉ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የአካዳሚክ ብቁነት

በዚህ ደንብ መሠረት ለመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ብቃት ቅደም ተከተሎች ተቀምጠዋል።

### MCPS ደንብ IRB-RA፣ በት/ቤት በጎ ፈቃደኝነት

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የወላጅ/ሞግዚት እና የማህበረሰብ በጎፈቃድ አገልግሎቶችን ስለማበረታታ እና በውጤታማነት የመጠቀም ሥርአት/ቅደምተከተሎችን ይደነግጋል።

### MCPS ደንብ ISB-RA፣ ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለመመረቅ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

ይህ ደንብ የስቴት እና የካውንቲ ለመመረቂያ ተፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎችን እና የአፈፃፀም ቅደም ተከተሎችን ያመለክታል። በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የኮርስ መጽሔት ላይ ተጨማሪ ዝርዝር ለማግኘት ይችላሉ።

### MCPS ደንብ JEA-RA፣ የተማሪ በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት

ይህ ደንብ ከት/ቤት ቀሪ የሚሆኑ ተማሪዎችን መቅረት እንዳያዘወትሩ ክትትል ስለማድረግ፣ በይቅርታ የሚታለፉበት ሁኔታ፣ ክትትል ስለማድረግና የሚቀሩባቸውን ቀናት መዝግቦ መያዝ፣ መቅረትን ስለማሻሻል ተግባራዊ የሚደረጉ አግባብነት ያላቸውን ን/ክፍሎች ለይቶ ያስቀምጣል፣ በትምህርት ላይ መገኘት፣መከታተል፣መሳተፍን ለማሻሻልና ከተማሪዎችና ከወላጆች/ሞግዚቶች ጋር ክትትል ስለማድረግ ቅደም ተከተሎችን ይገልጻል።

### MCPS ደንብ JEA-RC፣ የአለም አቀፍ እና የውጭ ተማሪዎች ምዝገባ እና ምደባ

ይህ ደንብ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩል የሚከናወኑ የውጭ፣ እና ዓለም አቀፍ ተማሪዎችን ምዝገባ እና የምደባ ሂደቶችን ይደነግጋል።

### MCPS ደንብ JEA-RE ፣ በትምህርት ክፍያ ላይ የተመሠረተ ምዝገባ

ይህ ደንብ ከሚማሩባቸው ክፍሎች ለመውጣትና ከት/ቤት ለዘለቄታው ለማቋረጥ ተማሪዎች መከተል ያለባቸው ቅደም ተከተሎችን ያስቀምጣል። እንደዚህ ለመሳሰሉት እርምጃዎች የጊዜ ገደቦችን ይገልፃል ለትምህርት ውጤት/ማርኮችና ለክሬዲቶች አሰጣጥም መመርያዎችን ያስቀምጣል።

### MCPS ደንብ JEE-RA፣ የተማሪ ዝውውር እና አስተዳደራዊ ምደባዎች

ይህ ደንብ በካውንቲው ውስጥ የትምህርት ቤት ምደባ ለውጦች (የተማሪ ዝውውሮች) እና የአስተዳደር ምደባዎችን የሚመለከቱ ሂደቶችን ይደነግጋል።

### MCPS ደንብ JFA-RA፣ የተማሪ መብቶችና ኃላፊነቶች

ይህ መመርያ የቦርድ መመርያ JFA፣ የተማሪ መብቶችና ኃላፊነቶች አተገባበር ቅደም ተከተሎችን ይሰጣል።

### MCPS ደንብ JGA-RA፣ የተማሪ ባህሪ የማስተካከል ጣልቃገብነቶች

ይህ ደንብ ጤናማ እና ለመማር አመቺ ሁኔታዎችን ለማዳበር የተቀየሱ በመማርያ ክፍል ውስጥ ዘላቂ የሆኑ ፅኑ የዲሲፕሊን እና የቁጥጥር ሥርአት ለመዘርጋት የሚያስችሉ ቅደም ተከተሎችን ይገልጻል። ደንቡ በዚህ ሰነድ አግባብነት በሞንጎሞሪ ካውንቲ የትምህርት ማህበር እና በቦርዱ መካከል ባለው ስምምነት መስረት የርእሰ መምህሩ(ሯ)ን ኃላፊነቶች በሚመለከት ግልጽ/ዝርዝር አቅጣጫዎችን ያሳያል።

### MCPS ደንብ JGA-RB፣ ከትምህርት ቤት ማገድ እና ማሰናበት

ይህ ደንብ በተማሪዎች ላይ ስለሚደረግ እገዳ እና ስንብት የስቴቱን ህግ በስራ ላይ ያውላል፣ ስለሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ሰራተኛ ሃላፊነቶች የሚገልፁ ቅደም ተከተሎችን ያስቀምጣል፣ በአሰራር ሂደት ላይ የተማሪዎች መብቶችን ያብራራል፣ እና የአቤቱታ መንገዶችንም ይጠቁማል።

### MCPS ደንብ JGA-RC ስንክልና ያለባቸውን ተማሪዎች ስለማገድና ማባረር/ማሰናበት

ይህ ደንብ በግላዊ የትምህርት ፕሮግራሞች (IEPs) የሚገኙ ተማሪዎችና ለRehabilitation Act of 1973/ የማገገሚያ ህግ አንቀጽ 504 የታቀፉ ተማሪዎች እገዳና ስንብትን የሚመለከቱ በፌደራል ህግ ስር የሚገኙ መመዘኛዎችን ይገልፃል/ያብራራል።

### MCPS ደንብ JGB-RA፣ ፍተሻ እና መውርስ

ይህ ደንብ ተማሪዎች የMCPS ደንብ የጣሰ የማይገባ/አደገኛ ነገር ይዘዋል ተብሎ በሚጠረጠሩበት ነገር ፍተሻ ስለማድረግና በጥርጣሬ ፍተሻ የተገኙ ነገሮችን ስለመውረስ በዝርዝርና በግልጽ የተቀመጠ መመሪያ ነው።

### MCPS ደንብ JHC-RA፣ ስለ ህፃናት መጎሳቆል እና ትኩረት መነፈግ ምርመራ እና ሪፖርት ማድረግ

ይህ ደንብ ህፃን/ልጅ ማጎሳቆልና ቸልተኝነት የሚገልጽ ሲሆን፣ ሁሉንም የሰራተኛ አባላት የሞንጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን በመወከል ያዩትን ሪፖርት አቅራቢዎች፣ ስለ ሃላፊነታቸው፣ የህፃን/ልጅ ማጎሳቆልና ቸልተኝነትን ምልክቶች እንዴት ማወቅ እንደሚቻል፣ እናም የሜሪላንድ ስቴትን ህግን አለማክበር ስለሚያስከትለው መዘዝ ለማሳወቅ እና ለማሰልጠን የሚወስዳቸውን ሂደቶች ይገልፃል። ይህ ደንብ በሞንጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሰራተኛ አባለት ተፈፀመ የሚባል የህፃን/ልጅ ማጎሳቆልና ቸልተኝነት፣ ወይም ሌላ ተገቢ ያልሆነ ስነምግባር ጥቆማዎችን/ጥርጣሬዎችን ለመመርመር MCPS የሚከተላቸውን ሂደቶች በተጨማሪ ይገልፃል።

### MCPS ደንብ JHF-RA፣ ተማሪን ጉልበት ተጠቅሞ ማጥቃት-ማስጨነቅ፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት

ይህ ደንብ ት/ቤቶች ለመማርያ ሰላማዊ ቦታ ይሆኑ ዘንድ ከወከባ፣ ከማስፈራራት እና ከማሸማቀቅ ነፃ የሆነ አካባቢ ለማስፈን MCPS ያለውን ቁርጠኝነት ይገልፃል። ደንቡ "ስለ ወከባ፣ ማስጨነቅ፣ እና ማስፈራራት" ይገልፃል እንዲሁም መከላከል፣ ጣልቃ-ገብነት፣ መዘዞች፣ እና የመፍትሔ እርምጃዎች፣ እናም የማሸማቀቅ፣ የወከባ፣ እና የማስፈራራት ተግባርን ሪፖርት የማቅረብ ቅደም ተከተል ደረጃዎችን ያስቀምጣል።

**MCPS ደንብ JHG-RA፣ ወንበዴዎች፣ የውንብድና እንቅስቃሴ፣ ወይም ተመሳሳይ አጥፊ ወይም ህገወጥ የቡድን ስነምግባር መከላከል**

ይህ ደንብ የሚገልጸው የትምህርት/አካዴሚያዊ ስኬት እና ማህበራዊ እድገት የሚጎለብቱት ተማሪዎችና ሰራተኞች ሰላም እንደሰፈነ ሲሰማቸው ነው የሚለውን የሞንጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እምነት ይገልፃል። ወንበዴዎች፣ የውንብድና እንቅስቃሴ፣ ወይም ተመሳሳይ አፍራሽ ወይም ሕገ-ወጥ የቡድን እንቅስቃሴዎች (የወሮበላነት-ስነምግባሮች) በት/ቤቶች ሰላማዊ የሥራ ሂደት ውስጥ ጣልቃ ይገባሉ። ደንቡ ወንበዴዎች፣ የውንብድና እንቅስቃሴ፣ የመከላከያ ተግባሮች፣ እና የጣልቃገብ እንቅስቃሴዎችን ይገልፃል። ለመከላከል የሚደረጉ ቅደምተከተሎች፣ ጣልቃ ገብነት፣ መዘዞቹ፣ የሪፖርት/የጥቆማ ቅደም ተከተሎች፣ የምርመራ ቅደም ተከተሎች እና የድጋፍ አገልግሎቶችን ቅደም ተከተሎች ይገልጻል።

**MCPS ደንብ JIA-RA፣ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የላቀ ትምህርት ማህበረሰብ እና የልቀት ተማሪዎች**

ይህ ደንብ በመካከለኛ እና በ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የልቀት ትምህርት ስርአት፣ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ደግሞ የላቀ ማህበረሰብ ስለማቋቋም ቅደም ተከተሎችን ይሰጣል።

**MCPS ደንብ JNA-RA፣ለተማሪዎች ከትምህርት ጋር የተገናኙ ወጪዎች**

ይህ ደንብ የተማሪዎች የኤኮኖሚ ሁኔታዎች ሳይገድባቸው፣ ሁሉንም ኮርሶች እንዲማሩ/እንዲያገኙ ማስቻል፣ ለኮርሶች የሚያስፈልጉ የትምህርት ቁሳቁሶች፣ እና የትምህርት ፕሮግራም ለሁሉም ተማሪዎች የሚቀርብበትን ስርአት ይገልጻል።

**MCPS ደንብ JNA-RB፣ ከተማሪ የፋይናንስ ክፍያ መሰብሰብ**

ይህ ደንብ የተማሪ የፋይናንስ ግዴታዎች መመርያዎችን ይዘረዝራል። MCPS ንብረት በመጥፋቱ ወይም በመበላሸቱ ለመተካት ወይም ለመጠገን፣ ወይም ያልተከፈሉ የተማሪ እዳዎችን ለሞንጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስለመክፈል።

**MCPS ደንብ JOA-RA፣ የተማሪ ሪከርዶች**

ይህ ደንብ ስለ ተማሪዎች መረጃ አሰባሰብ፣አያያዝ/ጥበቃ፣ እና ስርጭት ሃላፊነቶች የሚመለከት ስርአት ይገልጻል።

**MCPS ደንብ JPA-RB፣ ደህንነት እና የምልመላ ፕሮግራሞች፡- ሊድ/እርሳስ፣ ማዳመጥ፣ እና እይታ**

ይህ መመሪያ ሊድ/Lead በተሰኘ ኬሚካል የመመረዝ አደጋ ስለተጋለጡ ተማሪዎች እና የመስማት እና የማየት ችግር የሚኖርባቸውን ተማሪዎች የመመልመል እና ለመስማትና ለማየት ያልቻሉ ተማሪዎችን ክትትል ለማድረግ ለመመልመል የስቴት እና የፌደራል መመሪያዎችን ተግባራዊ ስለማድረግ አስፈላጊ መስፈርቶችን ያስቀምጣል። ይህ መመሪያ በተጨማሪም በትምህርት ቤት እና በየቢሮዎቹ የመጠጥ ውኃ ጤናማነት ከስቴት እና ከፌደራል መመሪያዎች ጋር የሚጣጣሙ ቅደምተከተሎችን ያስቀምጣል።

**MCPS ደንብ JPG-RA፥ ጤነኛ ቁመና፡- የአካላዊ እና የአመጋገብ ጤንነት**

ይህ ደንብ በት/ቤት ደረጃ ስለ ጤናማነት አማካሪ ቡድን እና ስለ ጤና እንቅስቃሴን እንደ ስሜታዊ እና ማህበራዊ ደህንነት በቅንጅት ማስኬድ በትምህርት ቤት ስለ ጤንነት መሻሻል ከሚደረጉ ተግባሮች አንዱ ሆኖ እንዲያዝ ይደነግጋል። ደንቡ በተጨማሪም አሁን በመካሄድ ላይ ያሉ የጤና ትምህርት፣ ስነ-አመጋገብ ትምህርት፣ የአካል እንቅስቃሴ ትምህርት፣ አካላዊ እንቅስቃሴዎች፣ በተመላሽ ክፍያ የት/ቤት ምግብ ፕሮግራም፣ እና ከተመላሽ ክፍያ ምግብ ውጭ ለሚገኙ ተማሪዎች የት/ቤት ምግብና የሚጠጡ ነገሮች ፕሮግራም አሠራርን ይገልጻል።

**MCPS ደንብ KBA-RB፣ የትምህርት አላማዎች እና MCPS የመረጃ አውታሮች አስተዳደር**

ይህ ደንብ ለሞንጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ድረ-ገፅ ቅርፅና ይዘት ይደነግጋል። ድረ-ገፁ የሞንጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርታዊ አላማ ማገልገሉን ያረጋግጣል የሞንጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞችና ተማሪዎችን የግል ገመና (privacy) ስለመጠበቅ መቆጣጠርያ ስልቶችን ይደነግጋል።

**MCPS ደንብ KBA-RC መተርጎም እና ማስተርጎም**

ይህ ደንብ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከሜሪላንድ ስቴት ህግ ጋር በማሳለጥ የመተርጎም እና የማስተርጎም አገልግሎት ሂደቶችን ይደነግጋል፥ እና በዩ.ኤስ. የትምህርት ዲፓርትመንት፣ የሲቪል መብቶች ቢሮ ለ MCPS አገልግሎቶች እና ፕሮግራሞች ትርጉም ያለው የቋንቋ ተደራሽነት መረጃ ይሰጣል። ደንቡ ከፌዴራል እና ከስቴት መመሪያ ጋር በተጣጣመ መልኩ የአስፈላጊ ሰነዶችን ይዘት እና መጠን ይገልጻል።

**MCPS ደንብ KEA-RA፣ በፖለቲካ ዘመቻ ተሳትፎ ማድረግ እና የምርጫ ቁሳቁሶች ስርጭት**

ይህ ደንብ በፖለቲካ ዘመቻና እንቅስቃሴ ስለ ተማሪ ተሳትፎ መስፈርቶች እና ለተሳትፎ ፈቃድ ማግኛ ቅደም ተከተሎችን ይገልጻል።

**MCPS ደንብ KLA-RA፣ ስጋቶች፣ ቅሬታዎች እና ለትምህርት ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት ይግባኝ ማቅረብ**

ይህ ደንብ በተቻለ መጠን በህብረተሰቡ አባላት የሚገለጹ ስጋቶችን በጋራ ለመፍታት ያበረታታል። ደንቡ የህግ አተገባበርን፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ (ቦርድ) ፖሊሲዎችን፣ ወይም የሞንትጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶችን (MCPS) ደንቦችን ወይም ህጎችን በሚመለከቱ የህዝብ ቅሬታዎች ላይ በተለይ ሌላ ድንጋጌ ከሌለባቸው በስተቀር አፋጣኝ እና ምላሽ ሰጪ መፍትሄዎችን ለማግኘት እና ለማስተናገድ የአፈጻፀም ሂደቶችን ያስቀምጣል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፣ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

A. በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት ሁሉም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው፡-
   (1) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ VI፣ እና
   (2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-
      (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
      (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
      (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

እባክዎን የግንኙነት መረጃ እና የፌዴራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ መረጃ ይዘትን በተመለከተ መስፈርቶቹ በዚህ ሰነድ እትም ላይ ተለውጠው ሊሆን ይችላል፥እና በወቅታዊ መረጃ እንደተተካ ልብ ይበሉ። በዚህ ውስጥ የተካተቱትን መግለጫዎች እና ማመሳከሪያዎችን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination

| በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** |
|---|---|
| Director of Student Compliance and Appeals<br>Division of Equity and Organizational Development<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ድጋንብ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የመገልገያ/አኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የመገልገያ/የአኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- |
| Section 504 Coordinator<br>Division of Specialized Support Services,<br>School Counseing Services Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-987-8031 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | |
| Title IX Coordinator<br>Division of Equity an Organizational Development, Student Compliance and Appeals<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org | |

*ይህ መግለጫ ከተሻሻለው የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።
**ይህ መግለጫ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር የተጣለጠ ነው።
***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡-
U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), 61 Forsyth St. S.W., Suite 19T10, Atlanta, GA 30303, 404-974-9406 and TDD: 800-877-8339, OCR.Atlanta@ed.gov, 1-800-421-3481,1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቋንቋ/ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services ስልክ ቁጥር 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, oወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

Montgomery County Public Schools
UNLEASHING POTENTIAL

ህትመት፡- Division of Communications for the Division of School Leadership and Improvement
0890.25ct • Editorial, Graphics & Publishing Services • 7/25 • NP